ምዕራፍ ሁለት

ወ/ሮ ሙሉ የዘረጉትን የቡና ረከቦት አላነሱትም ። የእሳቸው የቡና አፈላል ሁኔታ ከመንደሩ ሴት ሁሉ አፈላል የተለየ ስልት አለው ። የዕቃ አቀራረባቸው ፤ አቀማመጣቸው ፤ የግላቸው የሆነ ፈሊጥ ይታይበታል ። ምንም ቢሆን እርጥብ ነገር ሳይጉዘጉዙ ጨሳጨስ ሳያውዱ የፈካ አበባ ቆሎ ሳይበትኑ ቡና ማፍላትን አይሞክሩትም ።

ይህን ሁሉ ውብትና ንርጋታ ይዞ በቀን አንዴ የሚፈላው የወ/ሮ ሙሉነሽ ቡና በጐረቤቶቻቸው ይናፈቃል ። ዘወትር ቡናቸውን የሚያጫጭሱት ቀትር ላይ ጸሐዩ ሲገር በመሆኑ የሱሰኛን አምሮት ያረካል ። ተማሪዋ ልጃቸው ውዴ እንኳን የመጨረሻው የት/ ቤት መውጫ ደወል ሲደወል ተከታትሎ የሚታያት የናቷ የቡና ሲኒ ረከቦት ነው።

በእንቁጣጣሽ እለትማ ቄጠማው ሥርዶው እንደ ልብ ታጭዶ የተጉዘጉዘበት በመሆኑ በለምለም ቄጠማው መሀል በረከቦቱ ሞልተው የተቀመጡት ነጫጭ ሲኒዎችና ቀደም ሲል በተጠጣው ቡና ጊዜ የተበተኑት የማሽላ ፍንዶች በቤቱ ወለል ላይ በየአቅጣጫው ወድቀው ጉዝጓዙን የአበባ ምንጣፍ አስመስለውት አምረዋል ። የዕጣኑ የቡናው የሰንደሉ የሽቶው የጠላው የምግቡ ፤ ሽታ ተደበላልቆ አንዳንዴም አንዱ ከሌላው አይሎ ከቤቱ አልፎ ደጁን ያውዳል ። ቤቱ ይኸን ሁሉ ትኩስ ጠረን ቢይዝም

ውዴ ስትደርስ በቤቱ ውስጥ ሰው አላገኘችም ። በሩን መለስ አድርገውት እናቷ ወደ መንደር መሄዳቸውን አወቀች ። እንኳን በበዓል ቀን በአዘቦቱም ቢሆን የመንደሩ ሰው ያለውን ተካፍሎ ተሳስቦና ተዛዝኖ የመኖርን ባህል ያጠነከረ ስለሆነ ወደ ተረኛ አስተናጋጅ ቤት እንደሄዱ በማመን በሩን ገፋ አድርጋው ገባች ።

ከምድጃው አጠገብ ወላፈንዋ እሬያዋን እያወረዛው ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ ከምትንተከተከው ድስት የሚወጣው የወጥ ሽታ የመብላት አምሮቷን ቀሰቀሰው ። እረፍት ፈልጋ ስለነበር የውብሸት እንዳይላሉን ትርፍራፊ እንኳን ሳትበላ ነበር የመጣችው ። ነበልባሉ ከጠፋው ምድጃ ላይ የተጣደው የቡና ጀበና አልፎ አልፎ ቱግእያለ እንፋሎት ይተፋል ። ሰተት ባለው ሰፌድ ላይ ቀይ ጨርቅ ለብሶ የተቀመጠው ዳቦ ደረቱን ነፍቷል ። በገንቦ የቀረበው ጠላ ይብላላል ።

መኝታውም መቀመጫውም ምድጃውም ማጀቱም አንድ ላይ የሆነባትን መኖሪያ ቤታቸውን በዓይኖቿ ከማተረች በኋላ አንጠልጥላው የገባችውን ባዶ ዘንቢል ወደ መዝጊያው ሥር ወርውራ በእፎይታ ከትንሿ ድንክ አልጋ ላይ ተዘረጋች ። ከእንቁጣጣሽ ዋዜማ ጀምሮ በቅቤ የተነከረ ጨሌና ጥብቆ አጥልቀው ከቤት የማይወጡት እናቷ ያለወትሮአቸው በጨሌያቸው ማግስት ከቤት ወጥተው መገኘታቸውና የዕቃው ሁሉ ለብቻ መቀመጥ ገርሟት እናቷን ልታይ ቸኮለች ። ወ/ሮ ሙሉ ከሚጠሉት ነገር አንዱ ከሄዱበት መንደር ወይም ጐረቤት አውቀው ካልመጡ በቀር የሚጠራቸውን ሰው በመሆኑ ፤ ውዴም ይህን አመላቸውን እንድታውቅ ብዙ ጊዜ ተቆንጥጣ የተማረች ስለሆነ ፤ ለመፈለግም ለመጥራትም አልሞከረችም። እስኪመጡ መታገስ ነበረባት ።

በእናትዋና በጨሌያቸው መገረሚን ትታ ፤ የዋለች
በትን ሁኔታ በሀሳብ ተመለሰችበት ። ሥራዋን ጨርሳ ስት
ወጣ ውብሸት እንዳይላሉ የሰጣት አስራ አምስት ብር
ደስታም ጭንቀትም እንደ ፈጠረባት ተሰምቷታል ።
በተሰጣት ብር ምን እንደምትገዛበት ማሰላሰል ጀመረች ።
በግልጽ ከነገራት ምክንያት ሌላ ያሰበው ካለም በሚል
የተለያዩ መላዎችና ጥርጣሬዎችን ገመተች ። ዞራ ዞራ
በድኅነትዋ አዝና ሊረዳት ማቀዱን አምና ይህን ሀሳብዋን
ገፋችው ። ቀጥሎም የታየች አባ ጨፍቅ የተሻለ ሥራ
ለመስጠት መሰናዳትና ያሳየቻት የምናብ ኑሮዋ ትርኢት
ተራ በተራ በዐይነ ሕሊናዋ ታያት ። ኑሮአቸውንና ቤታ
ቸውን ከዚያኛው አኗኗርና ጠቀሜታ ጋር እያወዳደረች
ይኸኛውን ጠላችው ። ቁርቋሬው አዲስ ሆኖ ተሰማት ።
እንዴትና በምን መልኩ አስረድታ እናቷን አሳምና እንደ
ምትጀምረው ጭንቅ ቢላትም የታየች አዲስ ሥራ እያ
ጓጓት መጥቶአል ።

ከትምህርት ሰዓት በኋላ በታማኝነትና በጥሩ ችሎታ
በውብሸት እንዳይላሉ ቤት በአስራ አምስት ብር ጀምራ
በዕድገት ሃያ ብር ደርሳ የምታገኘውን ገንዘብ ለእናቷ
በየወሩ ተቀብላ ትሰጣለች ። ወ/ሮ ሙሉም ሃያውን ብር
ከራሳቸው የጥረት ውጤት ጋር አቀናጅተው ለኑሮአቸው
ያብቃቁታል ። ለወር ቀለብ ፤ ለቤት ኪራይ ፤ ለልዩ ልዩ
ወጪ ከሸነሸኗት በኋላ ውዴም በጓደኞቿ መካከል የሚ
ያስጠይፍ ለብሳ እንዳትሄድ ፤ ሽራ ጫማ እንኳን እንዳታጣ
ይጥራሉ ። ከዚህ በተጨማሪም በወንድማቸው ቤት የምት
ገኘውን የአልጋ ቁራኛ ሆና የቀረች ሽባ ልጃቸውን ምን
ተስኖትን አልፎ አልፎ ይጠይቁበታል ። ወ/ሮ ሙሉ ፈት
ለውና የአክርማ ስፌት ሰፍተው ይሸጣሉ ። ጠላውንም
አረቄውንም አውጥተው እየሸጡ ሞክረውታል ። ምንም

እንኳን አብዛኛው ድጋፍና እርዳታ የወንድማቸው ቢሆ
ንም ታማሚ ልጃቸውን በሳምንት አንድ ቀን አይተው
ልብሷን አጥበው መኝታዋን አራግፈው ቤቷን ጠርገው
ይመጣሉ ። የነበራቸው የጀሮ የጣትና የአንገት ወርቆች
ተሸጠው ለዚሁ ችግራቸው መቅረፊያ ለልጃቸው ማስታ
መሚያ ውሏል ። ጥሪታቸው ከተሟጠጠ በኋላ ነበር ወን
ድማቸው በሽተኛዋን ልጃቸውን በቤታቸው ሊረዱ የወ
ሰዱዋት ። ዋናው የወ/ሮ ሙሉ ጥረት ደግሞ ውዴን አስ
ተምረው በልጃቸው ድጋፍና እርዳታ ከያዙት የድቀት ኑሮ
ለመውጣትና ውዴ ለእሳቸውም ሆነ ለታማሚ ህእቷ አለ
ኝታ እንድትሆን ማሰናዳት ነበር ። ይህን ሁሉ የናቷን
መንገላታትና መጣር አስባ ውዴ ትክዝ ብላ ጥቀርሻ ባዘ
ለው የቤቱ ጣራ ላይ አፍጥጣ ቀረች ። እናቷ ለኔ ብለው አስ
በው የብር ሻሽ የገዙበትን ዘመን መራቅ አሰበችው ።
ውብሸት እንዳይላሉ በሰጣት ብሮች ለእናቷ የምትገዛላ
ቸውን ስጦታዎች አማረጠች ። የገንዘቡ ማነስ የልቧን አላ
ደርስ አለና መርጣ መርጣ ተወችው ። ጥሬውን ገንዘብ
ልትሰጣቸው ወስና ተዝናንታ ጋደም አለች ።

እንደገና ውብሸት እንዳይላሉ በሀሳብዋ መጣ ፤
ቁመናው ፤ አነጋገሩ ፤ አሳሳቁ ዝምታውና አከባበዱ ታያት
“ ቅድም ሳየው ምን አስደነገጠኝ ” አለችና ራሷን መረ
መረች ። ሊገባት አልቻለም ። “ ካዘነልኝ ምን ነበረበት
ይቺን አስራ አምስት ብር ሃያ ወይም ሰላሣ ቢያደርግልኝ
ኖሮ ፤ ለእማዬ ቀሚስ አሰፋላት ነበር ። ” አለችና ምኞ
ትዋን እያሰላሰለች ሳቀች ። ወዲያውም የመጡት ሴቶች
ትዝ አሏትና በተደረገው ትርኢት ተገረመች ። ከሚመጡት
ሴቶች ሁሉ በትህትናና በመውደድ አነጋገር የምትቀር
ባት ሕሊና መሸሻ ስለነበረች ስለ ህሊና ተቆጨች ።

ከተጋደመችበት ተነስታ ከድንኩ አልጋ ስር ያለች ውን ትንሽ የእንጨት ሳጥን ጐትታ ከፍታ ትንሿን መስታወት አውጥታ ገጽታዋን በጥንቃቄ ተመለከተች ። ፈገግ ሣቅ ፤ ፍዝዝ ፤ ትክዝ ፤ ኮስተር ፤ ኮስተርተር ደሞ ሣቅ እያለች በተለያዩ ስሜቶች ውስጥ የሚኖራትን ውበትና የመልክ ክፋት አየች ። የራሷን ምስክርነት ለራሷ ሰጠች ። ቢደላኝ ኖሮ ከሕሊና መሸሻ የማላንስ ቆንጆ እሆን ነበር አለች ። የታየች አባ ጨፍቅን አገላለጽም እውነት ነው ብላ ተቀበለችው ።

ታየች አባ ጨፍቅ የነገረቻት ሁሉ ቃል በቃል በእዝነ ልቡናዋ አስተጋባ ፤" . . . ትምህርትሽን እየተማርሽ ኮት/ ቤት መልስ በቡና ቤቱ ውስጥ የሂሣብ ሠራተኛና ኃላፊ ሆነሽ ትሰሪያለሽ ። ከዚህም ሌላ መልክሽና ቁመናሽ ቅርጽሽ ለማድቤት ሥራ የሚገባ አይደላም ። እግዜር የሰጠሽን ጸጋ ተጠቀሚበት ። ሰውን ሰው የሚያደርገው እድልና ገንዘብ ነው ። ታዲያ አንቺ ታድለሻል ። ትዳር ከፈለግሽም አሳምሬ እድርሻለሁ በመልክሽም ቢሆን ረብጣ ብር የሚረግጠውን ነጋዴ ወይም ቱጃር ማንበርከክ ትችያለሽ ። ከድኅነት የምትወጪበት መንገድ በጣም ቀላል ነው ። እንደ ታላቅ እህትሽ ተመልከቺኝ ። ሕይወትሽን ለማስተካከል ቅረቢኝ ። በቅርቡ እንደምትመጪ ተስፋ አደርጋለሁ ። " ፊትዋ ላይ ፈገግታ ተነጠፈ ።

ታየች አባ ጨፍቅ ገና በልጅነትዋ ለባል ተድራ ባልዋ ሸማግሌና አንድ ዐይና ስለነበር ጠልታው ካንድ ከወደደችው ልጅ እግር ባላገር ጋር ተመካክረው ሲጠፉ ፤ሜካ ሜካውን ከሰው ተሸሽገው ሲጓዙ ፤ ቅሪት ኖራ በእንግልቱ ምክንያት ደም ሲመታት የሞተውን ሽል ከማህጸኗ ለማስለቀቅ ያ ብቸኛ ሰው ግራ ተጋብቶ እትብት መቁረጫ እንኳ ስላልነበረ በባልጩት ቆርጠው ሽሉን በዚ

ያው በዱሩ ውስጥ ቀብረው ከብዙ እንግልት በኋላ ወደ መንደር ሲደርሱ በማሕጸንዋ ውስጥ በቀረው የእንግዴ ልጅ ምክንያት አብጣ ለሞት ደርሳ እንደነበርና የመንደሩ ሴቶች ተጋግዘው ተጠራርተው በወጌሻ እርዳታ ትራፊውን አካል አውጥተው ከሞት ቢያተርፏትም ዳግም ማኅጸንዋ ልጅ እንዳያፈራ ሆኖ እንደ ተሰነከለ ታውቃለች ።

ታየች አባ ጨፍቅ ፍቅር ተከትላ ስትሰደድ በደረሰባት ችግር እስከመጨረሻው ልታገኝ የማትችለውን እጦትዋን ለማካካስ ስትል ውዴን ድንገት አይታት ቀልብዋ ስለ ወደዳት እንደ ልጅ ለማሳደግና ምናልባትም የንብረትዋ ወራሽ ለማድረግ በመከጀልዋ ያደረገችላት ጥሪ የውዴን ልብ መኮርኮሩ አልቀረም ።

ዴጋግማ ያነሳችላት የቅርጽዋን ውበት የምታይበት ከፍ ያለ መስተዋት በቤቱ ውስጥ ባለመኖሩ ፤ ያሰበችውን ሌላ ዘዴ ለመሞከር ወደ ደጅ ወጣች ። መንገድዋ ወደ ምዕራብ ያዘቀዘቀ የምሽት ጸሐይ ሙሉ በሙሉ ከጀርባዋ እንድታርፍባትና ከሥሯ የሚወድቀውን ጥላ ለማየት ጀርባዋን ለጸሐይ ሰጥታ ቆመች ። ረዘም ብሎ ከእግሯ ሥር ተነስቶ የወደቀው ጥላ ቅርጽ አላረካትም ። በተለያዩ የአቋቋም ስልቶች ሞክራ ራሷን አሟልቶ የማያሳያት በመሆኑ ትታው ተመልሳ ገባች ።

ምንም እንኳን ስሙ " ቡና ጠጡ" ቢሆንም በበዓል ቀናት ያገር እድርና ወግ ሆኖ ሁሉም በየቤቱ እንደ አቅሙ ያሰናዳውን ሁሉ በጋራ ለመቃመስ ይጠራራልና ወ/ሮ ሙሉም በቡና ስም አካባቢውን አዳርሰው ተጋብዘው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ልጃቸው ከድንክ አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ እንደ ማሸለብ አድርጓት ይደርሳሉ ። ግንባሯን ሳም አድርገው ከጐኗ ቁጭ ሲሉ ብንን ብላ ትነሳለች ። ጭንቅላ

ትዋን ጭናቸው ላይ አሳርፈው በጸጉሯ ውስጥ ጣቶቻቸውን አስገብተው እያሻሹዋት ውሎዋን እየጠያዩቁዋት በዐውደ ዓመት ቀን እንኳ እቤትዋ አርፋ የተገኘውን በሥርዓቱ ሳትቃመስ በመዋልዋ እዝን ብለው እንባ ባዘለ ዐይን ተመለከቷት ።

ወዲያውም እጃቸውን ተጣጥበው እንጀራ አቅርበው ባፍ ባፍዋ እያጐረሱዋት እያጨዋወቱዋት ፤ ያሰናዶችውን ጠላና ዶሮ አሠሪዋ ማድነቅ አለማድነቋን እየጠየቁዋት ምሳዋን ጠገባ በላች ። ሥራው የሚያደክማት ሆኖ ዛል ስትል ስለሚያዩ ሁልጊዜ ይህን የችግር ኑሮ መቼ እንደ ሚላቀቁት ያሰላስሉታል ።ውዴ ደግሞ እንዴት በጨሌ በዓላቸው ማግስት ያለ ልምዳቸው ከቤታቸው ወጥተው ከሰው እንደ ተቀላቀሉና ለምንስ ሥርዓቱን እንዳጓደሉ ለማወቅ በጉጉት ወተወተቻቸው ። መልስ ሳይሰጧት ለብዙ ጊዜ ወደ ደጅ እየተመለከቱ በዝምታ ተውጠው ቀሩ ።

እንደ ወትሮአቸው ቢሆንማ ፤ ወ/ሮ ሙሉ የጐመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ እያሉ በቤታቸው አራት ማዕዘን እየዞሩ ጪስ ከወጉ በኋላ የችቦ ነበልባላቸውን ይዘው ወጥተው ከጐረቤቶቻቸው ጋር ደምረው በነበልባሉ ዙሪያ ከሚኮለኮሉት አረጋውያን ሕጻናትና ወጣት ጐረቤቶቻቸው ጋር ተሳስቀው ተመራርቀው ገብተው በዓመት አንድ ጊዜ ከእንቁጣጣሽ ዋዜማ ጀምሮ ለሶስት ቀናት የሚለብሱትን የጨሌ ጥብቆ አጥልቀው ሊሞሽሩ ይዘጋጃሉ ።

በጥንቃቄ ሲዘጋጅ የሰነበተው የምግብ ዓይነት በዙሪያቸው ይኮለኮላል ። ጌሾ አልባው ጠላ ወይም እምቡሽቡሽ በትንሽ ገንቦ ቀይ ጨርቅ ጠምጥሞ ከጐናቸው ይሰየማል ። ጨው የሌለው የበሰለ ቅንጨ ይቀርባል ። በበርበሬና በቅቤ ልውስ የራስ አነባበሮ ይዘጋጃል ። ያልተፈለፈለ ቡና በጣባ ይቀርባል ። የኑግ ልጥልጥ ጣል ጣል የተደረገበት የገብስና የሽንብራ ቅልቅል ቆሎ ሰፋ ባለ መሶበ ወርቅ ሞልቶ ይቀመጣል ። ለጋ ቅቤ ጮጮ በምትመስል ትንሽ ያጌጠች ቅል ይቀርባል ። ለጋና ለምለም የሠርዶ ሣር በጥንቃቄ የተጐዘጐዘበት ወንፊት የጨሌ ሙዳይም በክብር ይሰየማል ።

በየዓመቱ የሥርዓቱ ተኪፋይ የሆኑት ጐረቤቶች ይጠሩና በልዩ ልዩ ምግብና የምግብ እቃዎች መካከል እግራቸውን ዘርግተው የሚቀመጡት ወ/ሮ ሙሉ የጨሌ በዓል ሥነ ሥርዓታቸውን በቡና መቁላት ይጀምሩታል ። ቡናውን ከቆሉና አድባርዋን ካሸተቱ በኋላ ያልተፈለፈለውን ድፍን ቡና በቅቤ ጠብሰው በጣባ ገልብጠው ያስቀምጡታል ። ሠርዶ የተጐዘጐዘበትን ወንፊት አንስተው ከጭኖቻቸው ላይ ካስቀመጡ በኋላ የጨሌዋን ሙዳይ በጥንቃቄ ከፍተው በአንገታቸው ላይ ማጥለቅ ሲጀምሩ እንደ ወ/ሮ ሙሉም የጐረቤቶቻቸው እልልታ ይቀልጣል ። ጨሌያቸውን በደረታቸውና በትላልቅ ጡቶቻቸው ላይ ካንዠረገጉት በኋላ የቀለጠውን ቅቤ በሰርዶ ዘለላ እየነከሩ “ አቴቴ ሲፋ . . . .አቴቴ ዱላ . . . አቴቴ ጊምቢ” እያሉ እያነበነቡ በአንገታቸው ዙሪያ ያለውን ጨሌ ሲቀቡት እልልታው ይደጋገማል ።

ከዚህ በኋላ ወ/ሮ ሙሉ በቅቤ ከጠበሱት ድፍን ቡና መካከል ሲቆረጥሙ የጨሌውን በዓል ሊያከብሩ የተሰበሰቡት ጐረቤቶች ከድግሱ ይጋበዛሉ ። “ አቴቴ ደምቧ ነው” የሚሉት ባልቴቶች ጨው የለሽ ቅንጨና ጌሾ አልባ ጠላውን ሲጠጡ ፤ አብዛኞቹ ሽማግሌዎችና ወጣቶቹ

ደግሞ ጨው ጨምረው ይበላሉ ። እምቡሽቡሹን ወይም
የበዓሉን ጠላ ይጠጣሉ ።

የጨሌው በዓል በዚህ ሁኔታ እየተበላ እየተጠጣ
ረዘም ላለ ጊዜ ይቆይና ሁሉም በየቤቱ ሲሄድ ወ/ሮ ሙሉ
ደግሞ የጨሌ ሙዳያቸውንና ወንፊቱን በስተራስጌ
አድርገው በዚያ ዕቃ ሁሉ መሀል መጋደሚያቸውን አመ
ቻችተው ቡልኮ ደርበው ይተኛሉ ።

ዘንድሮ ግን ጨሌያቸውን ያከበሯትና የደገሱላት
ልባቸው እሁለት ተከፍሎ ነው ። የስለታቸው ነገር ፍንጭ
የማይሰጥ የዘወትር ልመና ሆኖ በመቅረቱ ተስፋቸው መን
ምናለች ። ከመቼውም ዘንድሮ ጨሌያቸውን ያነሷት
ቅሬታ ውጠው ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ነበር ።

እድሜ እየጨመረች በትምህርትዋ እየበሰለች ከዓ
መት ወደ ዓመት ልጃቸው ውዴ በምትተቻቸው ትችት
ብቻ ሳይሆን የራሳቸው መንፈስ የሚጨብጠው እያጣ
በፈጠረው ቅሬታ የተነሣ ከብዙው ሽርጉድ ተቆጥበዋል።
ጨሌያቸውን ባጠለቁ በሶስተኛው ቀን የመሸኛ ድግስ
ቢጤ ተደርጐ ጐረቤት ተጠርቶ የተዘጋጀው ቅንጨ ቂጣ
ውም ተበልቶ ስለት ተደርጐ ፤ ምርቃት ፈሶ ፤ ጨሌው
ሙዳይ ኮገባ በኋላ ደጅ ወጥተው ጸሐይ ይነካቸው ነበር ።
በዘንድሮው ዘመን ግን ሁኔታቸው ሁሉ ከአስራ አንድ
ዓመታት አድራጐታቸው ሁሉ እጅግ ያነሰና የተላየ የም
ንግዴ ዓይነት ነበር ። በዕለተ እንቁጣጣሽ ከጐረቤት ተቀ
ላቅለው ሲበሉ ሲጠጡ መዋላቸው ጐረቤቱን ሁሉ የገረ
መው ሲሆን ፤ ባልቴቶቹ ግን ሥርዓቱን በማጓደላቸው
የሕመም ቅጣት ወይም ዱብ እዳ ችግር እንዳይደርስባቸው
እየፈሩላቸው ተጨንቀዋል ።

ባለ ጥልፍ የዱሮ ጉዳ ቀሚሳቸውን በመቀነት ሸብ
አድርገው በላዩ ቀይ ጥለት በለሴ ነጠላቸውን ከትከሻቸው
ላይ ሰብሰብ አድርገው ለብሰው ፤ የአደስ ሽታ ያጣፈጠ
ውን ለጋ ቅቤ ተቀብተው ከደርባባነታቸው ጋር አምረው
ይታያሉ ። ወ/ሮ ሙሉን ልብ ብሎ ለተመለበታቸው ግን
የሕሊናቸውን መቁሰልና የመንፈሳቸውን መሰበር ከሁ
ኔታቸው መረዳት ይችላል ። መራመድና መናገር ተስ
ኗት ከጊዜ በኋላ ባደረባት ሕመም መንምና ተሽመድምዳ
የአልጋ ቁራኛ የሆነችውን ልጃቸውን ጉዳይ እንደ ሚያ
ሰላስሉ የኋሊት በሷ ነገር እንደሚጐተቱ ያስታውቃሉ ።
ለሷ ሲሉ ሀኪም ቤት ፤ ጠንቋይ ቤት ፤ ጠበል ፤ እያሉ ያል
ሞከሩት ነገር የለም ። ስለት በስለት ላይ ቢደርቡ ፤ ለጨ
ሌያቸውም ቢጠነስሱ ቢደግሱ ፤ የተስፋ ፍንጭ ሳይታይ
ልጃቸውም የታየባት ለውጥና መሻሻል ሳይኖር ዓመ
ታት አለፉ። ወ/ሮ ሙሉ የጨሌ እምነታቸውም እየጠወለገ
አድራጐታቸው ቀዘቀዘ ። ወ/ሮ ሙሉና ጨሌ ተቀያይመው
ታዩ ። ያልደመቀች ጨሌያቸውን ትተው ከጐረቤት የተ
ቀላቀሉት አለነገር አልነበረም ።

የውብሸት እንዳይላሉን ቤት የበዓል መሰናዶ ስታ
ደራጅ ቆይታ ለመጣችው ልጃቸው ቡና አፍልተው ሊያ
ጠጡ ምድጃቸውን ቆስቁሰው ወቅጠው ኳስቀሩት ቡና
ከጀበናው ጨምረው በረከበቱ ላይ ያሉትን ሲኒዎች በን
ጹህ ውሀ ለቃለቋቸው ። ቡናው ሳይወርድ በማጨሻው ላይ
እሳትና ጪሳጪስ አድርገው ኳደማመቁት በኋላ ቀና
ብለው ልጃቸውን ሲያዩ በድንክ አልጋዋ ላይ በጀርባዋ
ተኝታ በሀሳብ ተሰውራለች ። ልብ ብለው ተመለከቷት
እንደ እናትነታቸው በልጃቸው እድገት ፤ ቁመና ማማር ፤
የመልክ መዋብም አይደሰቱም ። እድሜዋ በጨመረ
መጠን ከልጅነት ወደ ወጣትነት ከዚያም ሴትን ሴት ሊያ

CamScanner

ሰኛት የሚያስችሏትን የአካል ለውጦች ባዩባት ቁጥር ልባቸው ይወጋል ። ይሰቀቃሉ ። ያዝናሉ ። ይሰስቷታል ። ምንጊዜም ልጅ ሆና ከአጠገባቸው ሳትለይ ከእቅፋቸው ሳትወጣ ብትኖር ይወዳሉ ። የጐረቤቱ አፍ ፤ የአካልዋ እድገት ፤ የትምህርትዋ መጠናከር ፍርሃት ካሳደረባቸው ሰንብቷል ።

ውዴ ግን እንደገና ታየች አባ ጨፍቅ በሳለችላት ኑሮና ጥቅም ውስጥ እየተመላለሰች ያለችበትን ጐስቋላ ሕይወት ማወዳደር መመርመር ይዛ ነበር ። የተለያዩ ሀሳቦች ይመላለሱባታል ። አንዴ ፤ የቡና ቤቱ ሂሣብ ሠራተኛ ሆና በምታገኘው ደመወዝና በመልኳና ከቁመናዋ ሳቢያ በሚቀርብላት በረከት በመነሣት ከዚህ የድኅነት ማጥ እና ቷንና ራሷን አውጥታ ሌላ ሰዎች ሆነው ሌላ ኑሮ ሲኖሩ ይታያታል ። እንደ ገናም ፤ በቡና ቤት ሥራ አካባቢ የተቆራኙት በዝና የምትፈራቸው ችግሮች ገጥመዋት ዘወትር እናቷ የሚያወግዙት የሚኮንኑት ገመና ደርሶባት ወደ ባሰ አዘቅት ስትሰምጥ ይታያታል ።

በዚህ በሁለቱ የሀሳብ ኑሮ ውስጥ ሽር ጉድ ስትል እጆችዋን ለጭንቅላትዋ አንተርሳ ዐይኖችዋ በአንድ አቅጣጫ እንደፈጠጡ መንፈሷ ተሰልቧል ። የሀሳብዋን ምንነት ባያውቁም በከባዱ መመሰጧን ያስተዋሉት እናቷ ፤ ከምድጃው አጠገብ ተነስተው ከድንኩ አልጋ ላይ እግሯን ገፋ አድርገው ተቀመጡ ።

“ ምነው ውድዬ ምን ሆነሻል ” አሏት ጭንቅ ብለው፤

“ ድክም ብሎኛል እማዬ ” አለቻቸው ሰፋ ያለ ቦታ ለመልቀቅ ወደ ኋላ መላ ሰውነቷን እያሸሸች ።

“ የለም ውድዬ የድካም ብቻ አይመስልም ሀሳብ ገብቶሻል ፤ ከፉኛ የምታሰላስይው ነገር ይዞሻል ፤ እስቲ

ንገሪኝ የሆንሽውን ሁሉ ” ዐይን ዐይኗን እያዩ እግሮቿን ያሻሹ ነበር ።

“ እማዬ ሙች የሆንኩት የለም ። ስለደከመኝ ብቻ ነው ” አለችና ከተጋደመችበት ተነስታ ቁጭ አለች ።

“ የለም ንገሪኝ ልጄ ችግራችንን በጋራ ካልያዝነው ትርፉ ሀዘንና የባሰ መከራ ነው ። የምታሰላስይው ነገር አለሽ ። ሳትፈሪ ንገሪኝ ውድዬ ላንቺ ከኔ ወዲያ ማን ይመጣል ፤ ለኔስ ካንቺ ወዲያ ማን አለኝ ” ድምጻቸው ሰብር አለ ።

“ እሺ ልንገርሽ እማዬ ” ብላ ፈገግ ስትል የምትነግራቸውን ሊሰሙ መንፈሳቸውንና ሰውነታቸውን ሰብስበው ጭንቅ ብለው ተዘጋጁ ።

“ ይኸውልሽ እማዬ ፤ ዛሬ ሥራዬን ጨርሼ ስወጣ ጋሼ ውብሸት ለደብተር መግዣ ይሁንሽ ብለው ብሮች ሰጡኝ ። እኔ ደግሞ በዚህ ገንዘብ ምን እንደምገዛልሽ ባስብ ባስብ ገንዘቡ ላሰብኩት ሁሉ በቂ ስላልሆነ መምረጥ አቃተኝ ። የማሰላስለው ይህንን ነበር ። ”

ነጠቅ ብላ ተነስታ ደብተሮችዋ መሀል ያስቀመጠችውን የአስርና የአምስት ብር ኖት አውጥታ ወ/ሮ ሙሉ በሚወዷቸው አማልክትና በፍቅራቸው ተማጥና ትክሻቸውን አቅፋ ደስ ያላቸውን ነገር እንዲገዙበት ለምና በእጃቸው አስጨበጠቻቸው ።

ሲሰቀጥጣቸውና ውስጣቸው ሲሸማቀቅ በቅስማቸው መሰበር ታየ ። ፊታቸው ቅሬታ ተላበሰ ። ለምን እንደተሸማቀቁ ፤ ለምን እንደከፋቸው ባታውቅም በሁኔታቸው ልጃቸው ደነገጠች ።

" ምነው እማዬ ለምን ቅር አለሽ " አለ ቻቸው ፡፡ የሚሉትን ልትሰማ ዐይን ዐይናቸውን ብታይም የሷን ጥያቄ እምብዛም ሳያጤኑ እጃቸው ላይ ያረፈውን ገንዘብ እንደ ቀፈፋቸው በሚያስረዳ ሁኔታ ከድንኩ አልጋ ጠርዝ ላይ እያኖሩ ፤

" ለመሆኑ ውድዬ ሰውየው ትዳርም አያስብ? እጮኛስ የለውም ?" አሏት

" እጮኛማ አለችው ፤ በቅርቡ እንደሚጋቡ ሲያወራ ሰምቻለሁ " አለቻቸው ፈጥራ ያቀረበችው መልስ ነበር እንጂ በውል የምታውቀው የውብሸት እንዳይላሉ ፕሮግራም አለመሆኑን ህሊናዋ ያውቀዋል ፡፡

በረዥሙ ተንፍሰው ጥቂት ዝም ካሉ በኋላ ፤

" ምን ዛሬ እንኳን በቀጠሮ ላይ ያለ ጋብቻና በሕግ ታውቆ ይፋ የተቀናጁት ባልና ሚስት እንኳ እግዚአብሔርን ፈርተው ትዳራቸውን አክብረው አንዱ ለሌላው ታምነው አልተገኙም ፡፡ እንዲያው ችግር ነው ውድዬ " አሉ በቅሬታ የተዋጠ ፊታቸውን ወደ ልጃቸው መልሰው፡፡ የህሊናዋን እውነት የሚያዩት ይመስል ዐይኖቻቸውን በዐይኖቿ ላይ ተክለው በትኩረት እየመረመሩት ፡፡ጥርጣሬያቸው ገባት ፡፡

" እማዬ ሰውዬው ገንዘብ የሰጡኝ እኮ አዝነውልኝ ነው ፡፡ ሁልጊዜም በትምህርቴ ጠንክሬ ራሴን እንዳሻሽል ይመክሩኛል ፡፡ ይህንንም ገንዘብ የሰጡኝ ለአስረኛ ክፍል ትምህርቴ ደብተር መግዣ እንዲሆንሽ ብለውኝ ነው ፡፡ እንዳየሻቸው ደግሞ በዕድሜም በክብርም ትልቅ ሰው ናቸው ፡፡ እኔን ለምንም ሌላ ነገር አያስቡኝም ፡፡ በዚያ ላይ

እቤታቸው የሚመለላሱትን ሴቶች ዓይነትና ቁንጅና ብታይ ትገረሚያላሽ ፡፡ ለኔ ግን በድኅነቴ ሊረዱኝ አስበው ነው"

" አይ ልጄ አሉ" ትክዝ ብለው ፤

" አይ ልጄ ፤ በዕድሜዬ ያየሁት ብዙ ነው ፡፡ ያሳለፍኩት ብዙነው ፡፡ የማውቀው ብዙ ነው ፡፡ ወንድ ሲያደባ ትሁትና ገራም ፤ ደግና ተቆርቋሪ ይሆናል ፡፡ መንጠቅ የሚፈልገውን ነገር እስኪነጥቅ በስጦታ በውለታ ያዘናጋል ፡፡ ወንድ ምንጊዜም ብልጠትና የበላይነትን ስለሚፈልግ እስኪ በልጥ ድረስ ሁን ያሉትን ይሆናል ፡፡ ይታመናል፡፡ይታዘዛል ፡፡ ያሰበው ነገር ሆኖ ፤ የልቡ ከደረሰ በኋላ የተቀበረ ጠባዩ ይወጣል ፤ የለመነውን የተለማመጠውን ያህል ለምኑኝ ይላል ፡፡ ደጋግ ሀሳብ በተናገረበት አንደበቱ ፤ ሙገሳና አክብሮት ባሰማበት አፉ ፤ ከሬት የመረረ ቃላት ይተፋል ፡፡ ብቻ ዋናው ነገር አለመበለጥ ነው ውድዬ "

" እንዴ እማዬ "

ንግግርዋን አቋረጣት ፡፡

" የለም ውድዬ ቁስል አለኝ ፡፡ ከብዙ ዓመት በፊት የቆሰለ ቁስሌ አሁንም እንዳመረቀዘ ፤ አሁንም እንደደማ ነው ፡፡ ቀን ቀን ቀልቤ ከሰው መሀል ሲነጥቀኝ እኔው እኔን ሳዳምጥ የማመነዥከው ፤ ሌሊት አገር እርጭ ብሎ በሰላም ሲያንቀላፉ የሚጠዘጥዘኝ ፤ የማልመዘምዘው ችግር አለኝ ፡፡ ውድዬ ልጄ ከእንግዲህ ነገር የማይገባሽ ልጅ አይደለሽም ፡፡ ለዚህ እድሜ ለዚህ ደረጃ በቅተሽ አምቄው የኖርኩትን ችግሬን ፤ ሸፍኘው የኖርኩት ቁስሌን ፤ ዕለት ተዕለት የሚያደማኝን የልቤን ሕመም ገልጬ አሳይሻለሁ ፡፡ አምላኬ ምስጋና ይግባው ለዚህ ደርሰሽልኛል ፡፡ "

ቀና ብለው ሲያዩዋት በዐይኖቻቸው ዙሪያ ተጠራቅሞ የነበረው እንባ ተዘረገፈ ። እንዲህ ከመቅጽበት ቅስማቸውን ሰብሮ ለከፋ ትካዜና ለቅሶ የዳረጋቸውን ጉዳይ ባለማወቋ ውዴን ግራ ገባት ። አለቃቀሳቸው ሲቃ እየታከለበት ፤ ቃላቸው ከጉሮሮአቸው ሊወጣ እየቸገረው ድምጻቸው እየሻከረ ሄደል ። የቧም አንጀት አልችል ብሎ እንባዋ ወረደ ።

“ ምነው እማዬ ምን አጠፋሁ ፤ በምን አስቀየምኩሽ ፤ ገንዘቡን ተቀብዬ መምጣቴ ጥፋት ከሆነ ልመልስላቸው ፤ ሁለተኛም ይኸን አልደግመውም ” እያለቀሰች ተማጸነቻቸው ።

“ ውድዬ ሌላ ሞት ፤ ሁለተኛ ሞት ፤ ከመሞቴ በፊት የምነግርሽ አለኝ ። ልብ ብለሽ ስሚኝ ፤ ለብዙ ያሰብኳት ብዙ የተማመንኩባት ልጄ ፤ ተጫውታ ሳትጠግብ አምራ ሳያልፍባት ፤ ሠርታ ሳትደክም ፤አልጋ ተቆራኝታ ፤ ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ ሆና የምትገኘው በልጅነትዋ በየዋኅነትዋ ተጠግቶ ፤ እወድሻለሁ ብሎ ያታለላት ወንድ በፈጠረባት ችግር አርግዛ በድብቅ አስወርዳለሁ ብላ ስራ ስሩን ጠጥታ ውሎ አድሮ በደረሰባት የአእምሮ መቃወስ ምክንያት ነው ። ውድዬ በሷ ሞቻለሁ ። እሷም ሞታለች፤ አለችኝ ብዬ ለመናገር አልደፍርም ። እንደገና ደግሞ ሌላ ሞት መቀበል አልችልም ። በየቤተክርስቲያኑ እየዞርኩ የወደቅሁበት የተነሣሁበት ስለት ነበረኝ ። ልጄ ሰው ሆና ተራምዳ ፤ እንደበቷ ተፈትቶ ተናግራ ፤ ካለኝ ይዞታዬን፤ ከሌለኝ ለምኜም ቢሆን ለፈጣሪዬ ለአማልክት በረከት መስዋዕት ላገባ ተማጽኜ ነበር ። አልሆነልኝም ። “ ጨሌ ከጌጥነት ሌላ ምን ይረባል ። እንዴት ሰው በእጁ በሰካው ጨሌ ያመልካል፤ያምናል ” ስትይኝ የመረረ ጸብ የምጣላሽ ከጭንቀት የተነሣ ሁሉንም ሞክሬ ይሆንልኝ ይሆ

ናል የሚል ተስፋ ይገኘ ነበር ። ብዙ ዓመት አለፈ አንዱም ጸሎቴ አንዱም ስለቴ አልሠመረ ። ለዚህ ነው ዛሬ የጨሌ ጥብቆ አውልቄ ጥዬ ከሰው ተቀላቅዬ አምላኬ የፈቀደው ይሁን ብዬ ስወዛወዝ የምታይኝ ። ተረትቻለሁ ። ልጄ አንጀቴ ለሌላ ሞት አሳልፈሽ አትስጭኝ ። ከዚህ የድኅነቴ ኑሮ ተምረሽ የረባ ሥራ ይዘሽ ታወጪኛለሽ ፤ ለእህትሽ ያለሻት ተስፋ አንቺ ነሽ ብዬ ስለማምን ውድዬ ተጠንቀቀሽ ለወግ ድረሽልኝ ።”

የሷን ጭንቅላት ከትላልቅ ጡቶቻቸው ላይ አስደግፈው ራሳቸውን ከሷ ላይ ዘምበል አድርገው እንደ ሕጻን ልጅ ሰብሰብ አድርገው አቅፈው እንደ እሽሩሩ አወዛወዟት ። እሳቸውም ብሶታቸው እያስለቀሳቸው አብረዋት ተወዛወዙ ።

ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም ሳይነጋገሩ የግል ስሜታቸውን እያፍተለተሉ ተቃቅፈው ቆዩ ።

“ እሺ ውድዬ ” አሏት በሚያባብል ጥያቄ

“ እሺ ” አለች ሀዘን በወጋው ድምጿ

“ አዎ ከዛሬ ጀምሮ የዛ ቤት ሥራ ቀርቷል ”

“ እንዴት እንኖራለን እማዬ ” ደነገጠች

“ ግድ የለም እንጨት ለቅሜም ሸጬ ቢሆን ሳንበላ አናድርም ። የኔ ጥረት ይበቃል ፤ አንቺ በርትተሽ ተጠንቅቀሽ ተማሪልኝ ብቻ ። ”

“ እረ እማዬ በትርፍ ጊዜዬ ሠርቼ ልርዳሽ ፤ ደስ ካላለሽ ከዚያ ቤት ወጥቼ ሌላ ቦታ ልስራ ”

“ የለም ይቅርብኝ አይሻኝም።”

“ ትጉጃለሽ ።”

" ይኸኛው ጉዳት ይሻለኛል ፤ በቃ ሥራ የሚሉት ነገር እሺ ውድዬ "

" እሺ እማዬ "

ቀና አድርገው ዐይኖችዋን ግንባሯን ሳሚትና ፊቷን በበለሴ ኩታቸው ጫፍ ጠራርገው የሳቸውን ያነባ ዐይንና የረጠበ ፊት አባብሰው ቡናቸውን ሊቀዱ ተመለሱ ። ቡናው ስለ በረደ መልሰው እሳቱን ገጠምጠም አድርገው ጀበናውን ከጣዱ በኋላ ከወረደው ፍም ዛቅ አድርገው ዕጣን ማጨሻው ላይ ጨመሩትና እንኳሩን ነጭ ዕጣን ጣል ጣል አደረጉበት ። ለሁለተኛ ጊዜ ጐረቤቶቹ ቡና እን ዲጠጡ ውዴ ልትጠራ ወጣች ።

ከረከቦቱ ፊት ለፊት ካለው ማጫሻ ላይ ቀጥ ብሎ ወደ ላይ የሚወጣውን የዕጣን ጪስ በተመስጦ ተመለከቱት አንዳንዴ ጪሱ እየተጠማዘዘ እየተጥመለመለ ሲነሣ ምኞታቸውም ሀሳባቸውም የተሸመደመደ እየመሰላቸው ቅር ይሰኛሉ ። ድንገት ደግሞ ከደጅ ወደ ቤት ሽው በሚል ንፋስ ጪሱ ሲበተን ብስጭት ሲሉ ይታያሉ ። በዚያጪስ ውስጥ የሚታያቸው ራዕይ የራቀ የጠለቀ ይመስል የዐይኖቻቸውን ቆዳዎች ሰብሰብ አድርገው በጥንቃቄና በትኩረት የጪሱን እንቅስቃሴ ከመነሻው እስከ መድረሻው ሊከተሉ ይሞክራሉ ። ጥሩ መዓዛ የሚያውደው የዕጣን ጪስ ወሪር ባለ ቅርጽ ተነስቶ ወደ ግራ ወደ ቀኝ በመጠኑ እያዘነበለ በአየር ላይ ትርኢት እየሠራ በኋላም ሲበተን የሳቸውም ሀሳብ በምኞት ብቻ ያላንዳች መቋጠሪያ ውል ብትን ሲል ይታያቸዋል ።

ወ/ሮ ሙሉ ይህን የጪስ ትርኢት መመልከት ይወዳሉ ። እሳቸው በሳቸው ውስጥ ሠርገው ግላዊ ጉዳያቸውን የሚያፍተለትሉት በዚህ ጊዜ ነው ። ቡና አጫጪሰው

እጣን አውደው ተደላድለው ሲቀመጡ ነው ለአማልክት ፤ ለሰማዕታት ለቅዱሳን ደግሞም ለጨሌያቸው ልመናቸውን የሚያሰሙት በስለት የሚማጠኑት ። ዛሬም እንደምንጊዜውም በዝምታ ፤ በትካዜ ፤ በድካም የዕጣን ጪስ ተከትለው በሀሳብ ነጉደዋል ።

ውዴ ጐረቤቶቻቸውን ጠርታ ከመመለሷ በፊት ፤ " እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ " ብለው በሩን ገፋ አድርገውት ገቡ ። አብዬ ቅጣው ዘምቢል የተሸከመ ትንሽ ልጅ አስከትለው ነበር ።

ወ/ሮ ሙሉ ከተቀመጡበት ደንግጠው ተነስተው የሰላምታውን አጸፋ ሰጥተው ተቀበሏቸው ። የባሕር ዛፍ ቅጠል ጣል ጣል የተደረገበትን ሥጋ የያዘ ዘምቢል ከልጁ ተቀብለው ወደ ማጀት ዞር ካደረጉ በኋላ ቁራሽ ዳቦ ሰጥተው ልጁን ሸኙት ። በተፍለቀለቀ ፈገግታ ተውጠው በድንኩ አልጋ ላይ እንዲቀመጡ አብዬ ቅጣውን ደጋግመው ጋበዟቸው ።

ባለ ብረት መያዣ ጭራቸውን እንደዘበት እየነሰነሱ በፍቅር ዐይን አዩዋቸው ። ያው እንደ ልማዱ የአብዬ ቅጣው ዐይኖቻቸው ከኒያ ትላልቅ ጡቶች ላይ አረፉ ። ራመድ አሉ ወደ ወ/ሮ ሙሉ ፤

" ሳሚኝ እንጂ ሙሉ ፤ እንኳን አደረሰህ አትይኝም"

" ምነው እቴ እርስዎ ደሞ ወግ ያበዛሉ ፤ ከርመው የመጡ ፤ ካገር የወጡ ይመስል መሳም ያምርዎታል " ወ/ሮ ሙሉ ተሽኮረመሙ ፤

" አልናፈቅሽም ማለት ነዋ "

" ሥራም አላጣሁ እቴ " ውሸታቸው መሆኑ ከጠቅላላ ሁኔታቸው ይታወቅባቸዋል ።

ለስላሳና መሸብሸብ የጀመረውን ጉንጫቸውን አገላብጠው ስመው እኒያን የሚወዷቸውን ትላልቅ ጡቶች በጃቸው ዳሰስ ፤ ጨበጥ ጨበጥ ካደረጉ በኋላ አብዬ ቅጣው ከድንኩ አልጋ ላይ ከወ/ሮ ሙሉ ፊት ለፊት እንፈራጠው ተቀመጡ ።

የዕድሜ ብርካቴ ያላወላገደው ደልዳላ ቁመናቸው ከአለባበሳቸው ጋር ግርማ ሞገስ ሰጥቷቸዋል ። የቅዱስ ዮሐንስን በዓል በጸአዳ ልብስ በማክበር ላይ ያሉት አብዬ ቅጣው ፤ ነጭ መብሩቅ ተፈሪ ሱሪ ከነእጀ ጠባቡ ለብሰዋል ። ባለ ቀጭን ጥበብ ኩታ ተጐናጥፈዋል ። ጥልፍልፍ ነጠላ ጫማ ተጫምተዋል ። እንቅፋት ያበላሸው የእግራቸው ጥፍር ከማስቀየሙ በቀር ተረከዛቸው አልተሰነጣጠቀም እግራቸውም አልተንሻፈፈም ።

የወ/ሮ ሙሉ ልብ በደስታና በፍቅር በዚያች ቅጽበት ፈካ ። ጨዋታ አዋቂ ንግግር አሳማሪና ልበ ሙሉ ወንድ በመሆናቸው የወ/ሮ ሙሉ ጐረቤቶች በተለይም ሽማግሌዎቹ ወታደሮች አብዬ ቅጣውን ይወዷቸዋል ። በኮሪያ ፤ በኮንጐ በኦጋዴን ያደረጉትን ተጋድሎ ያሳለፉትን ጀግንነት ፤ በወላለቀ ጥርሳቸው መሀል ምላሳቸውን ብቅ ጥልቅ እያደረጉ በጋለ ስሜት በመጡ ቁጥር ያወሩላቸዋል ። አብዬ ቅጣውም በአምስቱ የጠላት ወረራ ዘመን ሙያ የሰሩ በሚያውቋቸው ሁሉ የተደነቁና የተከበሩ አርበኛ ስለነበሩ ፤ የፋኖነት ፤ የአርበኝነት ወግ ሲነሣ ወኔያቸው የሚፈላ በመሆኑ ፤ አተኳኮሳቸውን ፤ አሰነዛዘራቸውን አጨባበጣቸውን ፤ በሰውነታቸው እንቅስቃሴ ፤ በአነጋገራቸው ስልት እየደገፉ ሲያወጉ የጥንቱ የጥዋቱ ሁሉ የዛሬን እየመሰላቸው ሽማግሎቹም አብዬ ቅጣውም ይቅበጠበጣሉ ። ይቁነጠነጣሉ ።

ውዷ ቡና ጠርታ ስትመለስ ፤ ፍንትው ያለ የዓመት በዓል ሽማ ለብሰው በደርባባውና በጐርናናው ድምጻቸው ቤቱን ያደመቁት አብዬ ቅጣው ጠላቸውን ሲጐነጩ ደረሰች ። የውዷ ሰው አቀራረብ የእናቷን ግንባርና አቀባበል የተከተለ በመሆኑ ለአብዬ ቅጣው ያላት አክብሮት እና የምታሳያቸው ትህትና ለሌሎች ከምታደርገው ሁሉ የተለየ ነው ። አብዬ ቅጣው ከወ/ሮ ሙሉ ጋር ከተዋወቁ በኋላ እየሰነባበቱ መለስ ቀለስ ማለት ባዘወተሩበት ሰሞን አደፋፍረውና ተያዥ ሆነው ውዷን ውብሸት እንዳይላሉ ቤት በጽዳት ሥራ እንድትቀጠር አድርገዋል ። በመጡም ቁጥር ለደብተር ለእርሳስ መግዣ ይሁንሽ እያሉ እጃቸውን ይዘረጉላታል ። ዛሬም እንዳስለመዷት በወረቀት የተጠቀለለ ትንሽ ነገር ይዘውላት መጥተዋል ።

ቡና የተጠሩት ጐረቤቶች ተከታትለው ከገቡ በኋላ ለሁሉም ጠላ ተቀድቶ ሲቀርብ ፤አብዬ ቅጣው ጃዊ ጨርቅ ለብሶ ተሸፍኖ የነበረውን ዳቦ እንዲቆርሱት ከቢላዎ ጋር ቀረበላቸው ። መቼውንም ወ/ሮ ሙሉ አብዬ ቅጣው ባሉበት ሰዓት የሚሠሩት ድንግርግር ይላቸዋል ። ያለ ምክንያት ከወዲያ ወዲህ ያንጐራድዳቸዋል ። የያዙትን ያስቀመጡትን ይረሱታል ። ዛሬም ታዲያ የደንቡን የቡራኬ ጸሎትና የመልካም ምኞት መነባንብ አነብንበው ዳቦውን ባርከው ሳይጨርሱ ወ/ሮ ሙሉ ጐንበስ ቀና ሲሉ የአብዬ ቅጣውን የብርጭቆ ጠላ ይደፉባቸዋል ። ይህን ያዩ ጐረቤቶቻቸው ሲቀልዱባቸው ወ/ሮ ሙሉ ሲያፍሩ ፤ አብዬ ቅጣው ግን የጣሉት የፍቅር መልህቅ በወ/ሮ ሙሉ ልብ ውስጥ ጠንካራ መሠረት መጨበጡን አረጋግጠው መንፈሳዊ ኩራት ቢጤ ወረራቸው ።

አብዬ ቅጣው በዋሉበት ውለው ቢያድሩ የሚያስደስታቸው ሽማግሎቹ ወታደሮች ፤ የትዝታንና የነበርን

ወግ ማድመጥ የማይሰለቻቸው ባልቴቶች ቡናው ካከ
ተመ በኋላ እንኳ ጨዋታቸው ደርቶ ተደላድለው ተቀ
መጡ ። ወ/ሮ ሙሉ ግን በልባቸው የጐረቤቶቻቸውን
መሄድ አጥብቀው ተመኙ ። አብዩ ቅጣው አሽክመውት
ካመጡት የቅርጫ ሥጋ መሀል ጮማ ጮማውን ቅልቅ
ሉንም መርጠው ጐረድ ፤ ጐረድ ፤ አድርገው በሚጥሚጣ
አርምደው ፤ ከዶሮው ወጥ ፈትፈት አድርገው ሊያጐርሷ
ቸው ሻቅለው ነበር ። ከዚያ ባሻገር ሰነባብተው ተነፋፍ
ቀው ብቅ ያሉትን ወዳጃቸውን ልዩ ልዩ ጉዳይ ሊያ
ጫዋውቷቸው ፈልገው ነበር ። በተለይም ስለ ውጼ ሥራ
ማቋረጥ ማወያየቱን ሊነግሯቸው አስበው ነበር ።

በችግርና በጭንቀት በተወጠረው ኑሮአቸው ውስጥ
ወ/ሮ ሙሉ እንደ ድንገት አብዩ ቅጣውን ማወቃቸ
ውና ማቅረባቸው ጥቂት እፎይታ ፤ ጥቂት ተስፋ ፤
ጥቂት አለኝታ ሆኖላቸው ሀሳባቸውን ስለሚያካፍሏቸው
በምክራቸውም ስለሚበረቱና ስለሚጽናኑ በእውቂያቸው
ይደሰታሉ አምላካቸውንም ያመሰግናሉ ። አብዩ ቅጣውን
እየወደዱ ያከብሯቸዋል ። ግንኙነታቸው በመተዛዘን ፤
በመተሳሰብና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ስለሆነ መን
ፈሳቸው እረፍትና ሰላም የሚላበሰው ናፍቆዋቸው እሳ
ቸውን ባሰላሰሉበት ሰዓት ብቻ ነው ።

ወ/ሮ ሙሉ ከወለሉ ላይ ከተበተነው ቄማ እየመዘዙ
ልብ ሳይሉት እየነከሱና እየቀነጠሱ ከአብዩ ቅጣው ጋር
በሚኖራቸው የብቻ ጊዜ የሚያቀርቡትን መሰናዶና የሚያ
ደርጉላቸውን መስተንግዶ ሲያሰላስሉ ፤ ካሁን አሁን
ጐረቤቶቻቸው ተነስተው ሊወጡ ነው በማለት ዐይና
ቸው እንቅስቃሴያቸውን ሲከታተል ፡ አፈፍ ብለው ተነ
ስተው ኩታቸውን ማስተካከል ጀመሩ ። ቢለመኑም ቢጐ

ተቱም ሀሳባቸው ቁርጥ ያለ ነውና አብዩ ቅጣው ወደ መን
ደራቸው ሊሄዱ ተሰነባብተው ወጡ ።

ወ/ሮ ሙሉም ፊታቸው ቅጭም ቅይር ብሎ በለሴ
ኩታቸውን ከትከሻቸው ላይ እያመቻቹ ሊሸኙዋቸው
ሲወጡ ደጁ ጭልምልም ብሏል ። ችምችም ካለው የሰን
ሰል አጥር ሥር ሲደርሱ ቆም ብለው የግራ እጃቸውን ጨብ
ጠው ያዟቸው ። ወ/ሮ ሙሉም እንደ መንጠቅ እየቃጣ
ቸው ፤

"እርስዎ ደሞ ዘወትር ጥድፊያ ይወዳሉ ፤ ወይ ቀደም
ብለው ቢመጡ በጄ ምን ይሉታል ይኼን አመጣጥ"

ኩርፊያም ቅሬታም የቀላቀለ የተነጫነጨ ንግግር፡
ነበር ።

" ዐይንሽን ካየሁት ከመብል ኮመጠጥ ይበልጥብኛል
አንቺን አይቼ ጠገብሁ መቼ አነሰኝ "

" የሰው ቀልብ መግፈፍ ይወዳሉ እቴ "

" ይልቅ ነይ ልንገርሽ " ወደ ሳቸው ጐተት አደረ
ጓቸው ።

" ኤድያ . . . ሳሚኝ እንዳይሉኝ " እጃቸውን ሊያ
ስለቅቁ ሞከሩ ፤

አብዩ ቅጣው በጠንካራ አጨባበጣቸው ስበው ወ/ሮ
ሙሉን እጅግ ካቀረቡ በኋላ ከኪሳቸው ያወጧትን ትንሽ
ቢልቃጥ በጡቶቻቸው መካከል አደላድለው አስቀመጧት
ወዲያውም እኒያን ሞንዳላ ትላልቅ ጡቶች ደሰስ ዳሰስ
ካደረጉ በኋላ ጐንበስ ብለው ሳሟቸው ። የአብዩ ቅጣው
ከንፈሮች በወ/ሮ ሙሉ ጡት ጫፍ ላይ አለፍ ሲሉ የአካል
ንዝረት ተፈጠረና ሳያስቡት ወ/ሮ ሙሉ ተወራጭተው

ገኙቻቸው ። ሳቅ ያልተለየው ቁጣ እየተቆጡ ደረታቸውን በነጠላቸው እየሸፋፈኑ ሁኔታውን ሳይጠሉት አጥላሉት ። ጊዜ ወስነው ፡ ቀጠሮ አድርገው ተሰነባብተው ሲለያዩ፡ አብዬ ቅጣው በፍቅር ግለት ነጠቅ ነጠቅ እያሉ ፈጥነው ሲራመዱ ወ/ሮ ሙሉ ደግሞ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ልባቸው በደስታ ሞቆ አካላቸው በነጸብራቁ ፈክቷል ።

ከወ/ሮ ሙሉ ጋር የተዋወቁበትን ዕለቱን ቦታውንና ሁኔታውን በትውስታቸው ውስጥ እያዩ አብዬ ቅጣው ወደ መኖሪያ ሰፈራቸው ገሰገሱ ። የአገናኛቸውን አጋጣሚ እየሳቁ አሰላሰሉት ።

ወ/ሮ ሙሉ ከመርካቶ ጌሾውን ብቅሉን ሽንኩርቱን ወይራውን ሌላ ሌላም ኮተቱ በዘንቢል ሞልተው ከሸመታ መልስ ወደ ሠፈራቸው ከሚያደርስ ታክሲ ውስጥ ገብተው ጥግ ይዘው ይቀመጣሉ ። አብዬ ቅጣውም ሁለተኛ ደራሽ ይሆኑና መሀል ይቀመጣሉ ። ወፈርና ረዘም ያሉ ሶስተኛ ሰው ገብተው የታክሲዋ በር ሲዘጋ ተጣበው አካል ለአካል እጅግ ይቀራረባሉ ። ከመጀመሪያውም የአብዬ ቅጣው ቀልብ ደንግጠባቸው ስለ ነበረ በጥበቱ ምክንያት ወ/ሮ ሙሉን መታከኩንና መደገፉን ወደውታል ። መኪናዋ ጠመዝማዛውን መንገድ እየተጠማዘዘች ስትበር ዘም በል ቀና እያሉ የወ/ሮ ሙሉን ትላልቅ ጡት እየነካኩት አብዬ ቅጣው ጨዋታ ይጀምራሉ ፤

" ቢንተራሱት ሕመም ያስለቅቃል እሜትዬ " ይሏቸዋል የወ/ሮ ሙሉን ጡቶች ክፉኛ እየተመለከቷዋቸው፤

ወ/ሮ ሙሉም ዘንቢላቸውን የሚያስተካክሉ መስለው ጉንበስ እንደማለት ብለው

" በሽተኛን ከመድኃኒቱ አያገናኘውም እንጂ ጌታዬ" ይሏቸዋል ። በዚሁ ይሳሳቁና ንግግሩ በአንደበት መሆኑ

ቀርቶ በመንፈስ በየውስጣቸው ሆኖ መኪናዋ ሽቅብ ወደ ጊዮርጊስ እየበረረች ግራና ቀኝ በመንገዱ ዳር ያለውን ሁሉ እያዩ ወደ መድረሻቸው ይፈጥናሉ ። አብዬ ቅጣው ግን ወዲያው የወሰኑት ጉዳይ ነበር ። እሳቸው ካሰቡበት ሳይሆን ወ/ሮ ሙሉ ከሚወርዱበት ሲወርዱ ። አፍንጮ በር አፋፍ ላይ ታክሲዋን አስቁመው ዘንቢላቸውን ጐትተው ወ/ሮ ሙሉ ሲወርዱ አብዬ ቅጣውም ዱብ አሉ ።

ይህ አጋጣሚ ነበር ለወ/ሮ ሙሉና ለአብዬ ቅጣው ግንኙነትና ዝምድና መሠረቱ ። አብዬ ቅጣው አስጨናቂም አቅማቸውና ፍቅራቸው በፈቀደው መጠን በወ/ሮ ሙሉ ችግርና ጭንቀት በመካፈል በሀሳብ በምክር በስጦታም ተካፍለዋል ። አብዬ ቅጣው አስጨናቂን ወትሮ ወንዶች በተፈተኑበት ሜዳ ከዚያም ወዲህ በኖሩበት አካባቢ የማያውቃቸው የማያከብራቸው የለም ። እንዲያውም 'አሉ አብዬ ቅጣው ' እየተባለ የሚወሱበት ልዩ ልዩ የአነጋገር ፈሊጥ አላቸው ።

የሁኔታን ሂደት ፣ አስተውለው ጅምሩን መዝነው ፣ ውጤቱን ገምተው ፣ የሚያመረቃ ካልመሰላቸው ከወዲሁ ለማረቅ ከወዲሁ ለማስተካከል ሲሉ የሚወረውሩት ብሂልና ብዙ ሰዎችም የሚያስተጋቡላቸው አባባል " ሠርዶን ሥር ሳይሰድ " የሚሉት ማስጠንቀቂያ ነው ። አረጋዊው አብዬ ቅጣው ራስን በመቻልና በሥራ ክቡርነት ስለሚያምኑ በገረጀፈው የእድሜ ዘመናቸው እንኳ የተሰማሩበት ሥራ ነበራቸው ። በልመናና በምጽዋት በረከት ህሊናቸውን ሊያጐድፉት ክብራቸውን ሊያወርዱት አይፈልጉም ።

እልፍ የመኪና ኮቴ ሲረግጠው ፣ እያል የሰው ዓይነት ሲመላለስበት ፣ ሁካታና ግርግር እንደደራበት በሚውለው አውራ መንገድ በምሽት የአንድ መደብር ዘበኛ ሆነው

ይሠሩ ነበር ። ጀምበር ስታቆለቁል ጊዜው እየመሸሸ ሲሄድ ዝምታው እየጠና ሲያድብ የሌቱም እኩሌታ ሲዳረስ ያኔ እንደቤትም ፣ እንደ አልጋም ፣ እንደሬሣ ሣጥንም መሆን የሚቃጣት የአብዬ ቅጣው የሌሊት መጠለያቸውና እሳቸው በመደብሩ ፊት ተሰይመው ይታያሉ ። ታዲያ ማታ ማታ በመንገዱም በአካባቢውም ፍጹም ጸጥታ ከቅዝቃዜ ጋር ይጋገርበታል ።

የፒያሣው የሌት ዘበኛ ቅጣው አስጨናቂ ረዥም ቁመናቸውን በሚመረኰዙበት ባለ ጀንፎ ከዘራ ላይ እየደገፉ ረጋ ባለው እርምጃቸው በመደብሩ ፊት ለፊት ከወዲያ ወዲህ መንጐራደድ ይወዳሉ ። በኮታቸው ላይ አዳፋ ጋቢ፣ በዚያ ላይ ረጅም የነተበ ካፖርት ደርበው በካፖርቱም ላይ አብሯቸው ያረጀውን የሳሳ አረንጓዴ ብርድ ልብስ አጣፍተው አለቅጥ አብጠው በሚንጐራደዱበት ሌሊት ሁሉ ወዲያ ወዲህ መንጐማለላቸው ሌባ ለማስደንበር እንቅልፍ ለማባረር ብቻ ሳይሆን ከነፍሳቸው ጋር ለሚያደርጉት ጨዋታ የሚመርጡት ሁኔታም በመሆኑ ነበር ።

ውርጭ በሚወረዛበት በረጋው ሌሊት ያለ እረፍት የሚንቀሳቀሱት አብዬ ቅጣው ያሳለፉትን ወቅትና ሁኔታ ባሳብ እየተማሩ ሲያዝኑ ሲተክዙ ፤ ሲሸነጡ ማንጋት ልምዳቸው ነው ።

የተዘጋ በር ከፍቶ ፣ የሞቀ መኝታ ገልጠ እንቅልፍ የሚያሸሸው ትዝታ ፣ ብርድና ዝምታ በነገሰበት ሌሊት አብዬ ቅጣውንም ሲያጨዋውታቸው ያመሻል ። አንዳንዴ የወኔያቸው ሙላት ፣ የልባቸው ኩራት የናረበትን የፋኖነት ዕድሜ እያነሳሱ ፣ ሊገሉ ሊማርኩ የፋሽስትን ትጥቅ ሊዘርፉ ቁልቁለቱን ሲወርዱት፣ አቀበቱን ሲሽቀነጠሩት ፣ በዱር በገደሉ ሲሸምቁ ፣ ለነጻነታቸውና ለአገራቸው ለወገናቸው ሲሉ ያሳለፉትን ጊዜና የኋላ ኋላ ወሮታቸው በሶስት ትርጉም የለሽ ሜዳሊያቸው ተገምቶ እንደ አሮጌ እንቅብ ወደ ዳር መገፋታቸውን እያሰላሰሉት ፣ በስተርጅና በዚያ መሰሉ ሥራና ማብቂያ ላይ መገኘታቸውን እየተቆጩበት ፤

“ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ ” በሚል ግለታምስሜት እንደ አራስ ነብር ሲንቆራጠጡ ይነጋላቸዋል ። አገርና ወገን ያቆሰሉ ባንዳዎች አዲስ የብልጠት ልባስ ተሸፋፍነው የውስጥ አርበኞች በመባል ከሥልጣኑ ቁንጮ ተቀምጠው የችግሩን ገፈት ሳይሆን የጥቅሙን እፍታ ሲያጣጥሙ ነጻነት ያስመለሱ ለወገን ሲሉ የተሰነከሉ እውነተኞቹን ድሆች ሲያዩ ዓይናቸው ደም የሚለብስ መኳንንትና መሣፍንትን ሲያዩ ገለህ ሙት የሚላቸው ወኔ ብዙ ቀን ይተናነቃቸው ነበር ። ሥራቸውንም ስለሚያውቁ ታሪክም ስለማይፋቅ እንደ ልባቸው በጀግኖች መሀል መራመድ በሰዎች መካከል መመስከር የማይችሉ፣ በክብርና በሰቀቀን የሚኖሩትን የንጉሡን ደጋፊዎች አገዛዙን አወዳሾች ሲያዩዋቸውም ሲያስቧቸውም በጥላቻ ነው ።

አብዬ ቅጣው ፉጨት ያምርላቸዋል ። ማንጐራጐር ይወዳሉ ። ያንጐራጐሩ እንደሆን የዘወትር ስንኞቻቸው ጀግኖችን የሚያወድስ ነበር ።

እንደ ካሣ አባ ታጠቅ
ታሪኩ ነው የጀግና ሰው የሚወሳ የሚደነቅ ፤
እንደ እምዬ አባ ዳኘው
የወገን ፍቅር ተጐናጥፎ በአበሻ ልብ የሚገኘው ፣
የሠራ ነው ግዙፍ ጉዳይ የሚዳሰስ የሚወረስ፣
ሀውልት ሆኖ ዝክረ ታሪክ ለተምሳሌት የሚጠቀስ ።
ማለት ይወዳሉ ።

በብሔራዊ ጉዳይም ሆነ በግል ትዝታቸው ሲወዘወዙ አምሽተው ሲነጋጋ ጉህ ሲቀድ ቅዝቃዜ አዝሎ የረጋው አየር ሲንቀሳቀስ ፡ የክፍለ ሀገር መንገደኛ ኰተቱን ተሸክሞ ውር ውር ማለት ሲጀምር ፡ ለማኙም ውሻውም ሲያዛጋ ፡ አብዬ ቅጣውም ያችን ቃሬዛ መሰል ቤት ጐትተው ከመደበሩ በስተጓሮ አሳርፈው ለእረፍት ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ ።

የመንገድ ዳር ዘበኝነቱን ትተው የውብሸት እንዳይላሉ ግቢ ዘበኛ ከሆኑ በኋላ መጠለያውም ክፍያውም የአጠባበቁም ሁኔታ የተሻለ ስለነበር የሳልና የቁርጥማት በሽታቸው የሚዳስሳቸው አልፎ አልፎ ነበር ።

የአስራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተና ወድቃ ለአራት ዓመታት ያለ ሥራ እቤት የዋለች መልከ መልካም ልጅ ነበረቻቸው ። አብዬ ቅጣው በውብሸት እንዳይላሉ ቤት በዘበኝነት ሲውሉ የሳቸውን ምሳ አቀብላ ከመሰል ጓደኞቿ ጋር ሥራ ፍለጋ ስትባዝን ውላ መመለሷ በዚህም መከሳት መንገላታትዋ እያሳዘናቸው እያንገበገባቸው ችግራቸውን በለሆሳስ ለውብሸት እንዳይላሉ አዋይተውት እሱም በጓደኛው በኩል የጽዳት ሥራ እንድትቀጠር አድርጎ ረድቷቸዋል ። አሥራ ሁለት ዓመታት ተምራ በተላላኪነት ሥራ በመቀጠሯ ልባቸው እየተወጋ ማዘናቸውን በድብቅ ይዘው በተገኘው ሥራ እንድትተጋ ይመክሯታል ። የተማረ ሥራ በማጣቱም ግርም ይላቸዋል ። በዚሁ ሥራዋ ለስድስት ወራት ቆይታ በመ/ቤቱ የውስጥ ውድድር ተካፍላ በእድገት የሂሣብ ሠራተኛ ትሆናለች ። ይህን የምሥራች ይዛ የመጣች እለት ያቀረበችላቸው ልመናም ነበር ። በውርጭና በብርድ እየተገረፉ የሚያመሹበትን ሥራ እንዲተውና በግቢያቸው ውስጥ የሚወዱትን ንብ

እርባታ አትክልት ማለምለም ሥራ እንዲጀምሩ በሞቱት እናቷ ስም ተማጥና እሺ አሰኝታቸዋለች ።

በዕለተ እንቁጣጣሽ ልጃቸው ለበረከት የገዛችላቸውን ጸአዳ የበዓል ልብስ ለብሰው ከሰዓት በኋላ ወደ ወ/ሮ ሙሉ ቤት አካሄዳቸው ይህንኑ የምሥራች ሊነግሯቸውና የዘበኝነቱንም ሥራ ሊተውት ማቀዳቸውን ለማጫወት ነበር ። የወ/ሮ ሙሉ ጐረቤቶች ያንኑ የጦር ሜዳ ሙያ የሚያወሳ ጨዋታ ጀምረው ትዝታውና ሳቁ በሞቅታ ደርቶ ፤ ጊዜውም መሽቶ አብዬ ቅጣው ያሰቡትን የመጡበትን ለወ/ሮ ሙሉ ሳይነግሯቸው ተመለሱ ። ሆኖም የቅርብ ቀጠሮ በማድረጋቸው በሁኔታው አልተከፉም ።

ጠረናቸውን አሽትቶ መድረሳቸውን አውቆ የተቀበጠበጠውን የውሻቸውን የመቻልን ድምጽ አብዬ ቅጣው ከርቀት ሰሙት ። ያረጀውን እንጨት ሊለውጡለት ሊያጠብቁት ያሰቡትን አሮጌ አጥራቸውን አልፈው ውሻቸውን ሊፈቱ ራመድ ሲሉ ፤ አጥራቸው በር ፊት ለፊት መኪና መጥቶ ድቅን ብሎ ሲቆምና ልጃቸው ስትወርድ ያያሉ ። ከትያትርና ዘፈን ቦታ መመለሷ ነበር ።

አመሻሽቶ መምጣትዋን ፤ ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር መላልሰው ማየታቸውን አልወደዱትም ነበርና የልጃቸው ሁኔታ ከነከናቸው ። እስክትቀርባቸው ቆመው ጠበቋት ። ገና ከአስተያየታቸው ስሜታቸውን መዝና በተፍለቀለቀ ፈገግታ ዐይን ዐይናቸውን እያየች እጃቸውን ጐትታ ይዛቸው ወደ ቤት ገባች ። መቻል ተቅበጥብጦ ቢጮኽም የሰማው አላገኘም ።

ልጃቸው ፈገግ ባለች ቁጥር የአብዬ ቅጣው ልብ ስንጥቅ ይላል ። ከናፍርዋን ሣቅ ሲገልጠው ችምችም

ያሉት ትናንሽ ጥርሶቿን ግራና ቀኝ ስርጉድ ከሚሉት ጉንጮቿ መካከል ሲያዩት ጤና አይሰጣቸውም ። የልጃቸው ሣቅና ፈገግታ የብቸኝነታቸውን ምድረ በዳ ስፋትና ክፋት የሚነግራቸው እየሆነ ያስቸግራቸዋል ። በአካል እናቷን መስላ በመወለዷ አብዬ ቅጣው በጉርምስናቸው ዘመን ደም የተቃቡበትን የሟች የሚስታቸውን ውበትና ለዛ ያስታውሱባታል ። እሷ ከሣቀች ሣቅዋ ፈገግታዋ ገፍቶ ከሀሳብ ከትዝታ ይዘፍቃቸዋልና ቁጣቸው በቀላሉ ይገሰሳል ። ሆነና ተገሰሰ ።

ምዕራፍ ሦስት

የመጨረሻው የጥሪ ደወል ኖሮ መነጋ፣ሪያውን ሲያነሳ ከወዲያኛው ጫፍ ዝምታ ሆኗል ። በውድቅት የሚደውል ማነው ፤ ለምንስ ይሆን የሚለውን የጥያቄ ሀሳብ ገና ከመንከሱ በሩን ገፍትረውት ገቡ ።

ለወጉ ያህል ጋቢ አጣፍተዋል ። አብዛኛው ደረታቸው ተጋልጦ ይታያል ። የጡት መያዣ ያላሻቸው እጅግም የልጅ ከንፈር ያልመጠጣቸው ጡቶቻቸው አዘንብለዋል ። ክታብና የብር መስቀል ፤ የጆሮ ኩክ ማውጫና መርፌ ቁልፍ ሰብስቦ የተሸከመው ወፍራም ጥቁር ማተብ በብር ድሪ ተሸርቦ ቁልቁል በጡቶቻቸው መሀል ወርዷል አመጣጣቸው በቁጣ ግፊት ነበርና መኩሪያ ከተኛበት ቀና ብሎ

“ ምነው እማዬ” አላቸው ሁኔታቸው እያስፈራራው፤

“ ምነው ይኸን ስልክ ቁጥሩን ለከተማው ሴቶች ሁሉ እየሰጠህ ቀን ተሌት ባታስጮህብኝ ፤ ደሞስ ይኼን ያህል ሲያንቃጭል ምነው ብታነሳው ፤

“ ከአንዳንድ ጓደኞቼ በቀር የስልክ ቁጥሩን የሚያውቅ የለም ዛሬ ደግሞ በጣም ደክሞኝ ስለ ተኛሁ ቶሎ አልሰማሁትም ሳነሳውም ድምጽ አልነበረም ።”
አላቸው እየሳቀ በትህትና ።

“ ይኸው ሁለት ቀን ሙሉ ለብርቱ ጉዳይ እፈልገዋለሁ የምትል ሴት ስታደርቀን ነበር ። ማነች እሷ ካንተስ ምን ጉዳይ አላት ”

“ ማነኝ አለችሽ ”

“ ሥራ አጥቼ የሷን ስም ሳስታውስ ፣ ሳሰላስል ፤ እኔማ ቢብስብኝ ሁለተኛ እንዳትደውል አስጠነቀቅኳት”

“ ልክ አይደለሽም እማዬ የምፈለገው ለልዩ ልዩ ጉዳይ ሊሆን ይችላል መልእክት ተቀብለሽ የደዋዩን ማንነት ጠይቀሽ ብታቆይኝ ሊጠቅመኝ ይችል ይሆናል ይልቅ አሳሰብሽኝ ማነኝ አለች ደዋይዋ እስቲ ለማስታወስ ሞክሪ”

“ የዛሬ ሴት ይሉኝታውን ሸጦ የበላ ነው ለራሷ ጉዳይ ፈልጋህ ይሆናል እንጂ ላንተ ጉዳይ ከሆነ መ/ ቤትህ ድረስ ይመጣልህ የለ ፤ አታስብ ልጄ ለየትኛው ቤትህ ለየትኛው ልጅህ ትጨነቃለህ፤ በል ስልኩን ወዲህ አምጣ ላስቀምጠው ” ስልኩን አንጠልጥለው የመኝታ ክፍሉን በር ዘግተውለት ወጡ ።

የመኩሪያ እናት ወ/ሮ ፋኖሴ በትንሹም በትልቁም ነገር አሳበውና አስታከው የሚነግሩት ብስጭታቸውና ብሶታቸው ያረፈበትን የአኗኗሩን ሁኔታ ጥላቻ ነበርና ቤትና ልጅ እንደሌለውና ሊያስብ ሊጨነቅ እንደማይገባው በአሽሙር ነግረውት መውጣታቸው አናዶት ቶጭኖት የነበረው እንቅልፍ ሸሸውና ቁልጭ አለ ።

ከምንም ነገር አብልጦ እናቱን የሚወድ በመሆኑ ከሳቸው ጋር መኖሩ ለሱ የሚሰጠውን ደስታ ያህል ለምን እሳቸው እንደማይደሰቱበት ዘወትር ግርም ይለዋል ። እንደሚወዱትና እንደሚጨነቁለት ደግሞ ያውቃል ሆኖም ቤት ይዞ ሌላ ሕይወት መስርቶ ከአጠገባቸው መሄዱን

አጥብቀው መፈለጋቸው እያሳሰበው መጥቷል ። ወ/ሮ ፋኖሴ መኩሪያ ተወልዶ እስኪጎለምስ፤ ማደጉ መማሩ ፈተና ማለፉ ሥራ መቀጠሩ ውሎ መግባቱ በሳቸው ጸሎትና ስለት መሆኑን አምነው የሚዘክሩት በዓል ብዙ ነው።

ከወለዷቸው ሶስት ልጆች መካከል የተረፉቸው እሱ ብቻ በመሆኑ ፤ ይሰስቱታል ። ሁለተኛ ደረጃን እስኪጨርስ ድረስ በቤትም በአካባቢም በቤተ ዘመድም አንቺ እየተባለ ይጠራ ነበር ። ማንን ለማታለል ከማን ለማሸሽ እንደሆነ ባይታወቅም መኩሪያ በጾታው የሚገባውን መጠሪያ ተነፍጎ “ አንቺ” መባሉን ከአስራ አንደኛ ክፍል የትምህርት ዘመኑ በኋላ አልተቀበለውም ። ትናንሾቹን የመንደር ልጆች እየደበደበ እናቱን ጎረቤቶቹንና ቤተ ዘመዶቹን ጥሪያቸውን ባለመቀበል ፤ ሴት እንዳልሆነ አምርሮ እያስረዳም የግድ በወንዴ ጾታ አጠራር እንዲጠራ አድርጓል ።

የወ/ሮ ፋኖሴ ጸሎት ያልሰመረበት አንድ ምክንያት የመኩሪያ ግድ የለሽነት ሆኖ እየታያቸው በወጣ በገባ ቁጥር በፊት ለፊት ጭቅጭቅ ነገር በነገር እያጣለፉ ወንደላጤነቱን ይኮንኑበታል ። መኩሪያ ለውጭ ትምህርት ተለይቶአቸው በኖረበት የስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ፤ በማኅበርተኞቻቸው መካከል ፤ካሉበት ሰፈርም ራሳቸውን የቻሉና የተከበሩ የተባሉትን ሰዎች ሁሉ እየመረመሩና እያስመረመሩ ለልጃቸው ሚስት የምትሆን ሴት ሲያፈላልጉ መቆየታቸውንና እንደመጣም የመረጡለትን ቤተሰብ በውጉ በደንቡ ለማስጠየቅ መዘጋጀታቸውን ነግረውት ይህን ሀሳባቸውን ውድቅ ካደረገው ወዲህ ተነጫንጨዋል ። አኩርፈውታል ።

በተደጋጋሚ የደወለችው ሴት ማን ትሆን ? ደጋግማ የደወለችውስ ለምን ይሆን ? እያለ ከርዳዳ ጸጉሩን እየመ

CamScanner

ዘዘና እያፍተለተለ በተለያየ አቅጣጫ ሲያስብ ድንገት የግንባሩን ጠባሳ ነካውና ስሬ የትዝታ በር ከፈተ ። ጠባሳው ከአካሉ ላይ ብቻ ሳይሆን በህሊናውም ውስጥ የቀረጸው ጉዳይ ተንቀሳቀሰ ። ወለል ብሎ ታየው ። የያኔውን አድራጎቱን በየዋኅነት ገመተው ። ሆኖም ተገቢ ነው ብሎ እንደገና አመነበት ። ለወለዷት ልጁ የመድኃኒት መግዣ እርዳታ የተጠየቀው ጓደኛው የመድኃኒት ማዘዣው ወረቀት እንደ ጠፋበት በነገረው ጊዜ ጭካኔውን ተንኮሉን በመቃወም በተፈጠረው የሀሳብ አለመግባባት ሲደባደቡ የደረሰበት ፍንክትና ጠባሳ ነበር።ልጅዋን ከነችግሯ ይዛ የቀረችው ሴት በምን ሁኔታ ትገኝ ይሆን የሚለው ሀሳብ የተለያዩ ግምቶችን አስጣለው ። በወቅቱ የአቅሙን እርዳታ አድርጎላት ሕጻኒቱን ይዛ ከተመለሰች ወዲህ ሴቲቱንም ሆነ ጓደኛውን አይቶም ተገናኝቶም አያውቅም ነበርና የሁኔታው ሂደትና ውጤት አጓጓው ። የት ይሆኑ ? እንዴት ይሆኑ የሚለው ጥያቄ ተመላለሰበት ። ወዲያው ስልክ ሲያንቃጭል መንፈሱን ወደዚያው አሰባስቦ ለመነሳት ተዘጋጀ ። ከአሁን አሁን ይጠሩኛል ብሎ ቢጠብቅ እናቱ እየተነጋገሩ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ ። አላስችል አለውና ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍሉ ሲሄድ ንግግራቸው ጭቅጭቅ ሆኖ አገኘው ። በዚያ ምሽት መደወሉን በመቃወም መኩሪያን ከመኝታው ሊቀሰቅሱት እንደማይችሉና እንደማይፈቅዱ ሲናገሩ ሰማ ። የሚያነጋግራቸው ወንድ በመሆኑ እንጂ የመኩሪያን መምጣት ሲያዩ ዝጊው ዝጊው ብሏቸው ነበር ። መነጋገሪያውን ሰጡት ።

“ ሀሎ አቤት ” አለ በጐርናና ድምጹ ያነጋገረው ሰው ማንነቱን ሳይገልጽ የሚፈልገው ሌላ ሰው መሆኑን ነግሮት አሳልፎ ከሌላ ተናጋሪ ጋር አገናኘው ። በጭንቀትም በመሸበርም የሚንቀጠቀጥ የሴት ድምጽ ነበር ።

አዎ “ እሺ” በሚሉ አጫጭር ቃላት የተናጋሪዋን ማንነት ሳይረዳ ፤ መልእክቱን በትክክል እስኪያውቅ ቆየ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ እናቱ በቁጣ አፍጠው ይመለከቱት ነበር። ፊቱ ፈገግ ሲልና እሺታውን ሲደጋግም ቀጠሮም ሲቀበል እናቱ ወ/ሮ ፋኖሴ ደግሞ ፊታቸው እየጠቆረ ለነገር ይሰናዱ ነበር ። በመጨረሻው “ እሺ ። እመጣለሁ ምንም ችግር የለበትም” በሚል ማጠቃለያ ንግግሩን ጨረሰ ። እናቱን መለስ ብሎ ሲያያቸው ገላመጡት ። ሌላ የመናገሪያ እድል ሳይሰጣቸው ጉንጫቸውን ስሞ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ ። ለሱ ያላቸውን የማይበርድ ፍቅር ፤ እንክብካቤ ፤ ቸር ሀሳብና ርህራኄ እያደነቀ በሴትነት ተፈጥሮና በእናትነት ድርሻ ያለውን የጠነከረ ግንኙነት መዘነው ።

ወ/ሮ ሙሉ ሳጥን ከፍተው ቦርሳ እየበረበሩ ወረቀት እያገላበጡ ለውዴ ታማ በተኛችበት እያሳዩ ካጠራቀሙት ልዩ ልዩ የስልክ ቁጥሮች መካከል ተሞክሮ መልሶ የተገኘበት የመኩሪያ ስምና በአቅጣጫው የተጻፈበት ቁጥር ነበርና ቀጠሮ ተቀብለው መኩሪያን አነጋግረው ሲዘጉ የስልኩን ባለቤቶች ጐረቤቶቻቸውን ከልብ አመስግነው ተመልሰዋል ። ልጃቸው ውዴ 12ኛን ከተፈነተች በኋላ በመታመምዋ ከምንጊዜውም የከፋ ጭንቀት ወድቀባቸው ነበር ።

መኩሪያም ትራሱን አመቻችቶ በቁመቱ ሙሉ በጀርባው ተዘርግቶ በመተኛት ቀደም ሲል የወጠነው ብዙ ዘመን ወደ ኋላ የቀረው የጓደኛውን ጉዳይና አሁን በዚህ በምሽቱ የደረሰው አዲስ ጥሪ እያስደነቀው ሀሳብ ያደራጀመር ። ሰዓቱ ረዘመበት ። አሁንም አሁንም ሰዓቱን ቢያይ ሆን ብሎ የሚንቀረፈፍ መሰለው ሌሊቱ አልተገፋም ። ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ ጣለውና በከባዱ እያንኮራፋ አካሉን አሳረፈው ።

እለቱ ሰንበት ስለሆነ ወ/ሮ ፋኖሴ ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በማለዳው ሄደዋል ። የግቢው የቆርቆሮ በር መቀርቀሪያው ተንስቶ እንዲሁ ተዘግቷል ። የወ/ሮ ፋኖ ሴን ጠባብ ግቢ ደፍሮ የሚገባ ሰው ከፈረደበት ተንክሶና ደምቶ ካልሆነም በውሻቸው ጩኸት ቀልቡ ተገፎ ይመ ለሳል ። ትንሿ ሚሚ በዚያ ማለዳ በጅዋ እንዳትጥይ ተብላ የተሰጣትን ወረቀት እንደጨበጠች በሩን ገፋ አድርጋ ሰተት ብላ ስትገባ ያ ክፉ ውሻ ቀና ብሎ አይቷት ተመልሶ አሸልቧል ። ሚሚ የሳሎኑን በር ያለ ማቋረጥ እያንኳኳች በዓይኖቿ ግቢው ውስጥ ያሉትን ቢልቃጦችና ትናንሽ ቆርቆሮዎች ቆርኪዎች አየች ልትለቅማቸው ወደ ኋላ ተመለሰች ። ለጊዜው የተላከችበትን ጉዳይም ረሣችው ።

በሚሚ የበር ኳኳታ የነቃው መኩሪያ ደንድርን እየረገመ ከአልጋው አካባቢ የወደቁትን ባዶ የቢራ ጠር ሙሶች በአይኖቹ ቃኛቸው ። ወደ ነመኩሪያ ሰፈር መግ ቢያ ላይ ያለው ደንድር ባለ ኪዎስኩ የወ/ሮ ፋኖሴም ሆነ የመኩሪያ ደምበኛ ነው ። ካለ ፤ በገንዘብ ከሌለ በዱቤ የጠ የቁትን ከልክሏቸው አያውቅም ። ደንድር ደግሞ በየደ ምበኞቹ ቤት የሄዱትን ጠርሙሶች ለመልቀም ዘንቢሉን አንጠልጥሎ ጤዛ በማይረግፍበት ማለዳ ሁሌም አካባቢ ውን ያዳርሳል በር ይደልቃል ። የሰው ሰላምና እንቅልፍ ቢገፈፍ ደንታው አይደለም። በዚህ ተግባሩ ከመኩሪያ ጋር ዘወትር ቢጨቃጨቁም ጥላቻው ሥር የለውም ። የደን ድር ትህትና ያበርደዋል ።

ያኔም ደንድርን እየተራገመ በወለሉ ላይ የተንከባለ ሉትን ጠርሙሶች አንድ ላይ በእግሩ ሰባስቦ የሳሎኑን በር ሊከፍት ወጣ ። በሩን እንደከፈተው ከሱ ቁመት መለስ የሚል ቀጭንና ጥርሰ ወላቃ ሰው ጠብቆ ነበር ። ያየው ግን ከግሩ ስር ቀሚሷን ወደ ላይ አጥፋ ቆርኪና ቢልቃ

ጦች ሰብስባ የያዘች ትንሽ ልጅ ሚሚን ነበር ። በቆመበት ሽብረክ ብሎ የዘረጋችውን እጅዋን ተቀብሎ ሳመው ።

" ከየት መጣሽ " አላት እየደባበሳት

" ከቤታችን" አለችው የለቀመቻቸውን ቢልቃጦች በጨመደደችው ቀሚሷ ውስጥ እያየች

" ማነው ስምሽ "

" ሚሚ"

" ማን ላከሽ "

" እማዬና ያ ልጅ "

" እማዬ ስሟ ማነው "

" እማዬ ነዋ " የናቷን ስም ባለማወቋ ፍልቅልቅ ብላ ሳቀችበት

" እማዬ የት ነው ያለችው

" ተኝታለች "

የሚጠይቃትን ባግባቡ ከማትመልስለት ሕጻን ጋር መደናቆሩን ትቶ የሰጠችውን የተጨባበጠ ወረቀት ማንበብ ጀመረ ።

" አቶ መኩሪያ በፀና ሕመም ስቃይ አድሬ ደክሚያለሁ እባክህ ሆስፒታል አድርሰኝ ። ጐረቤትህ ።" ይልና ፊርማ ቢጤ ተጭሮበታል ።

ሕመምተኛዋ እማዬ ቀይ ትሁን ጥቁር የማያውቃት ሴት ሆነችበት በግራ ይሁን በቀኝ ከፊት ይሁን ከበስተኋላ ጉርብትናዋ በየትኛው አቅጣጫ እንደሆነ አያውቅም ። ያችን የዋኅና ነፍስ ያላወቀች ሕጻን አየት አድርጐ መንፈ ሱ እጅግ ስለ ተነካ ልጅቷን ተከትሎ ለመሄድና የአቅሙን

እርዳታ ሊያደርግ ወሰነ ። ልብሱን በፍጥነት ለባብሶ የመ ኪናውን ቁልፍ ከኮቱ ውስጥ መኖሩን አረጋግጦ ቆማ የምትጠብቀውን ሕጻን እጅዋን ይዞ ከግቢው ወጣ ።

ትንሿም ልጅ እጁን ይዛ እመር እመር እያለች እየ ዘፋፈነች አንዳንዴም በኮልታፋ አንደበትዋ ታወራው ነበር ።

" አንተ" አለችው በሚጥም የሕጻን አጠራርዋ

" አቤት ሚማዬ " ሙሉ ፈገግታውን እያሳያት

" አንድ ልጅ እማዬን ቧጨራትና አለቀሰች ። እኔ ደሞ ዝም በይ ብዬ ሳምኳት " አለችው እንዲመልስላት አንጋጣ ዐይን ዓይኑን እያየች

" የቱ ልጅ ወንድምሽ ነው"

" አይ እሱ ትልቅ ልጅ ነው ተኝቷል እኮ " አለችው ጉዳዩ እንቆቅልሽ ቢሆንበትም ሚሚን ለማስደሰት ሲል ብቻ

" ልጁ ሁለተኛ እንዳይቧጭራት እንቀጣዋለን" አላት ። በዚህ መልሱ ደስ ብሏት እጁን እንደያዘች እን ጣጥ እንጣጥ እያለች ወደቤታቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ምነው ሰው በእድሜው ሙሉ እንደ ህጻን የዋህና ንጹህ ቢሆን በሚል ሀሳብ መለስ ቀለስ እያለ የያዛትን ሕጻን እያየ ከዋናው መንገድ ወደ ግራ በምትወስድ ቀጭን የእግር መንገድ ታጥፈው ከአንድ የእንጨት አጥር ካለው ችምችም ካለ ግቢ ውስጥ ገቡ ። ሥፍራው ከወ/ሮ ፋኖሴ ግቢ በስተጀርባ መሆኑ ነው ። ሕጻኗ ቀድም ብላ በሩን ገፋ አድርጋ ገባችና'ና ግባ' አለችው እየተፍለቀለቀች ። ቤቱ ጨልሟል ። ወደ ውስጥ ራቅ ብሎ እጅግ የፈዘዘ መብራት

ይታያል ። አይኑ ከጨለማው ጋር እስኪላመድ ጥቂት ደቂ ቃዎች እንደመቆም ብሎ ፤

" እንደምን አደራችሁ " አለ ። መልስ አጣ ። ግራ ገባው ። ሚሚ ካአጠገቡ ብዙም ሳትርቅ ቆማ ነበር ። " ሚሚዬ እማዬን ቀስቅሻት " አላት ። ለማዳዋ ሕጻን ወደምታውቀው አቅጣጫ በጨለማው ውስጥ ተሠወረች። " እማዬ እማዬ ያ ልጅ መጥቷል ተነሽ " ስትል ሰማት ። የልጅቱን ድምጽ ተከትሎ የመኝታውን አቅጣጫ ፈላለ ገና በመጠኑ ታየው ። ቢልለት የሷን ዓይነትና ከሷ በላይ የሆኑ በርካታ ልጆች ወልዶ ማድረስ የሚችለውን ጐል ማሳ " ያ ልጅ" ስትል በመስማቱ በአገላለጿ እየሳቀ ከበሩ አካባቢ ሳይነቃነቅ በቤቱ ውስጥ ያለውን ጠቅላላ ሁኔታ ላፍታ ቃኘው ። ጭለማው የከበደ ስለነበር እጅግም ግልጽ የሆነለት ነገር አልነበረም ። የሚያቃስት ድምጽ ሰማና ሕመምተኛዋ እማዬ ከአልጋዋ ተነስታ ልትመጣ መሆኑን ገምቶ ደግፎ ለማውጣት አማረው ግን ጨለማው አላ መች አለውና " መብራት ቢበራ ይሻላል ፤ ነይ ሚሚዬ መብራቱ ማብሪያውን አሳይኝ " አለ ።

በደበዘዘው ብርሃን በመጠኑ ከሚታየው አልጋ ላይ የሚንቀሳቀሰውን የሰው አካል በአንክሮ እየተመለከተ እንዳለ ድንገት የግራ ፊቱና ጆሮው በትልቅ መዳፍ ጥፊ ነደደ ። እንደ መብረቅ ብልጭታ ቅጽበታዊ እሳት ከዐ ይኑ የተወረወረ መሰለው ። ሚዛኑን መጠበቅ አቃተ ውና ተግተረተረ ።

እንቅልፍ ማጣትና ድካም የቢራውም ራስ ምታት በጠነከረበት ምሽት ማግስት ሆነበትና ባረፈበት ጥፊ ዞረ በት ። ወደ ኋላ ለመመለስ ሞከር ሲያደርግ በሩ በኃይል ተወርውሮ ተዘጋ ። የነበረው አማራጭ ከማያውቀው ከማ

ያየው ሰው ጋር ምክንያቱና ውጤቱ ለማይታወቅ ግብ ግብ ራሱን ማሰናዳት ነበር ። ብዥ ያለበት ሲረጋጋ ሀሞቱን ከተት አድርጐ መንፈሱን ሰብስቦ እጆቹን ለቡጢ አዘጋጅቶ ጥግ ይዞ ቆመ ።

እጅግ የደበዘዘውን ብርሃን በቁመቱና በትኅሻው ስፋት ጋርዶ የቆመው ግዙፉና የጠቀረው ሰው እጆቹን ደጋግሞ በጭንቅላቱ አኳያ ሰነዘረበት ። መኩሪያም መሞከሩ አልቀረም ። የመኩሪያ ምት ግን ሰውየውን የጐዳው አልነበረም ። በዚህ መወራጨት መሀል በሱ በኩል የነበረ የባልዲ ውሀ ተደፋና መኩሪያ በቀላሉ አዳልጦት ወደቀ ። ሰውየውንም እግሩን ጐትቶ ጣለው ። በተራ በተራ ከላይና ከታች እየሆኑ በቡጢ ከተደባደቡ በኋላ እንደ ድንገት ከመኩሪያ እጅ የገባችው ዱካ ገላገለችው ደህና አድርጐ ከጭንቅላቱ ላይ አሳረፋት ። ባላንጣው እጆቹን መሰንዘር አቆመ ። መኩሪያም የሙት ሙቱን ከተቀመጠበት ግዙፍ አካል ላይ ተነስቶ ግድግዳውን ተደግፎ ሲተነፍስ ማብሪያ ማጥፊያውን ነክቶት ኖሮ ቤቱን ብርሃን አጥለቀለቀው ።

ሁሉም ነገር ተገለጸ ።

ከወገቧ በላይ አካሏ ይታያል ። በክንዷና በትከሻዋ ላይ የተጋደመው ሰንበር የጠቀረ ደም እንደቋጠረ ያስታውቃል ። ጸጉሯ ተንጨፍሮ የተንጫጨውም በትራሷ አካባቢ ተበትኗል ። ከግንባሯና ከጉንጫ አካባቢ የተንሣው እብጠት የዐይኗን ሥፍራ ደብቆታል ። በትርምሱ ወቅት ከፍርሃት የተነሣ ተሸሽጋ የነበረችው ህጻን ብርድ ልብሱን ገልጣ ብቅ ስትል ደግሞ ከሞላ ጐደል የሴትዮዋ አካል ታየው ። በደም ተውጣለች ።

የሴቲቱን ማንነት ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጐት አድሮበት ነበርና አስተውሎ ተመለከታት ። ጥቂት እንደማቃሰት ብላ እብጠት ያልበዛበትን ነገር ግን የበለዘውን ዐይኗን ገለጠች ። አያት አየችው ። በዱላ የደቀቀችውን ሴት ሊያውቃት አልቻለም ። እንደ ጥቅሻ ቢጤ እጅዋ በተዘረጋበት እንዳለ በጣቶቿ እንቅስቃሴ ወደ አንድ አቅጣጫ አመለከተችው ። አፏንም እንደማንቀሳቀስ ሞከር አደረገች ። አልገባውም ። ጣቷ ወደ ተቀሰረበት አቅጣጫ መለስ ሲል በደረቱ የተኛው ሰው ሊነሣ እየሞከረ ብዥ ያለበትን እይታውን ለማስተካከል ዐይኑን ሲያሻሽ አየው ከመነሣቱ በፊት በሩን የኋሊት ዘግቶ ወጣ ። ከግራና ከቀኝ ያሉት ጐረቤቶች እንደ ወ/ሮ ፋኖሴ ቤተክርስቲያን ሄደው ካልሆነ በቀር ያ ሁሉ ግብግብ ሲደረግ በቤቱ ውስጥ ያለው ዕቃ ሲንኳኳና ሲታመስ ብቅ ብለው ሁኔታውን ይረዱ ነበር ። ሆኖም ብቅ ያለ ሰው አልነበረምና ሰው አየኝ አላየኝ በማለት ልብሱን እያስተካከለ ፟እያራገፈ ጸጉሩን እየደመደመ ፊቱን እያሻሸ ፈጥኖ ወደ ቤቱ ተራመደ ። የግቢውን በር ሊከፍት ሲል ያችው ሕጻን ከኋላው ከኋላው ስትሮጥ ነበርና ጠራችው ።

እጅግ ተበሳጭቶ ነበርና እንደ ኳስ በእግሩ ሊያጐናት አሰኘው ። ሆኖም አላደረገውም ። በጠቀረ ፊቱ መለስና ጐንበስ ብሎ ተመለከታት ። “ ያንን ልጅ መታኸው ” አለችው ከበፊቱ ባልተለየ ፈገግታዋ አንጋጣ እያየችው ። መልስ ሳይሰጣት የግቢውን በር ዘግቶ ገባ ። እዚያው እንደ ቆመች ሚሚ ምርር ብላ አለቀሰች ።

መኩሪያ እንደገባ በቀጥታ የሄደው ግድግዳው ላይ ወደ ተሰቀለው መስታወት ነበር ። በሰውየው ጥፊና ቡጢ ፊቱ በሚገባ ማበጡን አየ ። የነገሩን አጀማመርና መጨረሻውን አሰላስሎ ከልቡ ሥር በተፈነቀለ ሣቅ ቤቱን

ሞላው ። የገጠመው ሁኔታ እያበሳጨውም እያስገረመውም ብቻውን ከወዲያ ወዲህ ሲንጐራደድ ቆይቶ በቀዝቃዛው ውሀ ገላውን ተለቃልቆ ልብስ ለውጦ የግንባሩን እብጠት የሚከልልበት ኮፍያ ሲፈላልግ እናቱ ሲጠሩት ሰማ ። በነበረበት ሁኔታ በተለይም በዚያ ሰዓት የእናቱ ከቤተ ክርስቲያን መመለስና ከቤት መገኘት አስጠላው ። ደጋግመው ሲጠሩት ባለበት የመኝታ ክፍሉ ሆኖ ወፍራም ድምጹን ዘለግ አድርጐ በማሰማት ቶሎ እንደሚመጣ መለሰላቸው ። ከወደፊቱ መጠለያ ቢጤ ያለውን ቡናማ ኮፍያውን ዙሪያውን ለጥጦና አራግፎ እስከ ግንባሩ ዳርቻ ድረስ ደፍቶት ወጣ ።

ኮፍያ ማጥለቁ ፣ እስከ ግንባሩ ጠርዝ ማውረዱ አዲስ ፈሊጥ ሆነባቸውና እንደ እንግዳ ሰው ልጃቸውን አሻቅበው ተመለከቱት ። አንዴ መጠየቅ ከጀመሩ በቀላሉ የማይለቁት መሆኑን ስላወቀ ቶሎ እንደሚመለስና ቀጠሮ እንዳለው እንደ ቸኮለም ገልጾላቸው እንደ ቆሙ የሳሎኑን በር ዘግቶባቸው ፈጥኖ ወጣ ። የማታው የቀጠሮ ሰዓት ማለፉን እያወቀው በጉጉት ይጠብቀው የነበረው ቀጠሮ ነበርና በተስፋ ወደ ተባለው ስፍራ በታክሲ በረረ ። ከተጠቀሰው ስፍራ ሲደርስ ሰው የለም ። ከአፍንጮ በር አፋፍ ላይ ከአውቶቡስ ፌርማታው ቆሞ ግራና ቀኝ መለስ ቀለስ እያለ አንድ ሰዓት ያህል ጠበቀ ። የሚመጣው ሰው ሁሉ በታክሲ ወይም በአውቶቡስ እየተሳፈረ የሚሄድ እንጂ እንዲህ እንደሱ ሰው ጠባቂ አልነበረም ። ይበልጥ ተናደደ ። ቀኑን ረገመው ። ሰዓቱም ተዘቃዘቀና እሱንም ራበው ታክሲ አስቁሞ ወደ ፒያሣ ተሻገረ ።

ቁልቁል ወደ እቴጌ ሆቴል አመራ ። የሆቴሎች አውራና ግርማ ሞገሱ ያልተገፈፈውን ይህን ሆቴል ስለሚወደው ያዘወትረዋል ። ጸጥታው ፣ የመስተንግዶው ሥነ ሥርዓት ሆነ ብሎ ለስፍራው የሚመረጠው ለስላሳ ሙዚቃ ተቀናጅተው የመንፈስ ትፍስሕት ይሰጡታል ። ሲጋራውን ይዞ ቢራውን እየተጐነጨ የህሊና ጨዋታ በማድረግ ረዘም ያለ ጊዜ የሚያሳልፍበት ስፍራ ነው ። ያኔም ገና ከማለዳው የለከፈውን ቀን ለማገባደድ በስተቀኝ ክንፍ የታችኛውን የመጨረሻ ጥግ ይዞ ተቀመጠ ። ሙያቸውን በአግባቡ የሚያገለግሉበትና በትህትናቸው መወደድና መከበር ያተረፉት የሆቴሉ አንጋፋ አስተናጋጅ ሥርዓት ባለው የአቀራረብ ልምዳቸው ፍላጐቱን ጠይቀው ወዲያው አቀረቡለት ።

የራበውን ያህል አልበላም ። ወደ ቢራው አደላ ። ሲጋራውን አከታትሎ እያጨሰ ከማለዳ እስከ ረፋዱ የዋለውን ውሎ እንደገና እያሰላሰለ በተቀነባበረ ሁኔታ ሲያጠቃው የተዘጋጀውን ሰው ማንነት ለማወቅ አጥብቆ ተመራመረ ። ለዚህ ሁኔታ የሚያበቃ አንዳችም ሊያስታውሰው የሚችል ቅሬታ ጠብ ኩርፊያ አልከሰትልህ አሉት ። ጉዳዩን በዝምታ ማለፍ ፣ ለፖሊስ ማሳወቅ ፣ ለሰው ማማከር የትኛው እንደሚሻልም አሰበ ። ለክፉም ለደጉም ሕግና የሕግ ሰዎች ያወቁት ነገር እንደማይከፋ አምኖ ጉዳዩን ፖሊስ ጣቢያ ሊያቀርብ ከነጊዜው ከነ አባባሉ ተዘጋጀ ። ከዚያም ቀጠል አድርጐ ፣ የጓጓለትና የፈረሰበት ቀጠሮ ጉዳይ ሌላ ብስጭት ሆኖ ከነከነው ። የደወለችው ሴት ማን ትሆን ፣ ደጋግሞ ያስደወላትስ ጉዳይ ምን ይሆን የሚለው ሀሳብ በይሆናል ልዩ ልዩ መላ ምቶች ውስጥ እንዲዋኘርቅ አደረገው ።

ድንገት አንድ ሀሳብ ብልጭ አለበትና አስደነገጠው። በሕጻን ጥሪ ከሰው ቤት እንዲመጣና እንዲደበደብ ያደረገው ያላወቀው ጠላቱ የሸረበለት ሌላው የማጥቂያ ዘዴ እንደሆነም ጠረጠረ ። ይኼኛው ጥርጣሬው ደግሞ ይበልጥ

አጠናከረውና የሆነውን ሁሉ ፖሊስ እንዲያውቀው ወሰነ አብሮ አደግ ጓደኛውን መቶ አለቃ አፈወርቅን አሰበው።

የቀጠሮው መፍረስ የፈጠረበት የመንፈስ ውጥረት ረገብ አለለት ። እቅዱም አላማውም ወደ አንድ አቅጣጫ ተሰባሰበ ። ከእንግዲህ ድርጊቱን በደሉን ለፖሊስ ማሳ ወቅና ጠላቱን ማረጋገጥ ብቻ እንዲሆን ጸና ። በጊዜ ወደ ቤቱ መግባቱን ጠላው ። ወንደላጤዎች ከሚሰጡት ምክ ንያት አንዱን ሰጥቶ እናቱን እንዳይጨነቁ አድርጐ ወዲሁ መሀል አራዳ ለማደር አሰኘው ። በሰፌው የሀሳብ መስክ የግሉ የሆኑትን ልዩ ልዩ ጉዳዮች ሲያነሳ ሲጥል ሲሄድ ሲመጣ ከባድ የመንፈስ ድካም እንደደረሰበት የሚያው ውቀው እሱ ብቻ እንጂ ውጫዊ ተመልካችማ በዝምታው የረጋ ሮስላምና በጸጥታው የሰከነ መስሎ ሊታየው ይች ላል ። ለነገሩ መኩሪያ በልምድ ያመጣው ሳይሆን በተፈ ጥሮው ዝምተኛ ነው ። ይህ ዝምታው አንደበቱን እንዲና ፈቅ አድርጐታል ምኔ በቱናገረ፡ ምኔ በሳቀ የሚሉ ተመል ካቾችና አድማጮች አሉት ። ተናግሮ መሰልቸት ፤ አል ፎም ሰው ማስቀየም አልፈጠረበትም ። ይህ እርጋታውና ግዙፍ ቁመናው ተደማምረው ያከብዱታል።መኩሪያ የዋ ኅም ባይሆን ደግ ነው ።

እረፍት አንጻራዊ ነው እንደሚባለው ሁሉ ተቀምጦ ውሎ ሲሄድ የዋለ ያህል ደከመው ። ወደ ሶፋው ተለጥጦ እንደማንጠራራትና እንደ ማዛጋት ኳደረገው በኋላ መለስ ብሎ አካባቢውን በአስተውሎት ቃኘ ። የራሱን ጭውውት ተወት አድርጐ የውጭውን ድምጽ ማዳመጥ ጀመረ ። የካሣ ተሰማ ብርቱካኔ ክራር ቅኝቱ ነፍሱን ዳሰሰው ። የፋኖ ግርፉ ይዞት ነጐደ ። ይህንኑ የካሣ ቅኝት የምትወድ ዕድል ይሁን አጋጣሚ ከሱ የነጠላትን ሴት ለቅጽበት አሰ

ባት።በዚህ ትዝታ መነካካቱን ጠላውና ራሱን ቶሎ መለሰ። የተስፋዬ ሣህሉ “አንቺ ሆዬ ለኔ” ቅኝት አዝናናው ።

የያዘውን የሲጋራ ቁራጭ መተርኮሻው ላይ ጨቁኖ ካሻሻተ በኋላ ሌላ ሊያቀጣጥል ፓኬቱን ቢዳብስ አጣ ። ወዲያው ከግራ በኩል ተወርውሮ የመጣ የዊንስተን ፓኬት ተንሸራቶ ከፊቱ አረፈ ። አቅጣጫውን ተከትሎ የወረወረ ለትን ሰው ለማየት ዞር አለ ። እሱ ከመግባቱ በፊት ገብታ ኢያነበበች ፤ ኢያጨሰች ቢራዋን እየተጐነጨች የነበረ ችው ሴት መሆኗን አየ ። ምስጋናውን ከአንገቱ ዝቅ በማለት ካስታወቀ በኋላ ተቻኩሎ አንድ ሲጋራ አውጥቶ አቀጣ ጥሎ ፓኬቱን በትህትና መለሰላት ። በሀሳብ ማጥ ሰምጦ ሲዳክር ፤ ሲበሳጭ ፤ ሲደነቅ አንዳንዴም ብቻውን ሲስቅ አስተውላው ነበርና ጉዳዩ ባይገባትም ሁኔታው አሳዝ ኗት ነበር ። ይበልጥ እንድታስተውለው የሳባት ግን አልፎ አልፎ እየተገረመ ፈገግ ሲል ፈገግታው የሚፈጥረው የጉን ጮቹ ስርጉዳት ነበር ። ጥሎባት ፈገግታ የሚያሰረጉደው ጉንጭ ትወዳለች ። የሲጋራን ጥማትና ማቅበዝበዙን እሷም ስለምታውቀው የኪሱን ጨርሶ ሲቸገር በዝምታ ማለፉንም አልቻለችውም ።

ከዚያ ወዲያ መኩሪያ ራሱን ወዳለበት አካባቢ መልሶ ዙሪያውን በአግባቡ ማስተዋል ሲጀምር ልብ ብላ መመ ልከቱን ትታ በያዘችው መጽሔት ላይ አቀረቀረች ። ቆይታ ቆይታ ቀና ባለች ጊዜ ግን ዐይኖችዋ በሰያፍም ሆነ በሙሉ አስተያየት መኩሪያን መቃኘታቸው አልቀረም ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለተለየ ሀሳብ ጋበዘውና በሴትዬዋ አድ ራጐት እየተገረመ ደጋግሞ እንዲያያት ተገደደ ። የተሰ ጠውን ሲጋራ ለአያያዙም ለአጫጫሱም ለማጣጣሙም ልዩ አክብሮትና ትኩረት ሰጠው ። መኩሪያ ከሰዎች ውለታ ወይም ስጦታ ከመቀበል ይልቅ መስጠትን ስለሚ

ወድ እንደ ትልቅ ነገር ከበደው ። አጫጫኗን ፤ አለባበሷን፤ አቀማመጧን ፤ ጸጉር አበጣጠርዋን መልኳን በጥንቃቄ እያስተዋለ በውጫዊ ሁኔታዋ የሴትዬዋን ምንነትና ማን ነት ለማወቅ ብዙ ግምቶችን እየጣለ ሞከረ ። ከተፈጥሮው አፍጦ ሰው ማየት ስለሚጠላ እንዳጐነበሰ ሰረቅ እያደረገ በዓይኖቹ ሲመላለስባት አልፎ አልፎ ዐይን ላይን እየተ ጋጩ ደንግጦ ያቀረቅር ነበር ። ሲጋራ አከታትላ ስታጨስ ቢራ ደጋግማ ስትጠጣ ፤ በረዥም ቆይታዋና በብቸኝነትዋ ቅንጣት ያህል መጨነቅ ወይም መሰቀቅ አላየባትም ። በዚያ አካባቢ በመገኘትዋ ፤ በመጠጡም ሆነ በምታነበው ጽሁፍ የረካች ትመስላለች ። ማንም ቢመጣ ማንም ቢሄድ ደንታ አልነበራትም ። መኩሪያም መጨረሻዋን ለማየት ቢራ እንደገና አዞ ይመለከታት ነበር ። እንደ መኩሪያም ብዙዎች የአካባቢው ሰዎች በተለየ ሁኔታ ቢመለከቷትም ቀና ብላ ያየችው አልነበረም ። ነገረ ሥራዋን ካጤን በኋላ አጠቃላይ በሆነ ግምቱ ፈረንጅኛውን ባህል በአንድ አጋጣሚ ያየችና የተቀበለች አድርጐ ጠረጠራት ።

ዘምቢል የሚያህል ቦርሣዋን ከፊት አድርጋ የገንዘብ መያዣዋን ትንሽ ቦርሣ አውጥታ ለአስተናጋጁ ትሁት ሰው የሚፈለግባትን ሂሣብና ጉርሻ ጭምር ከፍላ መጽሔቶችዋን ሰባስባ ከመነሣትዋ በፊት የተጋመሰ ሲጋራዋን አከታትላ ስባ ቁራጩን በመተርኮሻው ላይ እያሻሸች ለአ ፍታ መኩሪያን ተመልክታ ከሀሳቡ የተላቀቀ መሆኑን አረጋገጠች ። በፊካ ገጽታ ቢያያትም በቃልም ሆነ በአካል ሰላምታ ሳትሰናበተው ተነስታ ሄደች ። አድራጐትዋ ገር ሞት ተከትሏት ሊሮጥ አማረው ። የአካባቢውን ሰው አፈ ረና ሳይወድ በተቀመጠበት ቀረ ። እንደ ድንገት ብልጭ ያለ ሀሳብ ጭንቅላቱን መታው ። እሷንም ጠረጠራት ። ያላወቀው ባላንጣው የላከበት ሌላዋ ዓይነት ወጥመድ

ትሆን ብሎም ደጋግሞ አሰበ ። ህሊናው በሁለት ተከፈለ ። ልትሆን አትችልም የሚለው ጥቂት አየል አለበትና ሊከ ተላት ወስኖ ተነሣ ። የሚፈለግበትን ሂሳብ ከፍሎ የሚ ያከብራቸውን ባለ ገብስማ ጸጉር አስተናጋጅ አነጋግሮ ተሰናብቶ ሲወጣ አሥራ ሁለት ሰዓት ከሃያ ሆኗል ። ሴትዬዋ የወጣችው ከአስራ አምስት ደቂቃ በፊት ነበር ። ከመንገዱ ጠርዝ ሲደርስ ቆም ብሎ አሰበ ። ቀኙን ይዞ በክሪዚያሲስ ታጥፎ ወደደጐል አደባባይ ሊወጣ አማ ረው ። እንደገናም ግራውን ይዞ በሲኒማ ኢትዮጵያ ጀርባ አድርጐ ወደ መሀል መናኸሪያ መሄድ ፈለገ ። ታቹን ወደ አሮጌው ቄራ ሄዶስ እንደሆን የሚል አጠራጣሪ ሃሳብ መጣበት ። ግራ መስመሩን መረጠና ፈጠን ፈጠን ብሎ ተራምዶ ወደ ሲኒማ ኢትዮጵያ ታጥፎ ኤሌክትሪክ ሕንጻ ሲደርስ ቆመ ።

ቁጣሮ እንዳለውና አጥብቆ ሰው እንደሚፈልግ ሰው ዐይኖቹ ወዲያና ወዲህ እየተንከራተቱ ፤ የልብስዋን ቀለም የቦርሳዋን ትልቅነት ምልክት አድርጐ ተቸግሮ ፈለጋት ። የደጐልን አደባባይ ዞሮ ወደ አራት ኪሎ በሚ በር ታክሲ ውስጥ እንደ ድንገት አያት ። ከሚገባው በላይ ዋጋ ወስኖ በሌላ ታክሲ በሰፊ ርቀት ተከተላት አቅጣጫ ዋ ወደ ሾላ መስመር ነበርና ባለታክሲውም እየገረመው እንደታዘዘው በርቀት የሚያየውን ታክሲ ተከትሎ ከነፈ። የቀደመው ታክሲ እንግሊዝ ኤምባሲ በር አካባቢ ደርሶ ሴትዬዋ ስትወርድ መኩሪያን የያዘው ታክሲ ደግሞ ከቤ ልጅግ ኤምባሲ አለፍ ብሎ ነበርና አያት ። የታክሲውን ሂሳብ ከፍሎ አመስግኖት እንግሊዝ ኤምባሲ በር ሲደርስ ወረደና መኩሪያም ቁልቁል ፈጥኖ ተራመደ ። ጊዜው በመምሸቱ ለዐይን ይዟል ። ግራና ቀኝ ያሉትን መንደሮች አልፉ ከሚዳው ደርሶ ነበርና በሰፊ እርምጃው ደረሰባት

ኋላም እርምጃውን መጥኖ ከጐን ከጐኗ መሄዱን አይታ ልብ ብላ እስተውላ አስታውሳ ፈገግ አለች ። ፈገግታዋን ጭለማው ጋርዶት ለመኩሪያ አልታየውም ። ይከተለኛል ብላ በጭራሽ አላሰበችም ነበርና ገርሟት ጆሮዋንና አካሏን አንቅታ በዝምታ ተራመደች ። ሊያነጋግራት እየፈለገ ምን ብሎ እንደሚጀምር ቸግሮት ረጅም መንገድ አብሯት ገሰገሰ ። ከኋላም ከፊትም የሚመጡት ሰዎች እያለፏቸው ሄደው መንገዱ ጭር ሲል በቅጡ ተጠግቶ የምሽት ሰላምታ ከሰጣት በኋላ ሳትሰናበተው በመውጣትዋ ቅር መሰኘቱን በመግለጽ ወቀሳ ቢጤ ሰነዘረ ። ወዲያውም ይበልጥ ሊያውቃት እንደፈለገ በመግለጽ ራሱን በቅድሚያ አስተዋወቃት ። ሰላምታውን ተቀብላ ማንነቷንም ነገረችው ። ያሰበውን ሁሉ ተናግሮ ሳይጨርስ ወደ ቀኝ ታጥፋ ቤትዋ ወደሚገኝበት መንደር ለመግባት አቅጣጫዋን እየለወጠች ስትሰናበተው ስንብቱን ተቀብሎ ቶሎ አልተለያትም ። ዳግም ተገናኝተው እንዲነጋገሩ እንዲጨዋወቱ ፈቃድዋን በመጠየቅ ቀን ቀጠሮ እንድትሰጠው ጨዋነት ባልተለየው ሁኔታ አሳሰባት ። ግብዣውን ተቀብላ ከሶስት ቀን በኋላ ሊገናኙ ተቀጣጥረው ተለያዩ ። መኩሪያም ቁልቁል በመንደሮቹ መሀል አቆራርጦ ወደ ቤቱ ወረደ ።

በሶስተኛው ቀን በቅድሚያ ከቀጠሮው ቦታ የደረሰው መኩሪያ ነበር ። ከሰላምታቸው ጀምሮ ጭውውታቸውን ለተመለከተ አንዱ ሌላውን በቅርብና በወግ የሚያውቅ ይመስል ነበር ። መኩሪያ ግን ልቡ ለሁለት እየተከፈለ ከደረሰበት ድብደባ ጋር እያጣመረና እየነጠለ በራሱ ግምትና ትዝብት ውስጥ አመላለሳት ። በጨዋታቸው መካከል ሆን ብሎ በሰነዘራቸው ጥያቄዎች የፋናዩን የኑሮ ገጽታ የሥራ ሁኔታ የትምህርት ደረጃ ለማወቅ አልቻለም ።መልሷም ሆነ ንግግሯ የተጠነቀቀና ውሱን ሆነበት ። በርካ

ታውን ጊዜ በወቅቱ ገናና ወሬ በነበረው የመኳከለኛው ምሥራቅ ጦርነት ላይ ተወያዩበት ። መኩሪያ በልቡ የሻተው ጨዋታና የትውውቅ ወግ ግን ይህ አልነበረም ።

ጊዜው መሽቶ የውጭው ጨለማ እየከበደ የሆቴሉ የውስጥ መብራት እየደመቀ ሲታይ ግብዣውን አመስግና ለመሄድ ተሰናዳች ። የጠጡበትን ሂሣብ አጠናቆ ከፍሎ መኩሪያም አብሮ ተነሣ ። ሊሸኛት እንደ ተዘጋጀ ሲገልጽላት ሀሳቡን ተቀበለችው ። ከታክሲ መሳፈሪያው ድርሳ እንደገና ልትሰናበተው ስትቃጣ መኖሪያቸው በአንድ አቅጣጫ መሆኑን ነግሮ በታክሲ ተሳፍረው ወደ ሾላ መስመር በረሩ ። ከታክሲ ወርደው ቁልቁል ወደቤትዋ የሚወስደውን መንገድ ሲያያዙት ለሷ ከሚያወራው ይልቅ መኩሪያ ከልቡ ጋር ከፍተኛ ሙግት ገጥሞ ነበር ። አልፎ አልፎ እየተነጋገሩ ጨለማው በጠናበት መንገድ ከተጓዙ በኋላ ወደ መንደሯ ስታቃረብ እንደ ልማድዋ ለስንብት ተዘጋጀች ። የዘረጋችለትን ቀኝ እጅዋን ጨብጦ ቀልድና ጨዋነት ቀላቅሎ ቤትዋን እንድታሳየው ቡናም እንድትጋብዘው ተጭኖ ጠየቃት ። ጥቂት ከአቅማማች በኋላ ሌላ ቀጠሮ ሰጠችው ። ቀጠሮውን መቀበል እንዳልቻለ በትህትናና ሥርዓት ባለው አነጋገሩ ተቃወማት ። እጅግም ደስ ሳይላት ጥያቄውን ተቀብላ እሷ ፊት ፊት እሱ ተከትሎ ወደ ቤትዋ አመሩ ።

በሩ ተከፍቶ መብራቱ በርቶ ሲገባ ዓይኖቹ በቤቱ ውስጥ ያሉትን እቆችና የአቀማመጣቸውን ሥርዓት ቃኙ ብዙ ውድ እቃ የለበትም ። ንጽህናውና የሥፍራ አያያዙ ሁኔታ ግን ደስ አሰኘው ። የእንግዳ መቀበያና የመኝታ ክፍሉ በወፍራሙ የወላይታ ባለ ጥለት ሸማ ግርዶሽ ተለይቷል ። ከበሩ በስተግራ ወለሉ ላይ የተደራረበ ፍራሽ የሚያምር ጨርቅ ለብሶ ተዘርግቷል ። ሶስት ትራሶች ተጥለው

በታል ። መጠናቸው አነስ ያለ ቀይ ሶፋዎች በቤቱ መካከል ተቀምጠዋል ። መጠነኛ ቢፌና አነስተኛ ቴሌቪዥን ተዛዝለው ይታያሉ ። ከመስኮቱ አጠገብ መጽሐፍ በብዛት የተሞላበት መደርደሪያ አለ ። ከአጠገቡም የተወጠረ ሸራ በላዩ ቅብና ስዕል ነገር ተወጥኖበት ብሩሹም ቀለሙም ከሥሩ ተቀምጦ ይታያል ። ከመጋረጃው በስተጀርባ ያለው ሁኔታ ለጊዜው ስውር ቢሆንበትም የጠባብዋን የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ይዘት በአጭር ጊዜ ውስጥ ገምግሞ ጨረሰ። ፋናዬ እንዲቀመጥ ጠይቃው ከመጋረጃው በስተጀርባ ከተከለለች በኋላ የምትሰራውን ባለማወቁ መቀመጡን ትቶ አለፍ ብሎ በመጽሐፍ መደርደሪያው ውስጥ በሰልፍ የቆሙትን መጻሕፍት አርእስት ማንበብ ጀመረ ። ከመጋረጃዋ ውስጥ እንደሆነች ቴፕ ከፍታ በካሣ ተሰማ ደርባባ ድምጽና የክራር ቅኝት የቤቱን ዝምታ ገሰሰችው ። የሌሊት ልብስ የመሰለ ዥርገድ ያለ የአበሻ ቀሚስ ለብሳ የአንገት ልብስ ቢጤ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ ብቅ ስትል ቆሞ ስላየችው እንደገና እንዲቀመጥ ጋበዘችው ። ጥያቄዋን በፈገግታ ተቀብሎ ሲቀመጥ ቶሎ ብሎ ያየችው የጉንጩን ስርጉዳት ነበር ። እንድትጋብዘው የጠየቃትን ቡና ለማፍላት ጉድ ጉድ ስትል ከመጻሕፍቱ መካከል መርጦ የያዛትን መጽሐፍ እያገላበጠ በዝምታ ተቀመጠ ። ከቡናው በፊት ራት ለማቅረብ ወዲያ ወዲህ ስትል እቃ በመቀበል ሊረዳት ተነሣ ። የሚቀርበውን ምግብና እቃ ወደ ጠረጴዛው ካደረሰ በኋላ ተቀምጠው ቤቷ ያፈራውን ተጋበዙ ። ገበታው ከፍ ብሎ ቡናው ከተቀዳ በኋላ የጊዜውን ጠንክሮ መምሸት አሳስባ ሳይበረታ ወደ መድረሻው እንዲሄድ በጨዋታዋ መሀል ጣል አደረገችበት ። መኩሪያ ግን ዐይኖቹ የተተከሉት ከስልክ መነጋገሪያው ላይ ነበር ። እንደ አጋጣሚ ስልኩ አንቃጨለ ከአጠገቡ ስለነበር አንስቶ ጥሪውን ተቀበለ የፋናዬን መኖር ተናግሮ መነጋገሪያ

ውን አቀበላት ። ከንግግሯ ይዘት በኑሮ ብቸኛ መሆኗን ገመተ ። መነጋገሪያውን በቦታው እንዲያኖር ስትሰጠው ተቀብሎ የራሱን ውሳኔ ለመፈጸም ሲል ፈቃድ ጠይቋት ደወለ ። አዳሩን እቤት እንደማይመጣ ነግሯቸው ዘጋ ። የናቱን መጨነቅ ያውቃልና ነግሮ ተገላገለ ።

በአባባሉ ተገርማ ስሜቷ ተኮሳተረ ። ለጥቂት ደቂቃች በጥያቄ አመለካከት አስተዋለችው ። ሀሳብዋን ስለ ተረዳ በቀጥታ መቅረቡን ትቶ ባለፈው ሰሞን የደረሰበትን በደል ረጋ ብሎ እያወራላት የሚኖራትን መልስና ሁኔታ በጥንቃቄ መከታተል ጀመረ ። በነገራት ሁሉ በመደነቅና በአዘኔታ ተመስጣ ስላያት ምናልባት ሌላዋ ወጥመድ ትሆናለች ብሎ የጠረጠራትን ሰረዘ ። አዳሩንም ፈቃደኛ ከሆነች ወለሉ ላይ በተነጠፈው ፍራሽ ላይ ካልሆነም በአቅራቢያው በሚገኝ ሆቴል ማድረግ የወሰነው ቀደም ሲል የደረሰበት ዓይነት በደል እንዳይደርስበት ለመጠንቀቅ አስቦ መሆኑን ቆፍጠን ብሎ አስረዳት ። የልቡ እውነት ግን እጅግ የተለየ ፍላጐት ነበር ። የተናገረውን ሁሉ ኮስማች በኋላ ቡናዋን በወግ አክትማ እቃዋን ማነሳሳት ጀመረች ።

ምሽቱን ከዚሁ አሳልፍ ፤ ወይም ማደሪያህን ፈልግ ሳትለው በመቅረቷ በተቀመጠበት ተደላድሎ የምሽቱን የቴሌቪዥን ትርኢት ተዝናንቶ መከታተል ቀጠለ ። ፋናዬም የራሷን ወሳኔ አድርጋ እንዲያድር ፈቅዳ ንጹህ አንሶላዎችና ብርድ ልብስ አምጥታ ጥግ ይዞ በተዘረጋው ፍራሽ ላይ ማንጠፍ ስትጀምር ማንጠፉን ረዳት ። ማንጣፉ ካበቃ በኋላ ሜሎቲ ኮኛክ እንዲጠጣ አቅርባለት እየጠጣና እየጠጣች ብዙውን ጊዜ ባላስተዋሉት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ አትኩረው አሳለፉት ። መታጠቢያ ክፍል ደርሳ ስትመልስ መልካም ምሽት ተመኝታ

ለት እንዲተኛ ነግራው ከመጋረጃዋ በስተጀርባ ተከለለች የኮመዲኖዋን የላይኛ ክፍል ከፍታ የምትመካበትን መጠበቂያዋን ካደላደለች በኋላ ሳትቆልፍ መለስ አድርጋ ትታው ተኛች ። የደበዘዘውን የራስጌ መብራትዋን አብርታ የእንግሊዙን ቢቢሲ ወሬ በለሆሳስ ከፍታ ማዳመጥ ስትጀምር መኩሪያ ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ገብቶ በሩን ሲዘጋ ሰማች ።

በመታጠቢያ ክፍሉ ለረዥም ጊዜ መቆየቱ እየገረማት በአካልም ሆነ በመንፈስ ንቃት ጠበቀችው ። ፋናዬም የቆየች ቆይታ በዚያች ወቅት ጠረጠረችው ለጥቅም የሚተናኮል ወስላታ ይሆን ብላም አሰበች ። መኩሪያም በመታጠቢያ ክፍሉ ውስጥ በተሰቀለው መስተዋት ገጽታውን እያስተዋለ እሱው ለሱ ብዙ ውይይትና ምክር ማድረግ ይዞ ነበር ። ላይተኛበት ባነጠፈው የመሬት መኝታ ላይ ለመጋደም ወስኖ ወጣ ።

የንጋት ወፎች አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ መዘመር ሲጀምሩ ነቃ ። ወዲያውም ውሀ ሲፈስ ሰማ። በጁም በእግሩም በአንሶላው ውስጥ ዳበስ ዳበስ አደረገ ። ፋናዬ ከአጠገቡ አልነበረችም ። መታጠቢያ ክፍል መግባቷን አውቀ ፈጥኖ ተነስቶ እስክትመለስ ድረስ አልጋውን አሟምሮ አነጠፈው ። ፍራሹ ላይ ተዘርግቶ የቀረውን ልብስም በመልክ በመልኩ አጣጥፎ አነሳው ።

ከመታጠቢያ ቤት ወጥታ ሻይ ስታፈላና እንቁላል ስትጠባብስ መኩሪያ ተጣጥቦ ወጣ ። የሻይ መጠጫ ብርቆጭዎችና የተዘጋጀውን ምግብ ከወጥ ቤት ወደ ሳሎኑ አቀራረበ ። ዛሬም ቢሆን የታገዱ ይመስል እምብዛም ንግግር አልነበራቸውም ። ቁርስ በልተው እቃውን አነሳስተው ሊወጡ ሲዘጋጁ ጊዜው ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ከሩብ

ሆኗል ። ቁልፉን ተቀብሏት በሩን ቆልፎ ፤ በአካሄዳቸውም እሷን አስቀድሞ ፤ ከግቢ ሲወጡ በሰከነ ሕይወት ውስጥ ዘመናትን አብረው የተራመዱ የተጣጣሙ ሰዎች ይመስሉ ነበር ።

" መልካም ቀን መኩሪያ " ብላው ታክሲ ስትሳፈር በአንገት ሰላምታ በሞቀ ፈገግታ ሸኘት ። ፈገግታው የሚፈጥራቸውን የጉንጩን ስርጉዳት ተጣድፋ አየቻቸው ። ወዳቸዋለች ። ታክሲው ይዟት በእንደራሴ ሰፈር አድርጐ ወደ ካዛንቺስ አቅጣጫ መብረሩን እንጂ መድረሻዋ ወዴት አካሄዱ ለምን እንደ ሆነ አላወቀም ። በውስጡ የሚንቀሳቀሰው ሀሴት በፈጠረለት ሙቀት በማለዳው ተዝናንቶ እሱም ወደ ሥራው ሌላ ታክሲ ይዞ ተሻገረ ።

ከቢሮው ሲደርስ በጐርናናው ድምጹ ፤ ረጋ ባለው አንደበቱ የጥዋት ሰላምታ ሰጧት አለፈ ። ጸሐፊው ተከትላው ገባች ። " እናትዎ ሁለት ጊዜ ደውለው ነበር " አለችው እየተቅለሰለሰች ። የተውለት መልእክት መኖር አለመኖሩን ከጠየቀ በኋላ እንዲደውል ብቻ መጠየቁን ስለነገረችው አመስግኗት ሊደውል ሲዘጋጅ በሩን ዘግታለት ወጣች ። ጣቶቹ የስልኩን ቁጥር ሲያሽከረክሩ ዓይኑ ሀሊናው ቤቱ ደርሶ እናቱን ከነጭንቀታቸው ከነሁኔታቸው ተመለከተ ። "ሀሎ" አሉ ያነሱት እናቱ ነበሩ ። የተለመደውን እሮሮ ቁጣ ካወረዱበት በኋላ ቸኩለው የደወሉበትን ምክንያት ነገሩት ።

" ልጅቷ ታማለች ብለው ደወሉልኝ አንተም ቶሎ እንድትደርስ ተጠርተሃል " አሉት ። መገረምም አድናቆትም ባለበት አባባል ፤

" የቷ ልጅ "

" እሱንማ አንተ ታውቃለህ ፤ ደዋዩ ሰውዬ የተጨነቀ ይመስላል ፤ አጥብቆ አደራ ስላለኝ አደራ በላ እንዳልሆን ነው የደወልኩት " አሉት እሳቸውም ምስጢሩን ባለማወቃቸው ቅር እንደ ተሰኙ በሚገልጽ ንግግር ።

" የት ሆስፒታል ነው ያሉሽ "

" ስድስት ኪሎ ሀውልቱ አጠገብ ካለው ነው አለኝ ቁጥሩ አሉና እንደማቋረጥ አሉ ።

"የምን ቁጥር" አለ "የተባለችው ልጅ የተኛችበት ነዋ" አሉት በቁጣ ።

"እሺ" አለ አካሉም ህሊናውም እየተቅበጠበጠ ።

ሠራተኞቸውን ከማድቤት ጠርተው አስታውሳ እንድትነግራቸው የነገሯትን ቁጥር ጠይቀው ነገሩት ። መልዕክቱን የሰጡት የወ/ሮ ሙሉ ጐረቤት ነበሩ ።

" እሺ" ብሎ ተሰናብቷቸው ስልኩን ዘጋ ።

ሰው ታሞ ወደ ሆስፒታል መሄዱን ለጸሐፊው ነግሮ ወደ ተባለው ሆስፒታል አመራ ።

እንደደረሰ ወደ ሁሙማን መኝታ ክፍል የሚያስገባውን በር ሊያልፍ አልቻለም ። ዘበኛው እንደ ብረቱ ጠንክሮ ብዙውን ሰው አግዶ አቆመው ። የአስታማሚነት ወረቀት ያላቸው ሲወጡና ሲገቡ በቀር መኩሪያና እሱን የመሰሉት ሰዎች ቆመው ቀሩ ። አስተዛዝኖ ቢናገር መልስ ሊሰጠው ቀርቶ ሊያዳምጠው ባለመፈለጉ የዘበኝነት ሥራ ሰብአዊ ርኅራኄ የሚባል ነገር የነጠፈበት የጨካኞች ተግባር ነው ብሎ ሊደመድም ቃጣው ። ከወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠ ነገር ሲያሰላስል ፤ ረጅም ቀሚሷን ከፍ አድርጋ ነጭ ውስጥ ልብሷን ለእይታ የጋበዘችው ቀይ ሻሽ የተከ

ናነበች ሴት ወደ ዘበኛው ጠጋ ብላ እንደመጨበጥ ካደረገችው ትንሽ ጊዜ በኋላ እንድትገባ ሲፈቅድላት በንዴት ተንደርድሮ ከዘበኛው ፊት ደረሰ ። ዘበኛውም እጁን ወደ ኪሱ አልከተተም ነበርና ተደናግጦ አሻቅቦ ተመለከተው እንደሚያጋልጠው ስለተረዳ እየተነጫነጨ መኩሪያንም እንዲገባ ፈቀደለት ።

ቤርላ የሕጻናት መኝታ ክፍል ከሚለው ሕንጻ ፊት ለፊት ደረሰና የመኝታ ክፍሉን ቁጥርና አቅጣጫ ጠየቀ። አቅጣጫውንና የጠየቀው ቁጥር የሚገኝበትን በስተቀኝ ያለውን ፎቅ አሳዩት ። ሶስተኛው ፎቅ ላይ ለመድረስ ደረጃዎቹን በእጥፍ እየተራመዳቸው ከተባለው የመኝታ ክፍል በር ላይ ሲደርስ ትንፋሹን ለመዋጥ ጥቂት ደቂቃዎች ቆመ ። በሩን በዝግታ ከፍቶ ሲገባ ሁለት አልጋዎች ላይ ሁለት ልጆች ተኝተዋል ። በስተቀኝ ካለው አልጋ ላይ የተኛው ልጅ ራሱ ላይ ጉዳት እንደደረሰበት በተለጠፈለት ፕላስተርና በተጠመጠመው ደም የሠረገው ሻሽ መረዳት ይቻላል ። አስታማሚዋ ሴት ልጁን ከማየት መለስ ብለው ተመለከቱት ። የሚያውቁት የሚያውቃቸው ባለመሆኑም ዝም ብለው ተያዩ ። በስተግራ በኩል ካለው አልጋ አጠገብ ያሉት አስታማሚ ደግሞ አልጋው ላይ ተደፍተው ቀና አላሉም ። "እግዚአብሔር ይማራቸው" ሲል ሴትዮዋ ቀና ብለው አዩት ። አያውቁትም አያውቃቸውም ነበርና ስብር ባለ አባባል 'አሜን' ብለው ተመልሰው ወደ ሕመምተኛ ሶዋቸው ዐይናቸውን መለሱ ። መኩሪያም ባለበት ቆሞ ቀረ ። ' ምነው ፤ ማንን ፈልገው ነው ' አሉት በስተቀኝ ያሉት አስታማሚ ። "እዚህ ክፍል ድረስ እንድመጣ ተጠርቼ ነበር " ሲል ከተቀመጡበት ወንበር ወ/ሮ ሙሉ ተስፈንጥረው ተነስተው ቆሙ ። እንደበታቸው ተንቀጠቀጠ ። አይን አይኑን እያዩት ዕንባቸው ወረደ ።

CamScanner

እንደምንም ጭንቀታቸውን ዋጥ አድርገው እሳቸው እንዳ ስጠሩትና ሊያነጋግሩት እንደ ፈለጉ ነገሩት ። ይዟቸው ወደ ውጭ ወደ መተላለፊያ ኮሪደር ወጣ ።

ሲቃ እየተናነቃቸው መናገር ስላልቻሉ ሁለት ፎቶ ግራፎች ከደረታቸው ልብስ ውስጥ አውጥተው ሰጡት አንዱ ከብዙ ዓመት በፊት የተነሣው የሱ ፎቶግራፍ መሆኑን አረጋገጠ ። ሌላውን ፎቶ ግራፍ ሲያይ እሱም ደንግጦ ሰውነቱ እንደ መብረክረክ ጀመረ ። “ የት አለች ? እሷነች የታመመችው ? ምንድነው ሁኔታው ፣ በሚል የተደራረበ ጥያቄ ወጠራቸው ። ኮእንባም ከሲቃም እየታገሉ ነገሩን ሁሉ አስረዱት ። አጣዳፊው ችግር ለትርፍ አንጀት ህመም ቀዶ ጥገና ለሚያስፈልጋት ልጃቸው ደም ማቅረብ ስለሆነ ደሙን እንዲሰጣት ተማጸኑት ። ጊዜ ሳያባክን ጋንዲ ሆስፒታል በስተጀርባ ወደ ሚገኘው የቀይ መስቀል ደም ባንክ ከነፈ ።

ያለደንቡ ሶስት እጅ ለታክሲ ከፍሎ ወደ ደም መስጪያው ሥፍራ ፈጥኖ ደረሰ ። አጣዳፊና አስቸኳይ ችግሩን ነግሮ በሞትና በሕይወት መሀል ያለችውን ልጅ ለማዳን ደሙን በሙሉ ፈቃደኛነት ተንጋሎ ተቀዳ ። ደም የሰጠበትን መግለጫ ይዞ እንደ ቀድሞው ከመደበኛ ክፍያ ይበልጥ እየሰጠ ወደ ሆስፒታል ገሰገሰ ። መኪናውን አለመያዙ አበሳጨው ።

የሆስፒታሉ ዘበኛ ገና ከሩቅ ሲያየው ጥቁር ፊቱን የበለጠ አጥቁሮ ተመለከተው ። ደም የሰጠበትን መግለጫ ወረቀት እያሳየ ለኦፕራሲዮን በአስቸኳይ የሚያስፈልግ መሆኑን ነግሮት ሊገባ ቸኮለ ። የበሩ ዘበኛ ግን ችኮላውና ጭንቁ ምንም አልመስልህ አለውና በሩን ከውስጥ እንደ ዘጋ በዝምታ ይንጐራደድ ጀመር ። ዐይኖቹ በአሻጋሪ

ካለው ፎቆ ላይ ተተክለው መንፈሱ ተንጠልጥሎ ነበርና ያችን ወረቀት እንዳንጠለጠለ መኩሪያም ከግቢው ወጭ ከወዲያ ወዲህ ተንቆራጠጠ ።

በዘበኛው ደንታ ቢስነት ተበሳጨ ። ኑነቀው እነቀው የሚል ስሜት ተሰራጨበት ። “ ይህን ወረቀት እንዳልሰጥ ከልክለኸኝ ታማሚዋ የሕክምና እርዳታ ሳታገኝ ብትሞት ኃላፊነቱ ያንተ ይሆናል ” አለው የጨበጠውን የግቢ መግቢያ ብረት በር በኃይል እየነቀነቀ ። ሁኔታውን ያዩ ፤ሰው ለመጠየቅ ፤ ዕቃ ለማቀበል ፤ ብርቱካንና ሙዝ ለመሸጥ፤ ጫማ ለመጥረግ የቆሙት ሁሉ መኩሪያን በመደገፍ በዘበኛው ላይ ተንጫጩበት ። ከአፈርኩ አይመልሰኝ ያለው ዘበኛ በእምቢታው ጸና ። በዚህ መሶሉ ሁኔታ ጥቂት ደቂቃዎች አለፈ ። የመኩሪያ ዓይኖች በአሻጋሪ ካለው ፎቅ ላይ ተሰክተው እጅግ በመጨነቁ ከአካባቢው ያሉት ሁሉ በአዘኔታ ይመለከቱት ነበር ። የሰዎች ትችትና ጭቅጭቅ ቀስ በቀስ እያስፈራው የመጣ ዘበኛ እየተጀነነ በሩን በጠባቡ ከፍቶ እንዲገባ ጠራው ። መኩሪያ የያዛትን ወረቀት ጉንበስ ቀና እያለ እያየ ተጣድፎ ገባ ። ሶስተኛው ፎቅ ላይ ለመድረስ ደረጃዎቹን በእጥፍ ተራመዳቸውና ከክፍሉ በር ላይ ሲደርስ ትንፋሹን ለመዋጥ ጥቂት ደቂቃዎች ቆመ ።

በሩን በዝግታ ከፍቶ ሲገባ ባየው ሁኔታ አለመጠን ደነገጠ ። አልጋው ባዶውን ነበር “ ውይ አይደንግጡ ፤ በሞትኩት ፤ መርፌ ለመቀየር ሀኪሞች ወደ መርፌ ክፍል ይዘዋት ሄደው ነው ” አሉት ልጃቸውን በማስታመም ላይ ያሉት ሌላዋ ሴት ። የድካሙም የድንጋጤውም ላብ ችምችም ካለው ጸጉሩ ውስጥ እየመነጨ በግንባሩ ላይ ፈሰሰ ። ፊቱን በመሀረም እየጠራረገ መርፌ ወደሚቀየርበት ክፍል ሄደ ። ኮቀጭን ክንዷ ላይ መርፌ የሚሰካበት ደም ሥር

CamScanner

ጠፍቶ እዚህም እዚያም እየተሞከረ ልጅቷ በሕመም ስት
ስቃይ ደረስ ። ዘገነነው ። እንደምንም የመርፌ ማስገቢያ
የደም ሥር ከተገኘ በኋላ በውስጡ መድኃኒት የተቀላቀ
ለበት ግሉኮስ በአግባቡ መስረግ ሲጀምር ወደ ክፍሏ እን
ድትመለስ ሆነና እናትዋና መኩሪያ አጅበዋት ነርስዋ
አልጋውን በዝግታ እየገፋች ወደ ክፍሏ ተመለሱ ።

ቀጭን ክንዷ ከጣውላ ጋር ታስሮ ጣውላው ከአልጋው
ጋር ሽብ ተደርጐ የተንጋለለችው ልጅ ሕመምዋን ተውት
አድርጋ በጉጉትና በመደነቅ እይታ አሁንም አሁንም ታየው
ጀመር ። መኩሪያም ገጽታዋን ለማየት ጊዜውም ሁኔታ
ውም የፈቀደለት በዚያ ሰዓት በመሆኑ ሕመምተኛዋን
ልጅ አትኩሮ በመገረም ተመለከታት። የያዘውን ደም የተሰ
ጠ መሆኑን የሚገልጸውን ወረቀት ለዶክተሩ ቢሮ እንዲ
ያሳዩ ለወ/ሮ ሙሉ ሲሰጣቸው ፤ እጅግ ዝቅ ብለው እጅ
ነስተው አመስግነው ተቀበሉት ። የሰጣቸውን ወረቀት
ለዶክተር ቢሮ ለማድረስ ሲሄዱ ነርሷ ውዴን ከመኝታዋ
አስተካክላ አንጋለለቻት ። መኩሪያም ከውዴ አልጋ
አጠገብ ተቀመጠ ።

“ ከመሰንበቻው ጥቂት ተሽሎሻል ” አላት በፈ
ገግታ ፤

“ በጐ ነኝ” አለችው ስልልና ድክም ያለ ድምጽ
ነበር ።

“ አይዞሽ በቂ ሕክምና ሲደረግልሽ የበለጠ በጐ
ትሆኛለሽ ”

“ እሺ” አለችው መጽናናትዋን በፈገግታ ለመግ
ለጽ እየሞከረች ።

“ ማን መሆኔን አውቀሻል ” አላት በይበልጥ ወደሷ
ጠጋ ብሎ በሹክሹክታ ፤

“ ማነህ አላወቅሁህም ” ራሷን በአሉታ በመጠኑ
አነቃነቀችው ።

“ አጐትሽ ነኝ የአባትሽ ወንድም ” አላት ።

በደስታም ፤ በድንጋጤም ውዲያው ስለ ተነካች
አፏን እንደ ከፈተች ቀረች ። ተነስታ ልታቅፈውም ይሁን
ልትስመው ፈልጋ የታሰረው እጅዋ ስላልተመቻት ብቻ
ሞክራ ተወችው ።

“ እውነትህን ነው” አለችው ዐይኖችዋ እንባ ቀስ
በቀስ እያቋቱ ፤

“ አዎ አጐትሽ ነኝ ። ለብዙ ዓመት ከኢትዮጵያ
ውጭ ስለነበርኩ አድገሽ እዚህ እስክትደርሺ ድረስ አል
ተገናኘንም ። ሕጻን ሆነሽ በደንብ አውቅሻለሁ ። ዛሬ ግን
ቆንጆ ልጃገረድ በመሆንሽ ፍጹም ተለውጠሽብኛል ።”
መኩሪያ ፈገግታ በሰፈነበት አመለካከቱ ዐይን ዐይኗን
እያያት አጐትነቱን ሲገልጽላት ፤ በጁም የግራ እጅ ጣቶ
ችዋን እያሻሸ ነበር ። ውዴም ፊቷ የደስታ ብርሃን አብ
ርቶ የተቋቱት የዕንባ ጠብታዎች ወደ ጉን አንሶላው
ላይ እየወረዱ ነበር ። እንባዋን በመሀረሙ እየጠራረገላት
በአድራጐቱም በአንደበቱም አጐት ያውም ደግ አጐት ፤
የሚያደርገውን እንክብካቤ ስላሳያት መንፈሷ ተጠናክሮ
በሽታዋን ለመቋቋም በገናው እንደ ሞከረ ከገጽታዋ ይነ
በብ ጀመር ። “ ስምህ ማ፤ው ” አለችው የሚዳስሳትን
እጁን ጭብጥ አድርጋ ደዛ ፤

“ የኔ ስም መኩሪያ ነው ያንችስ ” አላት

“ የት/ ቤት ስሜ ፍሬ መውደድ ነው ። እማዬ ግን
ውዴ ስለምትለኝ ብዙ ሰው እንደሷ ውዴ ብሎ ይጠራኛል።
አለችው ሣቅና ልቅሶ ባንድ ጊዜ እየታየባት ።

ደስታና መደነቅ በሰውነቷ ውስጥ ስለ ተሰራጨባት ከተንጋለለችበት ተነስታ ለመቀመጥ እንዲረዳት ጠየቀ ችው።በእጅዋ ላይ የተሰኳው መርፌ ጥንቃቄ እንደሚያስፈ ልገው ነግሯት አደላድሎ ካስተኛት በኋላ ስለ ትምህርትዋ ስለ ዝንባሌዋ ስለ ወደፊት ምርጫዋ አጨዋወታት ። ህመሙ ስላደከማት ብዙም አልመለሰችለትም ።

የውዴ እናት ወረቀቱን ለዶክተሩ ቢሮ ሰጥተው ሲመ ለሱ ፤ በልጃቸው ገጽ ላይ ሕይወት አንሠራርቶ ፤ ዐይኖቿ በርተው በፈገግታ ስትነጋገር በማየታቸው ደስ አላቸው። በመኩሪያ መገኘት እንኳን ልጃቸው እሳቸውም የጭን ቀታቸው ከፊሉ የወደቀላቸው በመሆኑ ቀለል ሲላቸው ታውቋቸዋል ። የአልጋውን ጠርዝ ተደግፈው አንዴ ልጃ ቸውን አንዴ መኩሪያን እያዩ በልባቸው ፈጣሪያቸውን ማመስገን ይዘው ነበር ።

መነጽሩን ጀርዎቹ እንጂ አፍንጫው ያልደገፉለት ኮሪያዊና አጠር ቀጠን ያለ ኢትዮጵያዊ ዶክተሮች በያ ዙት ወረቀት ላይ እየተወያዩ ስድስት ያህል በልምምድ ላይ ያሉ እጩ ዶክተሮች አስከትለው ሲገቡ መኩሪያና ወ/ሮ ሙሉ ስፍራውን ለቀው ወደ መተላለፊያው ኮሪ ደር ወጥተው ቆሙ ።

የበሽተኛዋን ልጃቸውን ሣጥኖችና ቦርሣዎች ማስ ታወሻ ደብተሮች በርብረው የመኩሪያን ፎቶግራፍ ካገ ኙና ካዩ ጀምሮ በህሊናቸው ውስጥ ቀርጸው የያዙትን እው ነት በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ከመኩሪየ ጋር ባደረጉት ጭውውት ልኩን አወቁት።ቀሪውን ችግር ለመፍታት የመ ኩሪያ መገኘት ዋናው ቁልፍ እንደሆነ ስለ ተረዱት አል ከፋቸውም ። ጉዳያቸውን ሁሉ ግልጥልጥ አድርገው ነገ ሩት ። ረጋ ብሎ በተመስጠ አዳመጣቸው ። በሰማው ሁሉ

ከልብ ተነካ ። እንዳሉት ሁሉ ሊያደርግ ተሰናዳ ። ወ/ሮ ሙሉ እንደ ምንተስኖትም የውዴ እናት መሆናቸውን አወቀ ።

የገቡት ሀኪሞች ተከታትለው ሲወጡ መኩሪያና ወ/ሮ ሙሉ ተመልሰው ገቡ ። ገላልጠው አይተዋት ነበርና ውዴ አተኛኘትዋ ተቀይሮ ነበር ። ከወ/ሮ ሙሉና ከውዴ ጋር ጥቂት ቆይቶ ሁኔታቸውን ሁሉ ከተገነዘበ በኋላ የሚመጣበትን ሰዓት ነግሮአቸው ተሰናብቷቸው ወጣ ።

በተሽከርካሪ ጋሪ ላይ ወጡን እንጀራውን ደርድረው በየ ክፍሉ ለበሽተኞች ምሳ የሚያቀብሉት ሠራተኞች እየተጣደፉ የሚያጣድፍ ትእዛዛቸውንና ንግግራቸውን እያንቃጨሉ በአጠገቡ ሲያልፉ ምግቡን ልብ ብሎ ተመ ለከተው ። እንጀራው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች “ራንግለር” ብለው የሰየሙት ከነ እብቁ ተፈጭቶ የሚጋገረውን ዓይ ነት ይመስላል ። ምግቡን ለመብላት ቀርቶ ለማየት ይቀ ፋል ብሎ አሰበ ። የመብላት አምሮቱም ተቆለፈ ። መኩ ሪያ በቀጥታ ወደ ቤት ሄደ ።

ሥጋና እርጅና የተጫነውን ቁመናቸውን እያርገደ ገዱ ከመኝታ ቤት ወጥተው በሳሎኑ ከጠፍር ድንክ አል ጋቸው ላይ ገና ሲቀመጡ መኩሪያ ተቻኩሎ ገባ ። እናቱ ወ/ሮ ፋኖሴ አድሮና ቀኑን አጋምሶ በመምጣቱ የደረ ረሰበትን ችግር ቢጠረጥሩም በግልጹ ሊያውቁ ፈልገው በጥያቄ ተቀብሉት፤

“ ምነው ልጄ ሰው ያስባል ይጨነቃል አትልም”

“ ተቸግሬ ነው እንደምትጨነቂስ አውቃለሁ ”

“ እንዲህ ለብቻህ የሚያሯሯሩጥህ ምን ችግር ገጠ መህ”

“ በግል የደረሰብኝ ችግር እንኳን የለም የቅርብ
ሰው ታሞብኝ ነው ” አላቸው ።

“ የታመመችው ልጅ ነች ሲባል እንጅ የቅርብ ሰው
ነው ሲባል አልሰማሁም ። ሲሆን በወጉ በማዕረጉ አግብ
ተህ ብትወልድ ቃሌን ብትቀበል ነውር አልነበረም ። ይህ
ቀርቶ ከውጭ የወለድካት ልጅህ ታማ በእግር በፈረስ
ተፈልገህ በነፍስ ድረስ ስትባል ለመደበቅ መሞከርህ
ምን ይሉታል ? እናትህ እንጂ ፤ አሳቢህ እንጂ ፤ ጠላትህ
አይደለሁ ምነው ታስቀይመኛለህ ” አሉት ቁጣቸው ፊደ
ቅሬታ እየተለወጠ ።

ጥያቄአቸውን በአጭር ለመቁረጥ አስቦ የሰጠው
ምክንያት ለበለጠ ጭቅጭቅ እንዳሳለፈው አወቀና በዝ
ምታ ቆየ ። ምሳውን እስኪበላ ድረስ እሳቸውም በዝምታ
ቆዩ ። ልብስ ለውጦ የሚያስፈልገውን ያህል ገንዘብ ይዞ
ለመሄድ ሲሰናዳ እንደገና ጥያቄአቸውን ጀመሩ ፤

“ ጓደኛህም ሆነ ልጅህ ፤ ሁነኛ ሰው ታሞብሃል
ማለት ነው፤ያንተ የሆነ ሰው ደሞ የኔም ነው ። አሁን አብ
ሬህ ሄጄ መጠየቅ አለብኝ ” አሉት ለመነሳት ድንኳን
አልጋ ተመርኩዘው አካላቸውን ሽቅብ እየገፉ ፤

“ እማዬ ለጊዜው የአንቺ መምጣት አያስፈልግም ”

“ አንተ ምንጊዜም ነገሬን ተቀብለህ ጉዳዬ ብለኸው
አታውቅም ። ሆስፒታሉን ክፍሉንም ሰምቼዋለሁ
እመጣለሁ” አሉት በቁጣ ዐይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ ።

“ እኔ ራሴ ማታ እመጣለሁ ። መጠየቅ ከፈለግሽ
ነገ በመግቢያ ሰዓት ሄደሽ ትጠይቂያለሽ ለዛሬ ሁኔታ
ውን ከኔ ትሰሚያለሽና አሁን አትድከሚ” አላቸው እን
ዳይመጡ በመከላከል ፤

“ ባዶ ቤት ታቅፈሽ ማን ተጨነቂ አለኝ ፤ አብሬህ
መጥቼ የሆንከውን አያለሁ ” አሉ ትንሿ ቦርሣቸውን ከጡ
ቶቻቸው መሀል አውጥተው በውስጧ ያለውን ገንዘብ
መጠን እግረ መንገዳቸውን እያረጋገጡ ።

ሻሻቸውን ለማስተካከልና ነጠላ ለመልበስ ወደ
መኝታ ክፍላቸው ሲገቡ መምጣት እንደሌለባቸውና እን
ደቸኮለም ተናግሮ ወጣ ። ለፖሊስ ሊየመለክት ያቀደው
ጉዳይ በሁኔታው ስላላመቸው ለጓደኛው ለመቶ አለቃ
አፈወርቅ በስልክ ሊያሳውቅ ወስኖ ፈጥኖ ተራመደ።
እሳቸው ግን በተባለው ሥፍራ ሊሄዱ የልጃቸው ልጅ
ብለው ያሰቧትን ሊያዩ ወስነው ተነስተው ነበርና መሰና
ዳታቸውን ቀጠሉ ።

ልጅ እግር ሠራተኛቸውን አስከትለው ከግቢያቸው
በር ሲወጡ የመኩሪያ አብሮ አደግ ጓደኛው አገኛቸውና
በሰላምታ ጥቂት አቆማቸው ። የመኩሪያን አለመኖር
ሲነግሩት ለብርቱ ጉዳይ እንደሚፈልገው ስለ ነገራቸው
ሳይወዱ ዘመድ ታሞባቸው ሆስፒታል እያስታመመ መሆ
ኑንና እነሱም ወደዚያው ለመሄድ መነሳታቸውን ነገሩት
የሆስፒታሉን ማንነትና የክፍሉን ቁጥር ካረጋገጠ በኋላ
የመኩሪያ ጓደኛ ተሰናብቷቸው ተመለሰ ። ወ/ሮ ፋኖሴና
ሠራተኛቸው ወደ ሀኪም ቤቱ የሚያመራ ታክሲ ጥበቃ
ቆሙ ።

መኩሪያም ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎችና ብስኩቶች ፤ የብ
ርቱካን ጭማቂ ገዝቶ ወ/ሮ ሙሉ እንዲጠብቁት ኮንገራ
ቸው ሰዓት ጥቂት ቀደም ብሎ ከሆስፒታሉ መግቢያ በር
ላይ ቆሞ ይጠባበቅ ጀመር ። ቀኝ ክንዱን ይዞ ጐተት እስ
ኪያደርገው ድረስ መኩሪያ ሙሉ በሙሉ ልቡ ከሱ ጋር
አልነበረምና መቶ አለቃ አፈወርቅን ሲያይ ደንገጥ አለ ።

ልባዊና የሞቀ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ስለ ታመመችው ልጅ ማንነትና የሕመምዋን ሁኔታ በመግለጽ መኩሪያ ለጠየቀው ጓደኛው አስረዳ ። ጓደኛውም የመጣበትን ዋነኛ ጉዳይ ዞር ወዳለ ስፍራ በመሆን ብቻቸውን እንዲነጋገሩበት ስለ ፈለገ ሆስፒታል በር ላይ እንደቆሙ በሌሎች ልዩ ልዩ የጋራና የግል ሀሳቦቻቸው ላይ ተወያዩ። ወ/ሮ ሙሉ በተባሉበት ሰዓት የመግቢያ ወረቀቱን ይዘው ብቅ ሲሉ መኩሪየ ጓደኛውን ሊሰናበት ተዘጋጀ ። ከመኩሪያ ቀደም ብሎ ወደ ዘበኛው በመጠጋት መታወቂያውን ካሳየው በኋላ ወደ ግቢው ገብቶ ጠበቀው ። መቶ አለቃ አፈወርቅ በመታወቂያው መኩሪያ በፈቃድ ካርድ ወ/ሮ ሙሉን ለውጦ ወደ ማስታመምያው ክፍል አመሩ።

ወ/ሮ ሙሉ ውዴ ሆስፒታል ከገባች ጀምሮ ወንበር ላይ ተጨብጠው ውለው ያደሩ በእንቅልፍ እጦት የተጎሳቆሉ ስለ ነበሩ እሳቸውም ሕመምተኛ መስለው ነበር ። ሌሊቱን በሆስፒታል በማደር ሕመምተኛዋን ልጃቸውን ለማስታመም በጠየቃቸው ጊዜ ሳያቅማሙ ሳይግደረደሩ ተቀብለውት አዳራቸውን በቤታቸው ሊያደርጉ ዘምቢላቸውን አንጠልጥለው ወጡ ።

መኩሪያና መቶ አለቃ አፈወርቅ እየተጨዋወቱ ውዴ ከተኛችበት ክፍል ደረሱ ። ውዴ የከሳውና የገረጣው ሰውነቷ መጎዳትዋን ከመግለጹ በቀር መንፈስዋ መጠናከሩና ሕይወት በውስጧ ማንሰራራቱ ከዓይኖቿ አገላለጥ ይታወቅ ነበር ። የወንድሜ ልጅ ነች ብሎ ከመቶ አለቃ ጋር አስተዋወቃትና እንዴት እንደ ዋለች የሚሰማትን ሕመም ጠየቃት ። እንደ ተሻላትና በጎ እንደሆነች ፈገግታ ባልተለየው አባባል መለሰችላቸው ።

መኩሪየ ካመጣቸው ብስኩቶች ፍራፍሬዎች ከፊሉን አውጥቶ የሚላጠውን ልጦ እየቀነሰና እየቆረሰ እየ

ጨዋወተ ሲያጎርሳት መቶ አለቃ አፈወርቅ የላጠውን ብርቱካን እየመጠጠ በሀሳብ ተውጦ ማዶ ማዶውን አሻግሮ ያይ ነበር ። መኩሪያም ቢሆን የመቶ አለቃ አፈወርቅ መምጣት ያለ ምክንያት አለመሆኑን ስለሚያውቅ የጉዳዩን ምንነት አስቀድሞ ለመገመት ለብቻው የተለያዩ ሀሳቦችን አንስቶ ጥሏል ። ትራሷን አመቻችቶ አስተኛኘትዋን አስተካክሎ በተለይም መርፌው የተነቀለለትንና ያበጠውን እጅዋን አደላድሎ ካስተኛት በኋላ የመስኮቱን ጠርዝ ተደግፎ ውጭ ውጭውን የሚያየውን ጓደኛውን ሊያነጋግረው ከአጠገቡ በክንዱ የመስኮቱን ጠርዝ ተደግፎ ቆመ ።

ሰፋ ላለ ንግግር አመቺ ሁኔታ ስለፈለገ መቶ አለቃ አፈወርቅ በስተቀኝ በኩል ቁስለኛ ልጃቸውን የሚያስታምሙትን ሴት መለስ ብሎ ካያቸው በኋላ ለጥቂት ጊዜ ውዴን እንዲያዩላቸው በትህትና ጠይቆ ቶሎ እንደሚመለሱ አስረድቶ የመኩሪያን እጅ ይዞ ሲወጣ ለውዴም ሳይቆዩ እንደሚመጡ ነገራት ።

የሕመምተኞች መታከሚያ የሆነውን ሕንጻ አልፈው ለሁሉም አገልግሎት ወደሚሰጠው ሻይ ቤት አመሩ። ሲገቡ በስተቀኝ ክንፍ አንድ ሰው ብቻውን ወደ ያዘው ጠረጴዛ በመሄድ ተቀመጡ ። ምን እንደሚጠጣ ሳይጠይቀው መቶ አለቃ ለሁለቱም ቡና ይዞ መጣ ። አብሯቸው የነበረው ሰው ለቆ እስኪሄድ ድረስ ወደ መሠረታዊ ጉዳይ ሳይገባ በዘወርዋራ መንገድ የመጣበትን ጉዳይ ፍንጭ ሊሰጠው ሞከረ ።

አብሯቸው የነበረው ከዐይኑም ከእግሩም አንዳንዱን ያጣው ቁስለኛ በራሱ ሀሳብ ውስጥ ሰርጎ እጅግ በራቀ የራዕይ ጉዞ የሚወዛወዝ ስለነበረ መቶ አለቃ እንደ ቸኮለው ፈጥኖ ሊነሳለት አልቻለም ። መቶ አለቃ ሲጋራውን አቀጣጥሎ አየሩን በትምባሆ ጢስ ጠረኑን ሲለውጠው

CamScanner

ቁስለኛው ሰውም በሱስ ግፊት ተነስቶ ሲጋራ ለመግዛት በአንድ እግሩ እየተራመደ ወጣ ። ያኔ ፊት ለፊት መተያየት እንዲችሉ የተለቀቀው ወንበር ላይ ተቀመጠና መኩሪየን ለጥቂት ጊዜ ትክ ብሎ አየው ። የመጣበትን ጉዳይ እንዲነግረው መኩሪያ አስቀድሞ ጠየቀው ።

"ጓደኝነቴን ቦታ ነፍገኸዋል" አለው መ/አለቃ አፈወርቅ ሲጋራውን በመተርኮሻው ላይ በጭካኔ እያሻት "አልገባኝም" አለው መኩሪያ ፈገግታ በፈጠረው ግፊት ጉንጮቹ ግራና ቀኝ ተሰርጉደው ፤ መንፈሱንም አካሉንም አሰባስቦ ቁም ነገር ሲናገርና ሲያደምጥ እንደሚያደርገው ሁሉ መቶ አለቃ ኮስተር ብሎ በአጭር በአጭሩ የመጣበትን ምክንያት ከነገረው በኋላ በግልጽ ሊየውቀው የፈለገውን ሁኔታ በተወሰኑ ጥያቄዎች ውስጥ አቀረበለት ።

" በመሠረቱ ከአንድ ሰዓት በፊት ደውዬ ከቢሮ አጣሁህ ክሱን እኔው ለመመስረት ተሰናድቼ ነበር ።እንደ እውነቱ ከሆነ የቀረበብኝ ክስ ጩኸቴን ቀሙኝ የሚያሰኝ ነው ። ግልጽ ባልሆነልኝ ምክንያት ከጸብ ቀለበት ውስጥ እንድገባ ሆኖ በዘዴ ሊያጠቁኝ በሚችሉበት ሁኔታ እንድወድቅ ከተደረገ በኋላ የተደበደብኩት እኔ ነኝ። በዚህ ወንጀል መከሰሴ ቢያስገርመኝም ጠንከር ያለ ጠላት እንደሚከታተልኝ የሚያስረዳኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። " አለ መኩሪያ በጥቅሉ ከጥቂት ቀናት በፊት የደረሰበትን ምክንያቱ ግልጽ ያልሆነ የጥቃት ሁኔታ አንድ በአንድ በዓይን ህሊናው እያስተዋለ ።

መቶ አሊቃ ግን ጭብጥ የሆኑ ማስረጃዎችን ወይም ጠቋሚ ሀሳቦችን የሚሻ በመሆኑ ያጋጠመውን ሁኔታ ሳይቀናንስ እንዲያስረዳው ጠየቀ ። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሆነውን ሁሉ መኩሪያ ካስረዳው በኋላ የመ/ቤቱን

ባልደረባ አሰለፈችን እስከምን ደረጃ እንደሚያውቃት መቶ አለቃ ረጋ ብሎ ጠየቀው ።

ይህ ጥያቄ ራሱን መታውና በተጠቀሰው ስም የሚጠሩትን የመሥሪያ ቤቱን ሰዎች መኩሪያ ለማስታወስ ሞከረ ። ሶስቱንም አሰባቸው ።

የመዝገብ ቤትዋ አሰለፈች ፤
የራሱ ጸሐፊ አሰለፈች ፤
የጽዳት ሠራተኛዋ አሰለፈች

ስለ የትኛዋ አሰለፈች እንደሚጠይቀው ስላላወቀ እንደ የሥራቸው ድርሻ ሴቶቹን ገለጸለት ። መቶ አለቃ ግን ያተኮረው በጽዳት ሠራተኛዋ አሰለፈች ላይ ነበረና ከአሰለፈች በዳኔ ጋር ስላለው ቀረቤታ እንዲገልጽለት ጠየቀው ።

" ቀረቤታ ግንኙነት ስትለኝ ሥራን በተመለከተ ወይስ ከዚያ ውጭ " አለው መኩሪያ መቶ አለቃም ሥራው ከሚፈጥረው ግንኙነት ባሻገር ባለው ግላዊ ዕውቂያ ላይ ስላለ ሁኔታ ለማወቅ የፈለገ በመሆኑ ያለ አንዳች ጭንቀት እውነቱን እንዲነግረው ጓደኝነቱን ተመርኩዞ ጠየቀው ።

መኩሪያም በውስጡ ያንሰራራው ቁጣ በንግግሩም ላይ ተደረበና ታወቀ ።

" ከጽዳት ሠራተኛ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ይኖረኛል " አለው መቶ አለቃን

" እኔም የምጠይቀው ይህንኑ ነው" አለ መቶ አለቃ ሌላ ሲጋራ እያቀጣጠለ ። የተጠቀሰችውን ሴት ለመተዋወቅና ለመቅረብ ቀርቶ በአግባቡ ለመተያየት

እንኳ የሥራቸው ጠባይ እምብዛም ስለማይፈቅድ በሌለ ጠብና ፍቅር ፣ ዕውቀትና ፣ ግንኙነት ላይ የሚናገረው ጠፍ ቶት ዝም አለ ። የጽዳት ተግባሯን በአብዛኛው ከሥራ መጀመሪያ ሰዓት በፊት ፈጽማ የምትወጣዋ ሴት በምን ሁኔታ ጣጣዋ ከሱ ጋር እንደተያየዘ ቢያስበው ቢያስበው አልከሰትልህ አለው ።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ክሱ የተመሠረተበትን ነጥብ እንዲነግረው መቶ አለቃን ቂጣ በተጫነው መንፈስና ግራ መጋባቱን በሚያስረዳ ሁኔታ ጠየቀው ፤ "ክሱ የተመ ሠረተው በሁለት ዐቢይ ነጥብ ላይ ነው" ሲል አስረዳው ።

"1ኛ/የሴትዬዋን እጮኛ እቤታቸው ድረስ በመሄድ በመደብደብህ ፤ በድብደባ ወንጀል ፤ ክስ

2ኛ/ ለዚህ ውጤት የደረሰው ከሴትዬዋ ጋር ያለህ ስውር ግንኙነት በሁለት ሰዎች መካከል ሰላምና አን ድነት እንዳይፈጠር በማድረጉ ተብሎ" አለው ። አንድም እውነት የሌለበት ከንቱ ውንጀላ ከንቱ ወሬ መሆኑን እየደጋገመ በመናገር መኩሪያ ክፉኛ በንዴት ተቅበጠ በጠ ። መቶ አለቃ ግን ረጋ ብሎ እንዲያስረዳው ገስጦት ከሳሽ ማስረጃ ብሎ ያቀረባቸው ጭብጦች እንዳለ አረጋ ገጠለት ።

" የእኔን በሁለቱ ሕይወት ውስጥ መግባት የሚያ ሳምን ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም " አለ መኩሪያ ።

" ቀርቧል " አለው መቶ አለቃ አጥብቆ

" ምን ዓይነት "

" በጽሁፍ ያለ ሀተታና ፎቶግራፍህ ጭምር "

" የኔ ፎቶግራፍ ? የኔ ጽሁፍ ?"

" አዎ"

መቶ አለቃ አፈወርቅ ራሱን የሚያውቀውን ያህል መኩሪያንም ጠንቅቆ ከነባህሪው ድርጊቱና ፍላጐቱ የሚያ ውቀው በመሆኑ መኩሪያ ባላወቀው የነገር ማጥ ውስጥ መግባቱን በመጠርጠር ሲያስብ ሲመራመር ሲከታተል ነገሩ ከእርሱ ቁጥጥር ሥር እንዳይወጣ አስፈላጊውን ክት ትል ሲያደርግ ሰንብቷል ። ተጐዳሁ ያለው ከሳሽና ሴት ዬዋም በቅድሚያ የሚገባውን ሕክምና እንዲያገኙና የከሳ ሽም ምስክሮች እንዲቀርቡ የአግባቡን መመሪያ ከሰጠ በኋላ ለምስክሮች መጥሪያ ለመውሰድ እንደገና ከሳሽ ሲመጣ ነገሩን በእርቅ ለማሳጠር እንዲቻል ጥረት አድር ጐና አስተካክሎ አሰለፈችን አነጋግሮና ጭብጡን ተረ ድቶ ስለነበር ዋናው አመጣጡ መኩሪያ በቀነ ቀጠሮው ከተመረጠው ሥፍራ ተገኝቶ ጸብና ቅሬታን በእርቅ ለመ ፍታት እንዲቻል ለማሳወቅ ነበር ።

መኩሪያ ግን ነገሩ እንቆቅልሽ ሆኖበት፣ በተለይም ማስ ረጃ ስለ ተባለው ፎቶግራፍና ጽሁፍ ጉዳይ አጥብቆ አሰ ላሶለ ። ምናልባት ህሊናውን ስቶ ካላደረገው ለጽዳት ሠራተኛዋ አሰለፈች ምስሉን በማታወሻነት የሰጠበት ስሜቱን በጽሁፍ የገለጸበት ሁኔታውም ፤ ጊዜውም ፤ ጭራሽ ትዝ አልልህ አሉት ። ራሱን ወደሚጠራጠርበት ደረጃ ሊደርስ ቃጣው ። የጓደኛውን መበሳጨትና ግራ መጋባት የተረዳው መቶ አለቃ ነገሮቹ የተቆላለፉበትን ዋነኛ ገጽታ ሊያሳየው ከሞከረ በኋላ ዝርዝር ሁኔታውን በእርቁ ቀነ ቀጠሮ እንደሚሰማው አረጋግጦለት በተባ ለው ቀን ከተመረጠው የእርቅ ሥፍራ እንዲገኝ ገልጾለት የመጣበትን ጉዳይ ቋጭቶ ከተቀመጠበት ተነሣ ።

ተያይዘው ሕመምተኛዋ ውዴ ወደ ተኛችበት ክፍል አመሩ ። ከሣሽ ሆኖ የቀረበውንም የመ/ቤቱ ሰው ማንነት ከሰማ በኋላ በአሠራር የሚግባቡ፤ በአክብሮት በትህትና

የሚተያዩ ከመሆናቸው በቀር ለዚህ መሰሉ ወንጀልና ክስ የማያስበው የሚሞክረው አለ መሆኑን ደጋግሞ መኩሪያ ሊገልጽለት ሞከረ ። መቶ አለቃ ደግሞ ይህን መሰሉን የዋህ አመለካከቱን ማስወገድ እንዳለበት ከቁጣ ጋር ገለጠለት። እውነተኛ ባህርይን ከሰዎች ውስጥ ለማግኘት በጥልቀት መመርመርና በጊዜ በድርጊት መለካት አስፈላጊ እንደሆነ አስረዳው ። ዓለምና ዓለማዊ ኑሮ አብዛኛው ሽፋኑ ሀሰትና ሀሰት የሚፈጥሩት እውነት እንደሆነ ሙያው ካስጨበጠው እውነታ እያስገነዘበ መንፈሱ እንዲሰባሰብና እንዲረጋጋ መከረው ። የመኩሪያ መደነቅ ግን ብስጭት እየበረዘው የግንባሩ ስሮች ቀስ በቀስ ከቆዳው በላይ ፈጠው ታዩ ።

መኩሪያና መቶ አለቃ እንደደረሱ ከውዴ ክፍል ሊገቡ አልቻሉም ። በተኛችበት እየመረመሩ ፤ ከቀን ወደ ቀን የተመዘገበውን የጤናዋን ሁኔታ እየተነጋገሩበት ሀኪሞቹ ክፍሉን ይዘውት ነበር ። ምርመራቸውን ፈጽመው ሲወጡ የውዴ አስታማሚ ማን እንደሆነ ከጠየቁ በኋላ የታዘዘውን የትርፍ አንጀት ህመም ኦፕራሲዮን ለማድረግ የሚያጣድፍ ሁኔታ አሁን ባለችበት ደረጃ አለመኖሩንና ሕመምዋን በመድኃኒት መከላከልና ማዳን እንደሚቻል ሆኖም በሆስፒታል ተኝታ የሀኪሞች ክትትል እንደሚያስፈልጋት ለመኩሪያ ገለጹለት ።

ይህ የውዴ ጤና መሻሻል ደግሞ አንድ ዓይነት የእፎይታ ስሜት ስለዘራበት ከነበረበት የመንፈስ ውጥረት ረገብ አለ ። መኩሪያና መቶ አለቃ ተከታትለው ሲገቡ ከተኛችበት ቀና ብላ ግድግዳውን ተደግፋ በግሎኮስ መርፌ ያበጠውን እጅዋን እያሻሸች አገኟት የመንፈስ ጥጋብና ተስፋ አጠንክረዋት ስለ ነበር ከመሰንበቻዋ ጊዜ ሁሉ ነቃ ብላለች ። ጤንነትዋ መሻሻሉንና ከጥቂት ጊዜ ህክምና

በኋላም ልትወጣ እንደምትችል ሀኪሞቹ እንደ ነገሩት ደስ እያለው ገለጸላትና የምታሻሸውን እጅዋን አንሥቶ እያየ በአካሏ ክሳት ልቡ ተነካ ። እሷ ግን የጤናዋን መመለስ ስትሰማ የማትሪክ ውጤትዋን ሁኔታ አስባ መልካም ተስፋና ምኞት ወዲያው ማሰላሰል ጀመረች ።

መኩሪያና ውዴ ሲነጋገሩ አልጋዋን ሲያስተካክልና ወደ ሽንት ቤት ለመሄድ ስትነሣ ጫማ ሲያቀርብላት ፤ ደግፎ ሲያራምዳትና እንደገናም አልጋዋ ላይ ሲያወጣት በአትኩሮት እየተመለከተ መቶ አለቃ ብቅ ስልብ ኩሚልበት ካንድ ሀሳብ ጋር ክፉኛ ትግል ይዞ ነበር ። ሊጨብጠው አልቻለም ። አስተያየቱ የጠነከረውም ውዴ ላይ ነበርና ሁሉቱንም እጆቹን ኮሱሪው ኪስ ኮቶ ብልጭ ድርግም እያለ የሚያስቸግረውን ሀሳብ ለመያዝ ሂሊናው ከወዲያ ወዲህ ሲባዝን እንዳፈጠጠባት ለረዥም ጊዜ ቆየ ። የውዴን አባት ገጽታ ለማሰላሰል እየሞከረ ነበር።ውዴን ግራ እንደገባት ያህል መኩሪያንም ገርሞት ምን እንደሆነ ጠየቀው ። አካሉ እንጂ መንፈሱ ለአጭር ጊዜ በዚያ ክፍል እንዳልነበረ ገልጾላቸው የውዴን እጅ ጨብጦ ጭንቅላቷን ደባብሶ ጤና ተመኝቶላት ሲወጣ መኩሪያ ለጥቂት ርቀት ተከትሎ ሸኘው ። መቶ አለቃም ኮቻለ ተመልሶ እንደሚመጣ ነግሮት በችኮላ የፎቁን ደረጃዎች ወረደ ።

የግቢውን በር ሲወጣ በስተቀኝ ግዙፍ ሰውነታቸውን ከትልቅ ድንጋይ ላይ አሳርፈው ጥላቸውን ተመርኩዘው ፤ ሠራተኛቸው ከኋላቸው ቆማ አያት ። የመኩሪያ እናት ነበሩ ። ሰላምታ ሊሰጣቸው ጐንበስ ሲል አዩት። የተመረኮዙትን ጥላ ተደግፈው ለመነሣት ሲቸገሩ ስላዩ ደግፎ አነሣቸው ። ከመጡ መቆየታቸውን ሊገቡ አለመቻላቸውን እያማረሩ ነገሩት ። አነጋገራቸው የስሞታ ዓይነት ነበርና መቶ አለቃ ባለው ስልጣን የሚያስገባቸው

መሆኑን ቅንጣት አልተጠራጠሩም ። በሽተኛ መጠየቂያው ዕለት በማግስቱ መሆኑን አስረድቷቸው የታመመችው ልጅ በጣም እንደ ተሻላትና በነገው ዕለት መጥተው ሊያይዋት እንደሚችሉ ሲያስረዳቸው የተደገፉትን ክንዱን ገፍተው ገላመጡት ። ሲሆን ባለው ሥልጣን አለበለዚያ ደግሞ ለምኖም ቢሆን አስተዛዝኖ እንዲያስገባቸው ማድረግ ሲገባው ያን ሁሉ መንገድ አቋርጠው መጥተው፤ ያለአንዳች ፋይዳ ተመለሱ ስላላቸው ተናደዱ ። ወ/ሮ ፋኖሴ ልባቸው እጅግ የከጀለው የታመመችውን የልጃቸውን ልጅ ለማየት ነበርና ተመልሶ መሄዱን ክፉኛ ተቃወሙት ። መቶ አለቃም የሚያደርገው ጠፍቶት ጥቂት ጊዜ በዝምታ ቆየ ። ከአስታማሚዎች አንዱ ወደ አጥሩ ተጠርቶ መጥቶ ሰዎች አነጋግሮ ሲመለስ መቶ አለቃም መኩሪያ የሚገኝበትን የክፍል ቁጥር ነገሮ እንዲጠራለት በትህትና ጠየቀው ። ጥቂት ቆይቶ የመኩሪያን መምጣት በርቀት ካየ በኋላ እናትና ልጁ እንዲገናኙ ትቷቸው ተሰናብቶ ሔደ ።

ወ/ሮ ፋኖሴና መኩሪያ ብዙ ከተነጋገሩ በኋላ የያዙትን ሁለት ኪሎ ብርቱካን አቀብለውት በማግስቱ በስምንት ሰዓት ሊመጡ ተወስኖ መለስ ሲሉ ወ/ሮ ሙሉ መኩሪያን ሲጠሩት ሰሙ ። ቆም ብለው ወ/ሮ ሙሉን ከእግር እስከራሳቸው አዩዋቸው ። በዕድሜ የከበዱና የተጎሳቆሉት ሴት ለመኩሪያ ያዘጋጁትን እራትና ሌሊት የሚለብሰው አንድ ጋቢ በላስቲክ ከረጢት በግንቡ አጥር አሾልከው ሲሰጡት በትኩረት ተመለከቱ ። መኩሪያም የውዴ ኦፕራሲዮን መሆን እንደቀረና በህክምና ብቻ እንደምትረዳ መወሰኑን ሲነግራቸው ወ/ሮ ሙሉ ፈጣሪያቸውንም መኩሪያንም ሲመርቁ አደመጧቸው ።

ጠዋት በማለዳው መጥተው እንደሚተኩት በትህትና እየተናገሩ አሁንም አሁንም እየመረቁት ተሰናብተው ወደ መንደራቸው ሲያቀኑ ወ/ሮ ፋኖሴ ከተል ብለው

" ማን ታመመብዎ እሜቴ " አሏቸው ወ/ሮ ሙሉን

" ልጄን አሞብኝ ነው እሜትዬ "

" ልጅዎ ልጅዎ ፤"

" አዎ ልጄን"

" ሕፃን ናት ከፍ ያለች ፤"

" እረ እሷስ ደርሳልኝ ነበር የአስራ ዘጠኝ ዓመት ልጅ ናት"

" መኩሪያ የሚያስታምማት እሷኑ ነው"

" እኒህ ያሁኑ ?

" አዎ ሳህንና ጨርቅ ያቀበሉት "

" አዎ ዛሬን አብረዋት ሊያድሩ ነው ፈጣሪ እንደ ርህሩህነታቸው ምርኩዝና ድጋፍ ይሁናቸው እንጂ "

" በሉ እግዚአብሔር ይማርልዎት " አባባላቸው ቁጣ ነበረበት ።

ወ/ሮ ሙሉን ከቆሙበት ትተዋቸው ሄዱ ። ወ/ሮ ሙሉም ግራ ገብቷቸው ወደ ናዝሬት ት/ቤት የሚወስደውን ጥርጊያ መንገድ አቋርጠው ታክሲ ለመያዝ ከአውቶቡስ ፌርማታ ደርሰው እስኪቆሙ የመኩሪያን እናት በዓይኖቻቸው ተከተሏቸው። መኩሪያም በግራና በቀኝ እጁ ያንጠለጠለውን እቃ እንደ ያዘ ወደ ማስታመሚያ ክፍሉ የሚያወጣውን ደረጃ በእርጋታ ሽቅብ እየ

ወጣ ለክስ ያበቃውን ጉዳይ እንደገና ማሰላሰል ጀመረ ።
በተፈጥሮው ምስሉን ለሰው መስጠት ፤ በተለይም ለሴት
መስጠት እንደማይወድና ይህን ከፍላጎቱ ውጭ የሆነውን
ድርጊት እንዴት ለማስረጃነት ኣንደ ተጠቀሙበት ሊገ
ባው አልቻለም ። በተለያየ ዘዴ ግን ከእጁ ሊወጣ እንደ
ሚችል ገምቶ ልዩ ልዩ ጥርጣሬዎችን ቢዳስስም እውነተ
ኛውን ሁኔታ በወቅቱ መስማት እንደሚሻል ደምድሞ
ተወው ።

የጉዳዩ አስኳል የሆነችውን ወ/ሮ አሰለፈችን በዐ
ይኑ ሀሊናው ኢየት ። ረዘም ቀጠን ያለች ሴት መሆንዋን
አረጋገጠ ። አንዳንድ ሠራተኞች እንደሚያወሩላት አለባ
በስዋ አካሄድዋ አነጋገርዋ የሚባለውን ሊመዝነው አል
ቻለም ። አንዳንዴ ማልዶ ሲመጣ የሚያያት ጐንበስ ብላ
ወለል ስትፈትግ ጠረጴዛና ወንበር ስትወለውል መስታ
ወት ስታሽ በመሆኑ ከዚህ ሥራ ውጭ ተነጥሎ የሚወሳ
ሁኔታዋን አጣው መልኳም አልከሰትልህ አለው ። ሁሉ
ንም ነገር በእለተ እርቁ የሚሰማውና የሚያየው በመሆኑ
ሀሳቡን ለዚያው ጊዜ ትቶ ነቃ ብሎ ተራምዶ ከማስታመ
ሚያው ክፍል ደረሰና ገባ ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ መቶ አለቃ አፈወርቅ በሩን
አንኳኩቶ ሲገባ ፤ ውዴና ራሱን የተፈነከተው ሌላው ሕም
ምተኛ ልጅና አስታማሚው ፤ መኩሪያም አልተኙም ።
አስታማሚዎች የጋራ የሆነ ወሬ ይዘው እየተቀባበሉ ይጫ
ወታሉ ። ጭንቀት የተገሰሰበት በሽተኞቹ ያገገሙበት
ክፍል በመሆኑ ለአንዱ የመጣውን ለሌላው በማካፈል
በመረዳዳትና በመተሳሰብ የሚደረገው መተዛዘን ቤተሰብ
አስመስሏቸዋል ። መቶ አለቃም ለመኩሪያ የሌሊት ልብ
ስና ጋቢ ከሆቴል ቤት ያስቋጠረውን እንጀራ ለራቱ ይዞ
ነበር ። የመጣውን ምግብ አንዱ ሌላውን እያጐረሰ የተ

ገኘውን ሁሉም በአንድነት ከተቃመሱ በኋላ መቶ አለቃ
አፈወርቅ ትቷቸው ሲሄድ ህሙማኑ ልጆች በአልጋዎ
ቻቸው ላይ አስታማሚዎቹ አልጋ ተደግፈው በየወንበራ
ቸው ላይ እንደሆኑ አሸለቡ ።

ነጋ አልነጋ ብለው ጐህ እንደ ቀደደ ስለመጡ መኩ
ሪያ ወ/ሮ ሙሉን ተክቶ ወደ ቢሮው ሔደ ። ፀሐፊው አሰ
ለፈች አልገባችም ። ቢሮውም አልተወለወለም ። ዘወ
ትር ብሩህ ቀለም ያለው አንድ ዝንጣፊ ጽጌረዳ የምትቀ
መጥባት አንገተ ረጅም ጠርሙስ የጠወለገችና ቅጠሎችዋ
የደረቁ ጽጌረዳ እንደያዘች ተቀምጣለች ። የጽዳት ሰራ
ተኛዋን የአሰለፈችን ከሥራ መቅረት በነዚህ ሁኔታዎች
አረጋገጠ ። እጆቹን እኪሱ ከትቶ ከወዲያ ወዲህ በቢ
ሮው ውስጥ ተመላለሰ። የመጀመሪያው የስልክ ጥሪ ጮኸ።
መነጋገሪያውን አንስቶ ረጋ እንዳለ ለጥቂት ደቂቃዎች
ተነጋገረ ። መኝታ ስላልተመቸው የረባ እንቅልፍ አል
ተኛም ነበርና በጥዋቱ እንደከበደው በንግግሩ አውቆ
በታል ። ዕርቁ ከሥራ ሰዓት በኋላ እንዲሆን በመወሰኑ
ከሱ ቢሮ ድረስ እንዲመጣ ነግሮት መቶ አለቃ አፈወርቅ
ተሰናበተው ። መኩሪያም ከወንበሩ ላይ አረፍ አለ ።

ሰዓቱ አልገፋ አለው ። አለወትሮው ተቅበጠበጠ ።
የቡና ፍጆታው ከፍ ብሎ ዋለ ። ከሳሹ የመ/ ቤቱ ባል
ደረባና የጽዳት ሠራተኛዋ አሰለፈች ዋቢ ሆና ፊት ለፊት
እየተያዩ ክስና ውቅስ የሚያሰሙበት ሰዓት ናፈቀው ።
ናፍቆቱ ደግሞ የሚሰንግ ናፍቆት ሆነበት ። ከሁሉም
ከሁሉም አሰለፈች በዳኔ በምን ተኡምር ምስሉንና ጽሁ
ፉን አግኝታ ለኤግዚቢት እንዳበቃችው ለማወቅ ጓጓ ።

ጊዜው ደረሰና ከሥራ ሰዓት በኋላ ወደ መቶ አለቃ
አፈወርቅ ቢሮ በረረ ። በሩን አንኳኩቶ ሰላምታ ሰጥቶ

ሲገባ በርከት ያሉ ሰዎች በክፍሉ ውስጥ አየ ። ከአንድ ሁለቱ በቀር ሌሎቹን ያውቃቸዋል ። መቶ አለቃ የወትሮ ሥፍራውን እንደያዘ ነበር። ተቀጣጥለው የረዘሙት ሁለት ጠረጴዛዎች በመሀከላቸው ተዘርግተው ፊት ለፊት የተቀመጡትን ሰዎች በመጠኑ አራርቋቸዋል ። በስተቀኝ ካለው ረድፍ ሰው ያልተቀመጠበትን ወንበር አይቶ አልፎ ተቀመጠ ።

መቶ አለቃ አፈወርቅ ኮምጨጭ ባለ አነጋገርና አስተያየት በዝምታ የተዋጠውን ክፍል ድምጽ አፈሰሰበት። ሰላምና ሀጋዊነት ከግለሰብ እስከ ሕብረተሰብ ለሚኖረው የኑሮ ቁርኝት አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ማሳሰቢያ ከሰጠ በኋላ በመኩሪያ ላይ ስለተመሠረተው ክስ ግልጽ የሆነ ሀሳብ መጨበጥ እንዲቻል ነገሩን በዝርዝር ማየት እንደሚያስፈልግ አስረዳ ።

ተከሳሹ መኩሪያም መንፈሱ ሲረጋጋና አካሉ ሲዝናና መንጽሩን ተገን አድርጐ የተቀመጡትን ሰዎች ቃኘ። ከሳሹ የመ/ቤቱ ባልደረባና አሰለፈች በዳኔ ጐን ለጐን ተቀምጠዋል ። ልብ ብሎ ተመለከታት ። አጋጥሞት ነጋ ጠባ ቢያያትም ያዩዋት የመ/ቤቱ ሠራተኞች የተናገሩላትን ሁኔታዋን በግልጽ አገኘው ።

የአለባበስዋ ስርዓት ገረመው ። ፈዘዝ ያለ የወይን ጠጅ ቀለም ያለው አንገተ መልካም ሙሉ ቀሚስ ለብሳለች ። የቀሚስዋን ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ሁለት ተንጠልጣይ ፈርጦች ከጆሮዋ ላይ እንጠልጥላ በተንቀሳቀሰች ቁጥር ብርሃን እየፈነጠቁ ያምራሉ ። ሸብ ያደረገችው ነጣ ያለ ቀበቶ የወገቧን ቅጥነት ብቻ ሳይሆን የዳሌዋን ስፋት ሆን ብሎ ያሳያል ። ደረብ ያደረገችው ወፍራም ኮትና ቦርሣዋ ያደረገችው ነጠላ ጫማ ደብዘዝ ያለ ነጭ

ቀለም አለው ። በተከፈተው መስኮት ተንደርድሮ የሚገባው ንፋስ የሚያውደው የጥሩ ጠረን ዑደት ከሷው የተገኘ እንደሆነ ገመተ ። ባልጠበቀው አጋጣሚ ተገናኙና እሱንም እንደ መሥሪያ ቤቱ ሰዎች አሰለፈች ገረመችው።

አልፎ አልፎ ዐይኖቿን ወርወር አድርጋ ከመነጽሩ በስተጀርባ ያሉትን ዐይኖቹን ለመያዝ ብትሞክርም ያያታል እንጂ ልታየው አልሆነም ። ከሳሽ አሰፋ በልሁ ግን የፖሊስ ጋዜጣ በእጆቹ እየደባበሰ መቶ አለቃ የሚሰጠውን ማሳሰቢያ በአንክሮ የሚያስተውል ይመስላል ።

ወ/ት አሰለፈች “ አለ መቶ አለቃ ፤ በለሰለሰ ድምጿ “ አቤት ” አለች ። “በመኖሪያ ቤትሽ ውስጥ በመገኘት አቶ መኩሪያ የድብደባ ወንጀል ፈጽሟል የሚለው ክስ እንደምታይው ሰብስቦናል ፤ ለዚህ ድርጊት መንስኤው ምን እንደሆነ ፤ በተለይም ከአቶ መኩሪያ ጋር ያላችሁ ግንኙነትና እውቀት ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው እዚህ ላሉት ሽማግሎች አስታራቂዎች ለሁላችንም ብትገልጭልን ” አላት በአክብሮት ። ወዲያውም ወገቡን ከወንበሩ አስደግፎ ቀና ብሎ ተቀመጠ ።

አንገቷን እንደደፋች ወ/ትዋ ብድግ አለች ። ተቀምጣ እንድትናገር መላልሶ ስላሳሰባት ተመልሳ ቁጭ አለች ። ያንቀሳቀሰችው የአካባቢው አየር በየሰው አፍንጫ ጣፋጭ ጠረንዋን ረጨ ።

የመኩሪያ ልብ ክፉኛ ተወጠረ ። ምን ልትል ይሆን የሚለው ጭንቀቱ ቀሰፈው ። አፏን እንደ ማንቀሳቀስ አለችና ፈገግታ የወረረውን ፊቷን ወደ መኩሪያ መልሳ አየችው ። አጸፋውን ባይመልስም ልቡ የተሰነጠቀ ያህል ተሰማው ። ውስጡን የሚያውቀው እሱ ብቻ በመሆኑ ለሰው ትዝብት ባለመጋለጡ ደስ አለው ። ወደ መቶ አለቃ

መለስ አለችና ፤ “ ጋሽ መኩሪያን አውቀዋለሁ ። የማውቀውም ከልጅነት እስከ እውቀት ነው።” አለች ። ትሁትና በተላበስ ፈገግታ እንደ ፈካች መለስ ብላ መኩሪያን አየችው ። በድንጋጤ አፉን እንደ መክፈት ብሎ ነበር ። ሁኔታው አሳቃትና ይበልጥ ዘርዛራ ጥርስዋን አሳየችው ። መኩሪያ ደንግጦ ነበርና አጸፋውን አልሰጣትም ። ፈገግታዋን ይዛው ተመለሰች ። ትኩረትዋን ወደ መቶ አለቃ በማድረግ ንግግርዋን ቀጠለች ።

“ ጋሽ መኩሪያ አብሮኝ ያደገ ጣኦቴ ነው ። በህሊናዬ ውስጥ ምንጊዜም የሚያበራ የማይጠፋ መብራቴ ነው ። ኑኔም እንዳልረሳው ያደረገው ራሱ ነው ። በልጅነት አእምሮዬ በልጅነት አንደበቴ ይሉኝታና ፍርሃት በኔ ላይ ኃይል ባልነበራቸው ሰዓት የተከለው የሀሳብ ፍሬ አልመከነም ። ከት/ ቤት ሲመጣ ፤ በኋላም ሥራ ይዞ ከሥራ ሲመለስ ሰዓቱን ለይቼ አውቄ ከአጥርና በር ላይ ተጣብቄ እየጠበቅሁት ሲመጣ ፈንድቄ እቀበለው ነበር ። ጐረቤት ነበርን ከረሜላና ብስኩት አስለምዶኝ ነበርና እጅ እጁን እያየሁ ኡናፍቀው ነበር ። ከነማማ ፋኖሴ ቤት ያጠመደ አያጣኝም ። እሳቸውም የልጄ ሚስት እያሉ ስለ ሚወዱኝ እወዳቸው ነበር ። ” ጥቂት ዝም አለች ። የሷ ፊት በቅሬታ ወይቧል ። አሰፋ በልሁ አቀርቅሯል ። መኩሪያ አትኩሮ ይመለከታታል ። የመቶ አለቃ ዓይኖች ከመኩሪያ ወደ አሰለፈች ከአሰለፈች ወደ መኩሪያ ይመላለሳሉ ። ሌሎቹም በተመስጦ ያዳምጣሉ ።

ግንባሯን ከስክሳ አስተያየቷን ስላ ያልተቅለሰለሰ ንግግርዋን ቀጠለች ። “ ጋሽ መኩሪያ ወደ ሱቅ ልኮኝ ስመለስ ፤ ካልሲውን ሳጥብለት ሲያመሰግነኝና ሲያጫውተኝ “ የኔ ሚስት አንቺ ነሽ አላንቺ ሌላ ሴት አላገባም ፤ ጠንክረሽ ተማሪና ፤ ኮሌጅ ድረሽና ዲግሪሽን ስትቀበይ

በሠርግ በቬሎ እንጋባለን ” ይለኝ ነበር ። ይህንን ቃል ኪዳን የከተበው አእምሮዬ በእርግጠኛነት ተቀብሎት ነበርና ከልጅነት እስከ እውቀት የማደርገው ነገር ሁሉ እሱን ለማስደሰትና እሱ ካለኝ የትምህርት ደረጃ ለመድረስ ነበር ። በሥራ ምክንያት ተቀይሮ ጉርብትናችንን ትቶ በኋላም አገሩን ለቆ ውጭ አገር ሲሄድ ብዙ አልቅሼ ብዙ ታመምኩ ። ብዙ ዓመትም ተለያየን አስራ ሁለተኛ ንም ማለፍ አልሆነልኝም ። ለሦስት ዓመታት ያህል እየ ዞርኩ ስራ ስፈልግ አሁን ባለሁበት መ/ቤት ውስጥ ድን ገት አየሁት ። ጠይቄ እንደ ተረዳሁት ከውጭ በቅርብ መጥቶ ሥራ እንደ ጀመረ አወቅሁ ። ላለኝ የትምህርት ደረጃ የሚመጥን ሥራ ባይሆንም የጽዳት ሥራውን ተወዳድሬ ተቀጠርኩበት።እኔ ባውቀውም እስከ ዛሬ እሱ አላወቀኝም ። ከማገኘው ደሞዝና ከምሠራው ሥራ ይልቅ የሚያስደስተኝ ነገር በየቀኑ እሱን ማየት ነው ። ይህ እንግዲህ አቶ መኩሪያን ምን ያህል ታውቂዋለሽ ለሚለው ጥያቄ የሚበቃ መልስ መሰለኝ ” አለች ፤ እንደገና ፈገግታ በገጽታዋ ላይ እያንሠራራ ።

ሁሉም አፉን ከፍቶ በተመስጦ ያዳምጣት ነበርና የሁሉም ዝምታ ንግግርሽን ቀጥይ የሚላት መሆኑን በመገንዘብ ቀጠለች ። “ በማስረጃነት የቀረበው ጽሁፍና ፎቶግራፍ ደግሞ የጽዳት ሥራዬን ሳከናውን ከቢሮው ጠረጴዛ ላይና ከቆሻሻ ማጠራቀሚያው ቅርጫት ውስጥ ያወጣሁት ነው ። በተለይ ያገኘሁት ጽሁፍ የኔን ስም ጠቅሶ የናፍቆት ሀተታ አዝሎ የተጻፈ ዐይነት ስለነበረ ፤ የተጨባበጠውን አስተካክዬ ለኔም የተጻፈ መስሎኝ ተደስቼ ወስጄዋለሁ ። ባለሁበት ሁኔታ ቢያስታውሰኝም አልረሳኝም ብዬ አመንኩ ።

መለስ ብላ መኩሪያን አየችው ። እሱ ግን ኩት ብሎ ሊስቅ ከጅሎት ነበር ። እንዳንዴ ግብታዊ ስሜት እየወ ጠረው ድርሰት ቢጤ ለመጫር እየጀመረ ማጣፊያው ሲያ ጥርበት ጅምሩን ሁሉ እየጨባበጠ እየቦጫጨቀ የሚጥል በመሆኑ የጠቀሰችው ወረቀት በዚህ ሁኔታ የተጣለ ፤ ነገር ግን አጋጣሚው አሳምሮ ለማስረጃነት ያበቃው እን ደሆነ ሰዎቹን ሊያስረዳ ፈለገ ። ሆኖም ንግግርዋን ሊያ ቋርጣት አልፈለገምና ነጥቡን ይዞ ማድመጡን ቀጠለ ።

“ ግብግቡ እንዴት ተፈጠረ ለሚለው ” አለች ምክ ንያቷን ልትስረዳ ፤ “ እወድሻለሁ ይለኛል ። አንጋባም ይለኛል ። አለች እጐኗ ወደ ተቀመጠው አሰፋ በልሁ ጥቂት እንደመዞር ብላ ። ለቅርብም ሆነ ለሩቅ ጓደኝ ነት ከጠየቀኝ ቆይቷል ። ሀሳቡን ተቀብዬ ቃል አልሰጠ ሁትም ሌላም የሰጠሁትም የለም ። ብዙ ጊዜ የምጠብቀው የምናፍቀው ማን እንደሆነ እየወተወተ ሲያስቸግረኝ የጋሽ መኩሪያን ጉዳይ አንስቼ ነግሬዋለሁ ። እሱ ግን በተለይ ጠጥቶ በስካር ተደፋፍሮ በመጣ ቁጥር “ እሱ እኮ ከነመ ፈጠርሽ የሚያውቅ ሰው አይደለም ። በሚገባ ተከታትዬ ዋለሁ ። ስላንቺ አንስቶ ቃል የተናገረበት ጊዜ የለም ። በዓይኑም ሙሉ አይቶሽ አያውቅም እያለ ልቤን ስለሚያ ቆስለው ለመበቀል እያልኩ በምናገረው አባባል እጅግ ይቀና ነበር ።

በተፈጥሮው ብዙ መናገር ስለማይወድ ፤ የግሉን ጉዳይና ምስጢሩን ለራሱ በመያዙ እንጂ ፤ መታየትም ስለማይ ፈልግ እንጂ ፤ እንዳልናቀኝና እንደሚወደኝ አረጋግጬ እናገር ነበር ። በዚህም ሀሳቡን ለሁለት ከፍየበታለሁ ”

ባለፈው ሰሞን ታዲያ በኃይለኛ ስካር እየተነዳ መጥቶ በማስፈራራትና በመደባደብ ሀሳቡን እንድቀበለው ሞከረ ፤

ሰዎች ገላገሉንና ሄደ ። እንደገና ሲነጋጋ መጥቶ ከመኩሪያ ጋር ያለሽ ግንኙነት ምን ያህል እውነት እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ አረጋግጭልኝ አለኝ ። ብዙም አንገላታኝ ። በቦርሳዬ ውስጥ ያገኘውን ጽሁፍና ፎቶም ወሰደው በኋ ላም በብጫቂ ወረቀት ላይ ጽፎ አብራኝ ለምትኖር ህጻን አስይዞ የነእማማ ፋኖሴን ቤት አመላክቶ ላካት ።

ጋሽ መኩሪያም ሳይቆይ መጣ ። ተገን ይዞ ቆሞ ጠብ ቆት ነበርና ባላወቀው ጉዳይ ተጠርቶ የመጣውን ጋሽ መኩሪያን አቶ አሰፋ ደበደበው ። ” አለችና እንደተኮሳ ተረች ዞር ብላ መኩሪያን አየችው ።

መኩሪያ ግን በሀሳብ ተሰውሯል ። ምንጩ ከየት እን ደሆነ ያላወቀው አንድ ጽሁፍ ማሰላሰል ይዟል ። ጽሁፉ ካዘለው ብዙ ሀተታ መካከል መዞ ያወጣውን አባባል እያስተካከለ እያቃና ደጋግሞ በዐይነ ህሊናው አነበበው። ያነበበው ጽሁፍ እንዲህ ይላል ፤
ወላጇ ሆይ ፤

የማትፈጽመው ከሆነ ቃል አትግባልኝ ፤ ቃል ከገባ ህልኝ ደግሞ ፤

ቅጣት ከሆነ ይፈጸምብኝ ፤

ስጦታም ከሆነ ይሰጠኝ ። የሚለውን ነበር ።

ሕፃናትን በመናቅና ዝቅተኛ ግምት በመስጠት የማ ይፈጸሙ ቃልኪዳኖችን መግባት እንደማይገባና ከሕጻ ናትም ጋር ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ጥንቃቄ የሚያስ ፈልገው መሆኑን እያስተዋለ ራሱን ነቀነቀ ። ጨቅላዋ አሰለፈች በትንሿ ልቧ ቋጥራ ያሳደገችው ተስፋ እንደጐዳት አይቶ አዘነላት ። ምን እንደሚልና እንደሚያደርግ ባያ ውቅም በአሰለፈች ሊፈርድ አልቃጣም ። አሰፋ በልሁም

ቢሆን መውደድ በፈጠረው የቅናት ስሜት ተገፍቶ በፈጸመበት ድብደባ ሊጠላው አልሆነለትም ይልቁንም አዘነለት ። ሁሉንም በይቅርታ እይታ ተመለከታቸው ።

ክሱ ቢራዘምም ኖሮ መኩሪያ ወልደሩፌ በወንጀል የማይጠየቅ መሆኑን አረጋግጧል ። መቶ አለቃ አፈወርቅ የጉዳዩን ጭብጥ ካረጋገጠ በኋላ ነገሩን የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች ባሉበት በዕርቅ እንዲያልቅ ማድረጉ አጓጉል የተነሳውን ስሙን ለማደስ እንዲቻል አስቦ ነበር ።

አሰለፈች በዳኜ የልጅነት ትዝታዋን ወቅታዊ ስሜቷንና ዘለቄታዊ ምኞትዋን ከተናገረች በኋላ መቶ አለቃ እንዲገኙ የጋበዛቸው አንዳንድ የመሥሪያ ቤቱ ሰዎች አስተያየት ሰጥተው ዕርቀ ሰላሙ ወረደ ። አሰለፈች የጽዳት ሥራዋን የመንፈስ እርካታ ማግኛ የማየት ሱስዋን መወጫ ብታደርገውም ኑሮዋን የምትመራው በጕጃም በረንዳ ቅቤና ማር የሚነግዱት አባቷ በሚያደርጉላት ድጎማ ነው።

ምዕራፍ አራት

በአትክልትና በእጽዋት ግጥም ካለው የአቶ ተገኑ መታፈሪያ ግቢ ውስጥ የእኩለ ሌሊት ዝምታና አደብ ገሰው ፤ አሰግዴ ወርቁ ሃሣብ ያፍተለትላል ፤ ምንተስኖት ቁርጥማትዋን ታዳምጣለች ፤ አቶ ተገኑም ደረቅ ሣላቸውን ያለማቋረጥ ይስላሉ ። የጉለሌን ጅብ ጩኸት እያዳመጡ አጸፋውን የተቃርኖ ጩኸት የሚያሰሙት ሁለት ውሾች ቤቱን ይዞሩታል ።

ከእግሯ ወደ ጀርባዋ ከዚያም ወደ ክንድዋ ተመላልሶም እስከ ጭንቅላትዋ የሚሯሯጥባት የቁርጥማት ስሜት ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚሰነጥር ራስ ምታት ይተክልባታል ። በጀርባዋ ተንጋላ በአካሏ ውስጥ የሚመላለስባትን ሕመም ስታዳምጥ በአፍንጫዋ የገባው ቀዝቃዛ አየር ሁለቴ አስነጠሳት ። አሰግዴ ወርቁም አበታትሎ ጉሮሮውን አጸዳና እህህ አለ ።

አሰግዴ ወርቁ የአቶ ተገኑ መታፈሪያ ጨሰኛ የነበረ ሲሆን በሬውን ፈትቶ እርሻውን ጥሎ ለብዙ ዓመታት ከአቶ ተገኑ ጋር የኖረ ጠምዛዛ ወንዳወንድ መንዜ ነው ። ለምን ቀዬውን ለቆ ፤ ትዳሩን አፍርሶ እንደመጣ በውል ባይታወቅም በግድያ ወይም ጠንከር ባለ ወንጀል መታማቱ ኦልቀረም ። አቶ ተገኑ ከትልቅ ቤታቸው በስተጀርባ ለማድቤትነት ካሠሯቸው ሶሣት ክፍሎች መካከል